# የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መጻሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ

በ
አዳነች አበራ

በኢትዮጵያ ሥነፅሁፍና ፎክሎር
ኤም ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል
የሥነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 2001 ዓ.ም.

# የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መፃሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ

በ

አዳነች አበራ

በኢትዮጵያ ሥነፅሁፍና ፎክሎር
ኤም ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት
የቀረበ ጥናት

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል
የሥነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ፣2001 ዓ.ም.

# የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መፃሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ

በ

አዳነች አበራ

አማካሪ

አቶ ዘሪሁን አስፋው

በኢትዮጵያ ሥነፅሁፍና ፎክሎር
ኤም ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት
የቀረበ ጥናት

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል
የሥነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ፣2001 ዓ.ም.

# የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መፃሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ

በ

አዳነች አበራ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የሥነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዘሪሁን አስፋው ______________________ ______________________

አማካሪ

ዮናስ አድማሱ ______________________ ______________________

ፈታኝ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ኢ.ጥ.ተ.
ቤተ መጻሕፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

## መታሰቢያ

ምኞትና ሃሳብሽ ከግብ ደርሶ ለማየት ላልታደልሽው እናቴ የሿአለቃ ሙሉእመቤት ዘውዴ ይሁንልኝ።

## ምሥጋና


- ውድ ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው የጥናት ፅሁፌን ደጋግመው በማረምና ሙያዊ ምክር በመለገስ ለዚህ ደረጃ እንድደርስ ቀና ትብብራቸው ላልተለየኝ መምህሬና አማካሪዬ ለአቶ ዘሪሁን አስፋው ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ፡፡
- በታሪክ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት አቶ ሽመልስ ቦንሳ እንዲሁም አቶ ጌታሁን መስፍን ለጥናቴ አስፈላጊ መረጃዎችን በመጠቆምና በመስጠት፤ ጥናቴ አቅጣጫ እንዲይዝ ሞራልና ድጋፍ በመስጠት ስላበረታታችሁኝ ለዚህ ደርሻለሁ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፡፡
- ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ቤተ መፃሕፍት ሠራተኞች በሙሉ ላደረጋችሁልኝ ቀና ትብብር ክፍ ያለ ምሥጋና አቀርባለሁ፡፡
- እናንተ በማታውቁት ጉዳይ ፊት ስነሳችሁ፤ ለእናንተ መስጠት የነበረብኝን ፍቅር እና ጊዜ ስነፍጋችሁ በትእግስት ጠብቃችሁ ጥናቴን ላስጨረሳችሁኝ ባለቤቴና ልጆቼ እንዲሁም ቤተሰቦቼ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡
- ከጥናቴ መጀመሪያ አንስቶ እስከ ፍፃሜው ድረስ ሃሳብ እና ሞራል እየሰጠሽ ለዚህ ላደረስሺኝ ጓደኛዬ አዳነች ካሣ ምሥጋና ይገባሻል፡፡
- በትምህርት ቆይታዬ የክፍል ጓደኞቼ ለነበራችሁ በሙሉ ባለውለታዬ በመሆናችሁ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡
- ውድ ጊዜሽን ሰውተሽ የጥናት ፅሁፌን በመተየብ እና ደጋግመሽ በማረም ለተባበርሽኝ ወ/ሮ በለጠች ሽመላሽ ምሥጋናዬ ይድረስሽ፡፡
- በመጨረሻ ነገር ግን ከሁሉ መጀመሪያ እዚህ ያደረሰኝን አምላክ አመሰግናለሁ፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና....................II
ማውጫ....................III
አጠቃሎ....................VI
1. መግቢያ....................1
1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት....................2
1.2 የጥናቱ ዓላማዎች....................2
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ....................3
1.4 የጥናቱ ወሰን.................... 3
1.5 የጥናቱ ዘዴ....................4
1.5.1 የናሙና አመራረጥ....................4
1.5.1.1 የታሪክ መፃሕፍቱ አመራረጥ....................4
1.5.1.2 የዜና መዋዕሎቹ አመራረጥ....................6
1.6 የጥናቱ አደረጃጀት....................7
1.7 ያጋጠመ ችግር....................7
2. ክለሳ ድርሳናት....................8
2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት....................8
2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት....................9
2.2.1 የፎክሎር ብያኔ....................10
2.2.2 የፎክሎር ቅርፆች....................11
2.2.2.1 ሥነቃል....................11
2.2.2.2 ሀገረሰባዊ ልማድ....................11
2.2.2.3 ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት....................14
2.2.2.4 ቁሳዊ ባህል....................14
2.3 የፎክሎር አውድ....................15
2.3.1 ባህላዊ አውድ....................15
2.3.2 ማህበራዊ አውድ....................16
2.3.3 ታሪካዊ አውድ....................16
2.4 የታሪክ ምንነት....................17
2.4.1 የፎክሎርና የታሪክ ትስስር....................17

2.4.2 ፎክሎር በታሪክ ምንጭነት........................................................21

2.4.3 ፎክሎር ለታሪክ አፃፃፍ ያለው ጠቀሜታ..........................................23

3. የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ ትንተና..........................................................26

3.1 የፎክሎር ቅርፅ................................................................ 26

3.1.1 ሥነቃል.................................................................26

3.1.1.1 ቃልግጥም.....................................................26

3.1.1.2 ዝርው ትረካዎች........................................... ..........35

3.1.1.3 አጫጭር የሥነቃል አይነቶች..................................36

3.1.2 ሀገረሰባዊ ልማድ..........................................................39

3.1.2.1 ስያሜ.............................................................39

3.1.2.2 ሀገረሰባዊ መድሃኒት..............................................41

3.1.2.3 ሀገረሰባዊ ዕምነት................................................42

3.1.3 ትውን ጥበባት.............................................................43

3.1.4 ቁሳዊ ባህል................................................................45

3.1.4.1 አልባሳት..........................................................46

3.1.4.2 ልዩ ልዩ መገልገያ ቁሶች........................................48

3.1.4.3 ምግብ..............................................................49

3.2 የፎክሎር ፋይዳ....................................................................50

3.2.1 የታሪክ ተዋንያንን ማንነት ማሳየት...................................51

3.2.2 ለግጭት መንስዔና ውጤት መሆን........................................54

3.2.3 የዘመኑን መንፈስ ማሳየት..................................................57

3.2.3.1 ፖለቲካዊ ሁኔታ..................................................57

3.2.3.1.1 የስልጣን መሳሪያ ሲሆን....................................57

3.2.3.1.2 ድጋፍና ተቃውሞ መግለጫ ሲሆን........................58

3.2.3.2 ማህበራዊ ሁኔታ..................................................60

3.2.3.3 ባህላዊ ፋይዳ.......................................................62

3.2.4 ፎክሎር ለታሪክ መረጃ ምንጭነት......................................63

4. በታሪክ መፃሕፍቱና በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ በሚገኙ የፎክሎር ቅርፆች ላይ የተደረገ ንፅፅራዊ ትንተና................................................65

4.1 በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ቅርፆች..........................66

4.2 በታሪክ መፃሕፍቱ ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ቅርፆች........................69

5. ማጠቃለያና አስተያየቶች....................................................................74

5.1 ማጠቃለያ...........................................................................74

5.2 አስተያየት.......................................................................................... 76
ዋቢ መፃሕፍትና ፅሁፎች ........................................................................................78
አባሪ .......................................................................................................81

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በተመረጡ የታሪክ መፃሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ቅርፃችን በመለየት ፋይዳቸው ምን እንደሆነ የሚያሳይ ነው::

ለጥናቱ የተመረጡት መፃሕፍትም:- ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት ፣ ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት ፣ የዘመን ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት ከ1896-1922 ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1966 የተሰኙት የታሪክ መፃሕፍት እንዲሁም ታሪከ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ እና የቴዎድሮስ ታሪክ የተሰኙት ዜና መዋዕሎች ናቸው:: ጥናቱ በመፃሕፍት ንባብ ላይ የተካሔደ ስለሆነ መረጃዎቹም የተተነተኑት በይዘት ትንተና ዘዴና በንፅፅራዊ የጥናት ስልት ነው::

በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ ታሪክ ፀሀፊው ሃሳቡን ለመግለፅ የተጠቀመባቸው እንደ ምሳሌያዊ ንግግር ያሉት የፎክሎር ቅርፃች እንዲሁም ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ በራሳቸው እንደ ታሪክ ተዘግበው ይገኛሉ::

በመፃሕፍቱ ውስጥ ሥነቃል ፣ሀገረሰባዊ ልማድ ፣ትውን ጥበባትና ቁሳዊ ባሕል የተሰኙት የፎክሎር ቅርፃች ተገኝተዋል:: ከነዚህም ውስጥ የታሪክ ተዋንያኑን ማንነት የሚያሳዩ ፣ የዘመኑን መንፈስ (ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታ) የሚያመላክቱ፣ በዘመኑ ተከስተው ለነበሩ ግጭቶች መንስዔና ውጤት የሆኑ እንዲሁም በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉ የፎክሎር ቅርፃች ይገኛሉ::

በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ ጎልቶ የሚታየው የፎክሎር ቅርፅ ሥነ ቃል ሲሆን በታሪክ መፃሕፍቱ ውስጥ ቃል ግጥም ከፍተኛውን ስፍራ ይዟል:: ዋና ትኩረቱም ሙገሳንና ተቃውሞን መግለፅ ነው:: በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ ደግሞ አፈ ታሪክ ጎልቶ ይታያል :: ዜና መዋዕሎቹ ውዳሴያዊ ይዘት ያላቸው በመሆናቸው አፈ ታሪኮቹም ለዚሁ ተግባር የዋሉ ናቸው::

ፎክሎር ለታሪክ ድርሰት በመረጃ ምንጭነት፣ ለትረካው ውበትና ተነባቢነት እንዲሁም የታሪኩን ጭብጥ በማጉላት ረገድ ከፍ ያለ ጠቀሜታ አለው:: ስለዚህም ታሪክ ፀሀፊዎችና ተመራማሪዎች ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጡት ጥናቱ ያመላክታል::

## 1.መግቢያ

ፎክሎር ከበርካታ ሙያዎች ጋር ትሥሥር ያለው መስክ ነው። ለምሳሌ ከሥነ ፅሁፍ፣ ከሥነ ሰብዕ፣ ከሥነ ልሳን ፣ ከታሪክና ከመሳሰሉት ጋር የጠበቀ ዝምድና አለው። በዚህ ጥናት ትኩረት የተሰጠው ፎክሎር ከታሪክ ጋር ስላለው ትስስር ነው። ፎክሎር ለታሪክ በመረጃ ምንጭነት (Marwick:1989:210፣ Georges and Jones :1995:84) ፣የታሪክ ተዋንያኑን ውስጣዊ ማንነት ለማሳየት (Levine :1983:340) ፣የታሪኩን ጭብጥ ለማጠናከር (ክንፈ-ርግብ፣1973፣3) ታሪኩ ደረቅና አሰልቺ እንዳይሆን በቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ ፎክሎርን መጠቀም(Nye,1966:139). የሚሉት ፋይዳዎች እንዳሉት ምሁራኑ ያስረዳሉ።

ፎክሎር በታሪክ መፃሕፍት ውስጥ በምን ቅርፅ እንደሚገኝና ከላይ የተገለፁትን ፋይዳዎች ለመመርመር በተመረጡ ሰባት የታሪክ መፃሕፍት ላይ ጥናቱ ተካሂዷል። የኢትዮጵያ ታሪክ አፃፃፍ ከባህላዊ ወደ ዘመናዊ የአፃፃፍ ስልት በሂደት ተሸጋግሯል። ስለሆነም የጥናቱን ዓለማ ለማሳካት ሁለት ባህላዊ የታሪክ አፃፃፍ ስልትን የተከተሉ ዜና መዋዕሎች እንዲሁም አምስት«ዘመናዊ» የታሪክ መፃሕፍት ለጥናቱ ተመርጠዋል።

በዚህን ጊዜ እንዲህ ተብሎ ተገጠመ ፣አገሌ/አገሊት የሚባል የምትባል አዝማሪ ይህን ብሎ/ብላ አዘመረ/አዘመረች፣ አንዲት አልቃሽ የሚከተለውን አለቀሰች ወዘተ. በሚሉት ሀረጎች ቃል ግጥሞች በታሪክ መፃሕፍትና በዜና መዋዕሎች ውስጥ ይቀርባሉ። በተጨማሪም ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ትውን ጥበባት እና ቁሳዊ ባህል በታሪክ መፃሕፍትም ሆነ በዜና መዋዕሎች ውስጥ ይገኛሉ።

በርግጥ ፎክሎር ለታሪክ በመረጃ ምንጭነት መጥቀሙን በተመለከተ የተአማኒነት ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይሁንና ይህ ጥናት በታሪክ መፃሕፍቱም ሆነ በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ የሚገኙትን የፎክሎር ቅርፆች እውነትነት (ተአማኒነት) አይገመግምም። የፎክሎሩን ጥንተ ነገርም አይፈልግም። የጥናቱ ትኩረት ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ የተፃፉ መፃሕፍትን በመመርመር ፎክሎር በምን ቅርፅና ለምን ፋይዳ እንደገባ ማጥናት ነው።

ታሪክ ፀሀፊዎች በአፃፃፍ ስልታቸው የተለያዩ ናቸው። አንዳንዶቹ በታሪኩ ጣልቃ ቀልዶችን ፣ተረቶችን ፣ቃል ግጥሞችን ፣ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ ታሪኩ በተጠራበት ዘመን ከፍ ያለ ቦታ ያላቸውን ልማዶችንና ትውን ጥበባትን በጥቅሉ የፎክሎር ቅርፆችን በመጠቀም ይፅፋሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ «ዘመናዊ» የታሪክ ፀሀፊዎች የሚባሉት ማስረጃ የሌላቸውን በተለይም የሥነቃል ቅርፆችን ከመጠቀም ይቆጠባሉ። ስለሆነም የፎክሎርና የታሪክ ትስስር

እስከ ምን ድረስ እንደሆነና ለታሪክ አፃፃፍ ያለውን ፋይዳ በዚህ ጥናት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር ሥር ከሚሠጡት የፎክሎር ኮርሶች አብዛኛዎቹ ማለት ይቻላል የፎክሎርን ዘርፈ ብዙ ሙያነት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ፎክሎር ከሥነ ሰብዕ፣ ከታሪክ፣ ከሥነ ልሳን እንዲሁም ከሥነ ፅሁፍና ከመሣሠሉት ሙያዎች ጋር የጠበቀ ዝምድና /ትስስር/ አለው፡፡ ፎክሎር ከታሪክ ጋር ያለው ግንኙነት አንዱ በሌላኛው ውስጥ ሲገባ ሊኖረው የሚችለው ቅርፅና ፋይዳ ትኩረቴን ሊስበው ችሏል፡፡ በተለይ የ Georges and Jones ን Folklore as Historical Artifact ሳነብ የመመረቂያ ጥናቴን ርዕስ በፎክሎርና ታሪክ ዝምድና ላይ ለማድረግ ተነሳሳሁ፡፡ ይበልጥ የተገፋፋሁት ግን እላይ ባነሳሁት ሀሳብ መሠረት በሀገራችን ታሪክ ፀሀፊዎች ከተፃፉ መፃሕፍት ጥቂቶቹን ካነበብኩ በኋላ ነው፡፡

በታሪክ መፃሕፍቱ ውስጥ ለአብዛዎቹ ነገሥታት የንግሥና መንስዔ፣ በሀገረሰባዊ ልማድ መሠረት መሆኑ ለምሳሌ ስልጣንን ከዘር ወደ ዘር ወይም ከአባት ወደ ልጅ የማስተላለፍ ፣በትንቢት፣ በህልም መገለፅ የሚሉትን የመሳሰሉ መሆናቸው፤ ድጋፍና ተቃውሞን ገላጭ የሆኑ በርካታ ቃል ግጥሞች መገኘታቸው እንዲሁም ትዕምርታዊ የሆኑ ቁሶች መኖራቸውን ተገንዝቤያለሁ፡፡ በመሆኑም ፎክሎር ከታሪክ ጋር ያለውን የጠበቀ ትስስር በመረጃ አስደግፌ ለማሳየት የጥናት ርዕሴን በዚሁ ላይ ለማድረግ ወሰንኩ፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡፡

- ፎክሎር በተመረጡት የታሪክ መፃሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ በምን ቅርፅ እንደገባ ማሳየት፣
- የፎክሎር ቅርፃቹን ፋይዳ መተንተን፣
- የፎክሎር ቅርፃቹ በምን ሁኔታ ሊገቡ እንደቻሉ (ደራሲው ሆን ብሎ የጻፋቸው ወይስ እንደ ክስተት ተዘግበው?) የሚለውን መመርመርና ማሳየት፣
- የትኛው የፎክሎር ቅርፅ ጎልቶ እንደሚታይና ፋይዳውም ምን እንደሆነ መግለፅ፣
- የፎክሎርና የታሪክ ትስስር እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ማሳየት፣
- በታሪክ መፃሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ቅርፃች አንድነትና ልዩነታቸውን ለይቶ በማውጣት ማሳየትና ትንታኔ መስጠት፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ ፎክሎር እና ታሪክ ያላቸውን ትስስር በተግባር በማሳየት ረገድ ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ በዚሁ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ጥናታቸውን ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች እኔ የተጠቀምኩባቸው ንድፈ ሃሳቦችና የትንታኔ መረጃዎች መነሻ ሃሳብ ሊሰጧቸው ይችላሉ፡፡ ለታሪክ ፀሀፊዎች እና ተማሪዎችም የፎክሎርን ፋይዳ በማስገንዘብ ለፎክሎር ተገቢው ትኩረት እንዲሰጠው ያሳስባል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

የኢትዮጵያ ታሪክ በተለያዩ ኢትዮጵያውያን እና በውጭ አገር ሰዎች በባህላዊ እና በዘመናዊ ዘዴ ተፅፎ ይገኛል፡፡ ባህላዊ ዘዴ ሲባል ፀሀፊዎቹ በልማድ ከሚያውቁት፣ ካዩትና ከሰሙት መረጃ በመነሳት የራቸውን አስተያየት በመጨመር የሚፅፉት ሲሆን እንደ ዜና መዋዕል ያሉትን ይመለከታል፡፡ በአንፃሩ ዘመናዊ የአፃፃፍ ዘዴ በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመርኩዞ እና የታሪክ ጊዜ ቅደም ተከተልን ሳያዛቡ ስልታዊ በሆነ መንገድ መፃፍን የሚመለከትነው፡፡በዚህ መልኩ ፀሀፊዎቹ ስለነገሥታቱ ታሪክ፣ ስለልዩ ልዩ ታሪካዊ ድርጊቶችና ክስተቶች በርካታ መፃሕፍት ፅፈዋል፡፡

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በኢትዮጵያውያን ደራሲዎች በተፃፉ የታሪክ መፃሕፍት ላይ ብቻ ነው፡፡ መፃሕፍቱም የአማርኛ ሥነፅሁፍ ከአበበበት፣ የዘመናዊነትና የማዕከላዊነት ፅንሰ ሃሳብ ተግባራዊ መሆን ጀመረበት ከሚባለው ከዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን እስከ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ፍፃሜ ድረስ ያለውን ታሪክ የሚወክሉ ናቸው፡፡

መፃሕፍቱ ብዙ በመሆናቸው የጥናቱን ዓላማ ሊያሳኩ ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸው ሁለት ዜና መዋዕሎችና አምስት የታሪክ መፃሕፍት ተመርጠዋል፡፡ ስለ አመራረጣቸው ቀጥሎ ባለው ንዑስ ክፍል ቀርቧል፡፡

ምንም እንኳ በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ ያሉትን የፎክሎር ቅርፆች በሙሉ ለቅሞ አውጥቶ የፎክሎሩን መነሻ፣ የስርጭት ባህል፣ የለውጥ ሂደት ወዘተ. ማጥናቱ አስፈላጊ መስሎ ቢታይም ጥናቱ ከተነሳበት ዓላማ አንፃር ቅርፅና ፋይዳውን ብቻ በመመርመር ላይ ተወስኗል፡፡

## 1.5 የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ በመፃሕፍት ንባብ ላይ የተደረገ ሲሆን የተመረጡት የአጠናን ዘዴዎችም የይዘት ትንተና እና ንፅፅራዊ ጥናት የሚባሉት ናቸው፡፡ የይዘት ትንተና ዘዴ የተመረጠው፣ በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ቅርፆችንና ፋይዳቸውን ለመመርመር ሲሆን፣ በንፅፅራዊ ጥናቱም በታሪክ መፃሕፍቱና በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ቅርፆች አንድነትና ልዩነት ይታያል፡፡

### 1.5.1 የናሙና አመራረጥ

ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ በኢትዮጵያውያን የተፃፉ መፃሕፍት በርካታ ከመሆናቸውም ባሻገር አንዳንዶቹ ደረቅ ታሪክን የያዙ፣ ገሚሶቹ በታሪክ ምሁራን ዘንድ "ተረት" የሚባሉ ሌሎቹ ደግሞ ሃይማኖታዊ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ ተገቢ የሆኑ መፃሕፍትን ለመምረጥ ዓላማ ተኮር ንሞናን (Purposeful sampling) ተጠቅሚያለሁ፡፡ " በዚህ የንሞና አመራረጥ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ነው" (ያለው፣1998፣ 136)፡፡ በተጨማሪም ስለ ታሪክ ፀሀፊዎቹ የተሰጡ ሙያዊ አስተያየቶችን መሰረት አድርጌያለሁ፡፡

በዚህም መሰረት ፎክሎርን በታሪክ መፃሕፍትና በዜና መዋዕሎች ውስጥ ለማጥናት ይጠቅማሉ፣ የጥናቱን ዓላማ ያሳካሉ ያልኳቸውን አምስት የታሪክ መፃሕፍትና ሁለት ዜና መዋዕሎች መርጫለሁ፡፡

#### 1.5.1.1 የታሪክ መፃሕፍቱ አመራረጥ

የታሪክ መፃሕፍቱ በዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ያተኮሩ ሲሆን መነሻቸውን የዐፄ ቴዎድሮስን ዘመነ መንግስት አድርገው ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ፍፃሜ ላይ ያቆማሉ፡፡ ይህንን ዘመን ይወክላሉ እንዲሁም የጥናቱን ዓላማ ያሳካሉ ብዬ የመረጥኳቸው ደራሲያን እና ስራዎቻቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

1ኛ. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት
ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት
ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት

2ኛ. መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ የዘመን ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት ከ1896-1922

3ኛ. ባሕሩ ዘውዴ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1966

ከላይ የተጠቀሱት ደራሲዎችና መፃሕፍቱ ሲመረጡ የተለያዩ ምሁራን የሰጡትን አስተያየት ግምት ውስጥ በማስገባትና የጥናቱንም ዓላማ ያሳካሉ በሚል ነው። ስለ ፀሀፊዎቹ ከተሰጡት ሙያዊ አስተያየቶች ለአስረጅነት በጥቂቱ ልጥቀስ፦

**1.ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፦** ተክለ ፃድቅ ከ12 ያላነሱ የታሪክ መፃሕፍትን ፅፈውና ተርጉመው ለህትመት አብቅተዋል ስለ ስራዎቻቸውና ስለ አፃፃፍ ስልታቸው Bahru ሲገልፅ፦

*Takla Sadeq Makurya, the person who could be regarded as the bridge between these early modern historians and the current generation. His four volume history of Ethiopia forms the first major attempt at a comprehensive reconstruction of the Ethiopian past, using more or less the standard techniques of historical writing (1988,90).*

*ተክለ ፃድቅ መኩሪያ በቀዳሚ ዘመናዊ የታሪክ ፀሀፊዎችና በአሁኑ ትውልድ መካከል እንደ ድልድይ ሊታዩ የሚችሉ ፀሀፊ ናቸው። አራቱ የኢትዮጵያ ታሪክ ቅፆቻቸው (መፃሕፍታቸው) ይብዛም ይነስም የታሪክ አፃፃፍ መደበኛ ቴክኒኮችን ተከትሎ በመፃፍ ረገድ በጥልቀት የኢትዮጵያን ታሪክ በማዋቀር ሂደት ውስጥ በቀዳሚነት የሚጠቀስ ሙከራ ነው።*

ይላሉ። ተክለ ፃድቅ በርካታ የታሪክ መፃሕፍትን በአማርኛ ቋንቋ በመፃፋቸውና በተወሰነ ደረጃ በአፃፃፍ ስልታቸው ዘመናዊ የታሪክ አፃፃፍ ስልትን በመከተል የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፀሀፊ ሊሆኑ ችለዋል።

የደራሲው ሶስት ሥራዎችም የመመረጣቸው አንዱ ምክንያት ከላይ የተገለፀው አስተያየት ሲሆን በተጨማሪም ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ፣ ስለ ዐፄ ዮሐንስና ስለ ዐፄ ምኒልክ የዘመን ታሪክ በስፋትና በዝርዝር ያሰፈሩ በመሆናቸው እንዲሁም ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በብዛት በማካታተቸው ነው።

**2.መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ፦** ፀሀፊው የታሪኩ ተሳታፊ በመሆናቸውና ከስፍራው ከነበሩ ሰዎች የሰሙትን መረጃ በመጠቀማቸው መፅሐፉ በታሪክ መረጃነት የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍ ያለ ነው። እንዲሁም በሌሎች ታሪክ ፀሀፊዎች ብዙ ሽፋን ያልተሰጠው የአቤቶ ኢያሱ እና የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት ታሪክ በስፋት የቀረበበትና ስለ ዘመኑ የተሟላ ስዕል የሚሰጥ መፅሐፍ ነው። ከነዚህ ምክንያቶች በተጨማሪ የጥናቱ ትኩረት የሆነው ፎክሎር በስፋት የቀረበበትና የዘመኑን መንፈስ በማሳየት ረገድ ከፍተኛ ሚና የተጫወተበት ነው። ይህን በተመለከተ ዘውዴ የሚከተለውን ብለዋል፦

*የማኅበረሰብ ሁኔታዎችንም በተመለከተም አዶ ከብሬ እንዴት እንደተስፋፋ፣ በአጣን ታጅቦ ቡና የመጠጣት ባህል መቼ እና እንዴት በከተማ እንደተለመደ ፣ የሙጃሌ፣ የጣጣቴ፣ የኀዳር በሽታ አመጣጥ......... በመግለፅ የታሪኩን አድማስ ማስፋፋታቸው ከተለመደው ታሪክ ነገሥት አጻጻፍ የተለየ ያደርገዋል ( ዘውዴ ገብረ ሥላሴ ውስተ መርስዔ ኀዘን ፣1999፣5)::*

3. ባሕሩ ዘውዴ:- ከዘመናዊ የታሪክ ፀሀፊዎች አንዱ ናቸው:: አብዛኛዎቹ ዘመናዊ የታሪክ ፀሀፊዎች የኢትዮጵያን ታሪክ የፃፉት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሲሆን ባሕሩም በእንግሊዘኛ የፃፉትን ወደ አማርኛ መልሰው በመፀፋቸው በአማርኛ ከፃፉት ጥቂት ምሁራን መካከል ተጠቃሽ ሊሆኑ ችለዋል:: መፅሐፋቸውም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማስተማሪያነትና በማጣቀሻነት በማገልገል ላይ ይገኛል:: ከዚህ አንፃር በዘመናዊ የታሪክ አፃፃፍ ስልት ውስጥ ፎክሎር ያለውን ፋይዳ ለማሳየት መፅሐፉ ሊመረጥ ችሏል::

### 1.5.1.2 የዜና መዋዕሎቹ አመራረጥ

ዜና መዋዕል የጊዜን ቅደም ተከተል በመጠበቅ የሰፈረና የተጠናቀረ ግርድፍ የታሪክ ቅንብር ነው /ከነፈ-ርግብ፣1973፣2/:: ዜና መዋዕል የራሱ አፃፃፍ ባህሪ አለው:: የነገሥታቱ ልሳን በመሆኑ በግነት የተሞላና ውዳሴ አዘል ነው:: ዜና መዋዕል ነገሥታቱ በህይወት ሳሉ እና ከሞቱ በኋላ ይዘጋጃል:: ነገሥታቱ ካለፉ በኋላ የሚዘጋጀውም ቢሆን ያለፉትን በማንኳሰስ አሁን ያለውን በማወደስ የሚፃፍ ነው:: ከዚህ አንፃር ዜና መዋዕል ድክመት ቢኖርበትም "one has to give proper recognition to the value of chronicles as the basis, sometimes,the only one,for the reconstruction of the Ethiopian past. (Bahru,1988 :89):: ለዜና መዋዕሎች ተገቢውን ዕውቅና መስጠት ይገባል:: የኢትዮጵያን ያለፈ ታሪክ ለማዋቀር አንዳንድ ጊዜ ብቸኛ መረጃ ሊሆኑ ይችላሉ::

ለጥናቱ የተመረጡት ዜና መዋዕሎች በአለቃ ዘነብ የተዘጋጀው <u>የቴዎድሮስ ታሪክ</u> እና የጸሀፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ <u>ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ</u> ናቸው:: ሁለቱ ብቻ የተመረጡበት ምክንያት ዜና መዋዕል አሁን ባለንበት ዘመን ስለማይፃፍ ፎክሎር በዜና መዋዕል ውስጥ ምን ቅርፅና ፋይዳ እንዳለው በማሳየት ረገድ በቂ ነው በሚል እንዲሁም በመፃሕፍቱ ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በስፋት በመቅረባቸው ነው::

ስለ ፀሀፊዎቹ የተሰጡ አስተያየቶች:-

አለቃ ዘነብ (አስፋው፣1966):- ዜና መዋዕል በባህሪው ነገስታትን አወዳሽ ቢሆንም የቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ግን የተለየ ነው::

*He had greater freedom in expressing independent views than his predecessors and consequently he avoided exaggerating the facts.... He was more precise and accurate in describing the events which he witnessed while at the Emperor's court" (Sergew,1972:4).*

*ፀሀፊው በነፃነት ሃሳቡን ገልጿል። እንዲሁም እውነታዎችን ከማግነን ተቆጥቧል። የተመለከታቸውን ክስተቶችና እውነታዎችንም ቁጥብና ትክክለኛ በሆነ መንገድ አቅርቧል በተጨማሪም በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈ የመጀመሪያው ዜና መዋዕል ነው።* በመሆኑም ለጥናቱ ተመራጭ ሆኗል።

**ጸሃፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ** :- በአፃፃፍ ስልታቸው ከቀደምቶቹ የዜና መዋዕል ፀሀፊዎች የተለዩ አይደሉም። መፅሐፉ በግነትና በውዳሴ የተሞላ ነው።ልዩነታቸው በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈ በመሆኑ ነው (Sergew, 1972:5) ።ዐፄ ምኒልክ በኢትዮጵያ ታሪክ ጉልህ ሥፍራ የሚሰጣቸው በመሆናቸው ስለ እርሳቸው የተፃፈ መረጃ በመሆኑና የተለያዩ የፎክሎር ቅርፆችን በማካተቱ መፅሐፉ ተመርጧል።

## 1.6 የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች ቀርቧል። የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን ጠቅላላ ሁኔታ የሚያሳይና ለቀጣዮቹ ምዕራፎች መነሻ የሚሆን ሲሆን በሥሩም መግቢያውን ጨምሮ የጥናቱ ዓላማ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ ወሰን፣ ጠቀሜታዎችና ያጋጠሙ ችግሮች ተካተዋል። ሁለተኛው ምዕራፍ የንድፈ ሃሳብ ዳሰሳና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትን ሲያካትት ሦስተኛው በተመረጡ አምስት የታሪክ መፃሕፍትና በሁለት ዜና መዋዕሎች ውስጥ በሚገኙ የፎክሎር ቅርፆች እና ፋይዳቸው ላይ ትንታኔ የተሰጠበት ምዕራፍ ነው። አራተኛው ምዕራፍ በታሪክ መፃሕፍቱና በዜና መዋዕሎች ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ቅርፆች በንፅፅር የቀረቡበት ነው። ማጠቃለያ እና አስተያየት ደግሞ በምዕራፍ አምስት ቀርበዋል።

## 1.7 ያጋጠመ ችግር

ይህን ጥናት ለማካሄድ ስጀምር የገጠመኝ ዐብይ ችግር ጥናቱን የሚያግዙ የንድፈ ሀሳብ መፅሐፍት ማግኘት አለመቻሌ ነው። በመሆኑም ለጥናቱ መሰረት የሆኑ ንድፈ ሀሳቦችን ተጠቅሜ ጥናቱን ለማስኬድ ከፍተኛ ችግር ገጥሞኛ ነበር። ይሁንና ከተለያዩ መፅሐፍት ያገኘኋቸውን ንድፈ ሃሳቦች አሰባስቤ ወደ አንድ በማምጣት ችግሩን ለማቃለልና ጥናቱን ለመስራት ችያለሁ።

በጥናቱ ከሥነቃል ቅርፆች ውስጥ ቅኔያት፣ዘፈኖች፣እንጉርጉሮዎችና ቀረርቶዎች ከዝርው ዜና መዋዕሎች ጐን ለጎን ስለ አፄ ቴዎድሮስ ሁለንተናዊ የታሪክ ሁነቶች የሰጡት መረጃ ለአብነት ቀርቧል።

በክነፈ-ርግብ የቀረበው ጥናት የፎክሎር ዘርፍ የሆነው ሥነቃል ለታሪክ ፀሐፊዎች በመረጃ ምንጭነት ወይም/እና ጭብጥን ለማጉያነት ሊጠቅሙ እንደሚችሉ ግንዛቤ በመስጠቱ ከኔ ጥናት ጋር በተወሰነ ደረጃ ሊመሳሰል ችሏል። ይሁን እና የኔ ጥናት አጠቃላይ የፎክሎር ቅርፆችን በስፋት ከመዳሰሱም ባሻገር ፋይዳቸውን በዝርዝር የሚመረምር በመሆኑ ልዩነት ስላለው ጥናቱን ለማካሄድ ችያለሁ።

<u>ተረትና ታሪክ በኢትዮጵያ</u> በሚል ርዕስ ታደሰ ታምራት በ1984 ዓ.ም. በውይይት መፅሔት ላይ ያቀረቡት ሌላው ፅሁፍ ነው። ፀሐፊው ታሪክ ከተረት የሚለይባቸውን ባህሪያት ከገለፁ በኋላ ተረት በኢትዮጵያ የታሪክ መጻሕፍት አፃፃፍ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ማሳደሩን ያብራራሉ። ለዚህም ምክንያቱ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ምሁር ስለ ሀገሩ ያለው መሰረታዊ አስተያየት ከየተረቱና ከየአፈ ታሪኩ ያላለፈ መሆኑ እንደሆነ ያስረዳሉ። ለአብነትም የንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉዞን ታሪክ በተመለከተ በየታሪክ መፅሐፉ የሚገኘው መረጃ ተረት እንደሆነ ትንታኔ ይሰጣሉ።

አንድ የታሪክ ፀሐፊ ታሪክ ሲፅፍ ከህብረተሰቡ የሚሰበስባቸውን ቃላዊ መረጃዎች ወይም ሥነቃሎች እንዳለ በእምነት ተቀብሎ እውነትነታቸውን ሳያረጋግጥና ከተጨማሪ መረጃዎች ሳያመሣክር መፃፍ እንደሌለበትም ይመክራሉ። ፎክሎር በመረጃ ምንጭነት ስለማገልገሉና የተአማኒነት ጥያቄም ማስነሳቱ እንደማይቀር በኔም ጥናት ስለተነሳ ከታደሰ ፅሁፍ ጋር በመጠኑም ቢሆን ተመሳስሎ ሊፈጠር ችሏል። በታደሰ ፅሁፍ ፎክሎር ለታሪክ በመረጃ ምንጭነት መጥቀሙ ብቻ ነው የተመለከተው። ከዚህ ውጭ ስለ ፎክሎር ቅርፆች እንዲሁም ፋይዳቸው አልተገለፀም። በመሆኑም የፎክሎርን ልዩልዩ ቅርፆችና ሌሎች ፋይዳዎችን በስፋት ለማጥናት አስችሎኛል።

## 2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ባነሳሁት ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ የመስኩ ምሁራን ምን ምን ንድፈ ሃሳቦችን ፅፈዋል? እኔስ ከፅሁፎቹ ምን ምን የመነሻ ሃሳቦችን ይገኘ ነው ጥናቱን ያስኬድኩት? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል።

### 2.2.1 የፎክሎር ብያኔ

ፎክሎር ከሚሸፍነው ጉዳይ መስፋት የተነሣ ይሄን ያካትታል ይህን አያካትትም ብሎ ቅልብጭ ያለ ብያኔ ለመደንገግ ያስቸግራል፡፡ በመሆኑም በርካታ የፎክሎር ምሁራን ፎክሎርን ለመበየን በፎክሎር ውስጥ ይካተታሉ ያሏቸውን ጉዳዮች ብቻ ይዘረዝራሉ፡፡ ለምሳሌ Dundes ፎክሎር፤የፎክና የሎር ጥምር ቃል መሆኑን ገልፀው ፎክ የጋራ ጉዳይ ያላቸውን የትኛውንም የሰዎች ስብስብ ወይም ቡድን ያጠቃልላል ሲሉ ሎርን ደግሞ የቡድኑ የጋራ ጉዳይ የሆነውን ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም ቁሳዊ ነገሮችን ሀተታ ተፈጥሮን፣ አፈታሪክን፣ ተረቶችን ፣ቀልዶችን ፣ምሳሌያዊ ንግግሮችን ፣እንቆቅልሾችን ፣ሀገራዊ አልባሳትን ፣ሀገረሰባዊ ዳንሶችን ወዘተ...ያካትታል በማለት በመዘርዘር ብያኔያቸውን ያስቀምጣሉ (In Oring:1965:3)፡፡ Baumanም ስፋትና ጥልቀቱ የማይታወቀውን ፎክሎር በነጠላ መገለጫዎቹ ከመበየን ይልቅ ከባህላዊነቱ፣ ከማህበራዊ መሰረትነቱ እና ከውበቱ አንፃር መቃኘቱ ያዋጣል ይላሉ (ውስተ ፈቃደ፣ 1991፤5) ፡፡

Leach ደግሞ:- Folklore is the lore, erudition, knowledge, or teaching, of a folk, large social unit, kindred group, tribe, race, or nation, primitive or civilized through its history (1950, 690). ፎክሎር ያልሰለጠነ ወይም የሰለጠነ አንድ ማኅበረሰብ፣ሰፊ ማኅበራዊ ተቋም፣ ጎሣ፣ዘር ወይም ብሄር ልማድ፣ እውቀት፣ ትምህርት ወይም መማሪያ ነው፡፡ ካሉ በኋላ ፎክሎርን ሥነፅሁፋዊ፣ ሥነልሣናዊ፣ ሳይንሳዊ እና ድርጊታዊ በማለት በአራት ይከፍሉታል (1950, 690) ፡፡

ሥነጽሁፋዊ ፎክሎር ባሉት ውሥጥ ሀተታ ተፈጥሮ፣ አፈታሪክ፣ ተረት እና ቃል ግጥም ሲካተቱ፣ ሥነልሳናዊ ብለው ባሥቀመጡት ክፍል ውስጥ ደግሞ ንግግር፣ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ እንቆቅልሾችና ምሳሌያዊ ንግግሮች ይጠቀሳሉ፡፡

ፈውስ፣ ትንቢት መናገር እና ሀገረሰባዊ እምነቶች በሳይንሳዊ ፎክሎር ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ማለትም ሙዚቃ፣ ዳንስ፣ ጨዋታ፣ ክብረበአል፣ ድራማ፣ እደጥበብ፣ የምግብ ሥራ የመሳሰሉት በድርጊታዊ ፎክሎር ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ እነዚህን ከመሳሰሉት ዘርዛሪ ብያኔዎች ለጥናትም ሆነ ለምደባ የተሻለው የDorson የብያኔ ዘዴ መሆኑን ፈቃደ ይመክራሉ(1991 ፤10)፡፡ Dorson ፎክሎርን፣ ቃላዊ ሥነጽሁፍ፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እና ቁሳዊ ባህል በማለት በአራት ይመድቡታል (1972፤2-4)፡፡

### 2.2.2 የፎክሎር ቅርፆች

በDorson ምደባ መሰረት አራቱ የፎክሎር ቅርፆች ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል።

#### 2.2.2.1 ቃላዊ ሥነጽሁፍ

Dorson፣ ቃላዊ ፎክሎርን ቃላዊ ሥነጽሁፍ እያሉ ይጠሯቸዋል። እንደ እርሳቸው እምነት፣ ቃላዊ ፎክሎር በቃላት አማካኝነት በሚፈጠሩት በተረት፣ በአፈ ታሪክ፣ በሀተታ ተፈጥሮ፣ በቃል ግጥም፣ በምሳሌያዊ ንግግር፣ በእንቆቅልሽ(ህ)፣ በእንካስላንትያ ወዘተ... በመሳሰሉት ላይ የሚያተኩር ነው።

ይህ እኛ «ሥነቃል» የምንለው የፎክሎር ዘርፍ፣ የራሱ ባህሪይና ውበት ያለው በቋንቋ የሚደረስ የሰዎች ሃብት ነው። በባህሪው ህዝባዊ ሲሆን፣ የሚፈጠረውም ለተግባር ነው። ህዝባዊ ነው ሲባል፣ በህዝብ ተፈጥሮ፣ በህዝብ በኩል፣ ለህዝብ (ለትውልድ) የሚተላለፍ በመሆኑ ነው። ተግባራዊ ነው ሲባል ደግሞ ቃላዊ ክዋኔንና የፈጣሪውን ማህበረሰብ ባህል፣ ታሪክ፣ የህይወት ፍልስፍናና ርዕዮተ-ዓለም አቅፎ የያዘ በመሆኑ ነው።

የሰው ልጅ ከተፈጥሮና ከአካባቢው ጋር ከሚያደርገው መሥተጋብር እና እርስበርሱ ከሚነጋገረው እውነታ በመነሳት ብዙ የሥነቃል ዐይነቶችን ይፈጥራል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሰው አካባቢውን ባለመቆጣጠሩ የተነሳ ከሚመጣበት አደጋ ራሱን ለመጠበቅ ለመዝናናት፣ ሥነ ምግባር ለማስተማር እና ለመሳሰሉት ተግባራት የሚፈጥራቸው ወጎች ናቸው እነዚህ ሥነቃሎች። ሥነቃሎች ከተፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ የየትውልዶችን ወቅታዊ አሻራ ተከትለው የየዘመኑን ወግና ልማድ፣ እምነትና ፍልሥፍና እንዲሁም የማህበረሰቡን የሥልጣኔ ደረጃ ሲገልፁ ይኖራሉ።

Luthi በቃል የሚገኙትን የፎክሎር አይነቶች በሶስት ከፍለው አብራርተዋቸዋል። እነዚህም ሥድንባባዊ አፋዊ ትረካዎች፣ ቃልግጥም እና ገላጭ ንግግሮች ናቸው (1986:10)። አፋዊ ትረካዎች ሀተታ ተፈጥሮን፣ አፈ-ታሪክንና ተረትን፣ ሲይዙ፣ ቃላዊ ግጥሞች ደግሞ መዝሙሮችን፣ እርግማኖችን፣ ለቅሶዎችን እና ሙገሳዊ ግጥሞች ያካትታሉ። ገላጭ ንግግሮች የሚባሉት ደግሞ ምሳሌያዊ ንግግሮችና እንቆቅልሾች ናቸው።

#### 2.2.2.2 ሀገረሰባዊ ልማድ

ልማድ አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ አንድን ሁኔታ ወይም ሁነት ሆንብሎም ይሁን በአጋጣሚ በተደጋጋሚ ሲከውን፣ ሲሰራ ወይም ሲናገር፣ ለዚያ ሁኔታ ወይም ሁነት የሚሰጥ ስያሜ ነው። ሀገረሰባዊ ልማድ ሲባልም አንድ ማህበረሰብ በቆዬው ልማዱ ሥር

## 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ሁለት መሠረታዊ ርዕስ ጉዳዮች ተነስተዋል:: የመጀመሪያው ከኔ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች የተቃኙበት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ የያዝኩትን ርዕስ ጉዳይ በተመለከተ በመስኩ ምሁራን ዘንድ የተፃፉ ንድፈ ሃሳቦች የቀረቡበት ነው::

### 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ትኩረታቸውን በፎክሎር ላይ ያደረጉ የዲግሪ ማሟያ ጥናቶችና የሴሚናር ፅሁፎች በተለያዩ ሰዎች ተዘጋጅተዋል:: ይሁን እንጂ ከነዚህ ሥራዎች ውስጥ ትኩረቱን የፎክሎርን ዘርፎችና ፋይዳቸውን በታሪክ መፃሕፍት ውስጥ በመመርመር ላይ ያደረገ ፅሁፍ የለም :: የሚከተሉት አንድ ዲማፅና አንድ ለሴሚናር የቀረበ እንዲሁም በመፅሔት ላይ የታተመ ጥናት ባነሱት ርዕስ ጉዳይ ከኔ ጥናት ጋር መጠነኛ ተዛምዶ እንዳላቸው ተረድቻለሁ:: በተዛማጅነታቸውም ቃኝቻቸዋለሁ::

እሸቴ ዳምጤ በ1995 ዓ.ም « ስለአፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስ እና አፄ ምኒልክ የተነገሩ የአማርኛ ቅኔያት ይዘት ንፅፅራዊ ጥናት» በሚል ርዕስ ዲማፅ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል አቅርበዋል::

የእሸቴ ጥናት ትኩረት በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ስለሚጠቀሱ ሶስት ገናና ነገሥታት በተነገሩ ቅኔያት ላይ ነው:: አጥኚው ቅኔያቱን በአማርኛ ቋንቋ ከተፃፉ የታሪክ መፃሕፍት ፣ መፅሔቶችና ያልታተሙ ታሪካዊ ሰነዶች እንዳሰባሰቧቸው በጥናታቸው መግቢያ ላይ ገልፅዋል :: የቅኔያቱንም ይዘት በመርመር የነገሥታቱን ግላዊ ባህሪ ማለትም ደግነት፣ጀግንነት፣ጨካኝነት አሳይተዋል::

የእሸቴ ጥናት ቅኔያት ላይ ያተኮረና ይዘቱን ብቻ የሚመረምር ከመሆኑ አንፃር ከኔ ጥናት ሊለይ ችሏል:: ይህን ልዩነት መሰረት አድርጌ በታሪክ መፃሕፍት እና በዜና መዋዕሎች ውስጥ የፎክሎርን አጠቃላይ ቅርፃች እንዲሁም ፋይዳቸውን እንድመርመር አስችሎኛል::

ክነፈ-ርግብ ዘለቀ በ1973 ዓ.ም ለትውፊት ሴሚናር «የቃል ታሪክ» በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርበዋል:: ጥናቱ ያልተማረው ሕዝብ የራሱን መደባዊ አመለካከት፣አስተሳሰብ እንዲሁም የተፈፀመውን ታሪካዊ ድርጊት በሥነ ቃሉ እየመዘገበ ከትውልድ ትውልድ እንዴት ማስተላለፍ እንደቻለ ያስገነዝባል::

ሆኖ በጋርዮሽ መኖሩን ማሳያ ነው። ለሀገረሰባዊ ልማድ ትልቁ ነገር የግለሰቦች ድርጊት ሳይሆን የቡድኖች መስተጋብር ነው። ለዚህም ነው Dorson "one such area we may call social folk custom. Here the emphasis is on group interaction rather than on individual skills and performances" (1972:3). አንዱ እንዲህ አይነቱ ዘርፍ ሀገረሰባዊ ልማድ ሊሆን ይችላል። የዚህ ትኩረቱ ያለው በግለሰብ ዕወቀት እና ክዋኔዎች ላይ ሳይሆን በቡድን መስተጋብር ላይ ነው ያሉት።

ሀገረሰባዊ ልማድ የአንድ ህብረተሰብ የጋራ ይዞታ የሆኑ ልማዶች መጠሪያ ነው። ልማዶቹ በዘር፣ በቀዬ፣ በክልል፣ በሥራ፣ በሃይማኖት፣ በፆታ ወይም በእድሜ ተለይተው ሊቆሙ ለሚችሉ ቡድኖች፣ መታወቂያ ናቸው። ልማዶቹም በመደረግ፣ በመገለጽ፣ በመከወን እና በመነገር ይተላለፋሉ። በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ሌሎች አራት ንዑሳን ክፍሎች አሉ። እነዚህም ፌስቲቫልና ክብረ በዓል (ከበራ)፣ መዝናኛዎችና ጨዋታዎች፣ ሀገረሰባዊ መድሃኒት እና ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ናቸው (ፈቃደ፣1991፣13)።

ሀገረሰባዊ ፌስቲቫሎች በሰዎች የህይወት ጉዞ ውስጥ የሚገኙና ከበራና ድግስ የሚያጅባቸው የማህበራዊ ኑሮ አጋጣሚዎች ናቸው። ለዚህም ልደትን፣ጋብቻን፣ ሹመትን፣ ምረቃን፣ ሥራ መያዝን፣ ጡረታን፣ ሞትን የመሳሰሉትን እና እነሱን አጅበው የሚከሰቱትን ማህበረሰባዊ ልማዶች ምሳሌ አድርጎ መውሰድ ይቻላል።

ክብረበአል በተወሰነ ጊዜ እየተደጋገመ የሚመጣ ማህበረሰባዊ ልማድ ነው። በክብረበአል ወቅት፣ እያንዳንዱ የማህበረሰቡ አባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁኔታ የሚሳተፍበት እድል አለው። ለምሳሌ ያህልም፣ በቅዱሳን ቀናት፣ በሃይማኖታዊ ቀናት (ገና፣ ፋሲካ፣ ልደታ፣ አረፋ፣መወሊድ፣ህዳር ሚካኤል ወዘተ)፣ በስፖርት ቀናት በሚደረጉ ሥነሥርዓቶች የማህበረሰቡ አባላት እንደየእምነትና ፍላጎታቸው ይሳተፋሉ። ፈቃደ ስለዚህ ጉዳይ ሲያብራሩ «የፌስቲቫል ዓቢይ ጉዳይ ተደርጎ የሚታየው ሰዎች ባንድነት ሆነው እንዲጫወቱና እንዲቦርቁ ማድረግ ነው። በዚህ ቡድናዊ ቡረቃም ግለሰቡ እና ማኅበሩ አንፃራዊ የሆነ የነፍስ፣ የአእምሮ ይባል የሥነልቡና «ዕዳት» (cleansing) ያገኛሉ» (1991፣14) ይላሉ።

ሌላው የሀገረሰባዊ ልማድ ክፍል ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ነው። የተለያዩ ሃይማኖታዊ ክዋኔዎችን የሚመለከት ሲሆን ከሀገረሰባዊ ሃይማኖት ጋር አብሮ የሚጠናው ሀገረሰባዊ እምነት ነው። ሀገረሰባዊ እምነት አንድ ህዝብ ተፈጥሮንና የወዲያ በኩል (ሰማይ ቤት) የሚባለውን ዓለም የሚረዳበትና ያንን ዓለም ለመተርጎም የሚገለገልበት መሣሪያ ነው። ይህ አይነቱ እምነት የሚፈጠረው በህዝቡ ዘንድ እውቅና ላገኙ አንዳች ተጨባጭ ቁሳዊ ነገር (ጀበና፣ ዛፍ፣ ድንጋይ፣ ወዘተ...) ወይም ባዕድ አምላክ ላይ መመካት ሲጀመር ነው።

ከሀገረሰባዊ እምነቶች አንዱ ምልኪ ነው። ምልኪ ይገጥማል ተብሎ የሚታሠብን ጥሩ እድል ወይም መጥፎ አጋጣሚ ወይም ገድ ከሌሎች እምነታዊ ሁነቶች፣ ድርጊቶችና ክስተቶች ጋር በማያያዝ ለመተንበይ የሚሞክር ልማዳዊ ትንበያ ነው። ምልኪ በባህሪው በሶስት ይከፈላል ተለምዶአዊ፣ መስዋዕታዊ እና መናፍስታዊ (Georges and Jones 1995:158)።

የመጀመሪያው የምልኪ አይነት ማስነጠስን፣ ማዛጋትንና የአይን መርገብገብን የመሳሰሉትን የሚያካትት ሲሆን፣ ለነዚህ ድርጊቶች አንዳች የሆነ ተለምዶአዊ ትርጉም የሚሰጥ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በደም ላይ ያነጣጠረ ነው። ከማህበረሰቡ አባላት ለእርድ ወይም ማህበረሰቡ የሚያምንበት መንፈስ ላረፈበት እንስሳ፣ ዛፍ፣ ድንጋይ ወይም ሌላ ነገር በስጦታ መልክ የሚቀርብበት እምነት ነው። ሶስተኛው የሙት ሰዎች፣ የአጋንንት ወይም የአማልክት መንፈስ እንዴት ከማህበረሰቡ አባላት ጋር በተለያዩ መንገዶች ሊቆራኝ እንደሚችል የሚያትት ሀገረሰባዊ እምነት ነው።

ሌሎቹ የሀገረሰባዊ እምነት ክፍሎች ደግሞ፣ ጣኦት፣ ጥንቆላ (ድግምት)፣ የሙት መንፈስ እና ዛር ናቸው። ጣኦት የመለኮት ሃይል አላቸው ለሚባሉና መንፈሱ ለሚያርፍባቸው ግዑዝ ለሆኑ አካላት መገዛትን የሚመለከት ሲሆን፣ ጥንቆላ ደግሞ ከአምላክ መገናኛ የተለየ ተሠጥኦና ቋንቋ አላቸው በሚባሉት ሠዎች የማመን ክስተት ነው። የሙት መንፈስ የሚባለው እምነት፣ በሞቱ ሰዎች መንፈስ መታመንን የሚያሳይ ነው። ዛር ደግሞ፣ የግሉ የሚያደርግ እና የሚቆጣጠር መንፈስ ሠፍሮብኛል ብሎ ማመንን ይመለከታል።

አራተኛው የሀገረሰባዊ ልማድ ክፍል ሀገረሰባዊ መድሃኒት (folk medicine) ነው። ይህ አይነቱ ልማድ ሣይንሳዊ መሠረት የሌለው ነው። ምንነቱን በተመለከተ ፈቃደ ሲያብራሩ፣

> *የሀገረሰብ መድኃኒት ጥናትም ተፈጥሮአዊ (ኔቸራዊ) መድኃኒትን፣ ጥንቆላዊ (magico-religious) መድኃኒትንና ባንድ ወቅት ከሳይንሳዊ መድኃኒት ይቆጠሩ የነበሩና በሳይንሳዊው ምርምር መዳበር ምክንያት ከሀገረሰብ መድኃኒት ጎራ እየተካተቱ የሚታዩትንና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ያጠናል ማለት ይቻላል (1991፣14) ይላሉ።*

### 2.2.2.3 ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ሙዚቃን፣ ጭፈራንና ድራማን ያካትታል:: በእርግጥ ሙዚቃ፣ ጭፈራና ድራማ ብቻቸውን የሚቆሙ ትውን ጥበባት አይደሉም:: በተግባር ጊዜ አንዱ ባንዱ ውስጥ ይኖራል እንጂ:: ሙዚቃን ከጭፈራ፣ ጭፈራን ከሀገረሰባዊ ድራማ ለይቶ ማየት አይቻልም:: ሌላው ቀርቶ ሀገረሰባዊ ልማድን (ከበራን፣ ፌስቲቫልን፣ ክብረበአልን ወዘተ..) ከነዚህ ትውን ጥበባት ውጭ ማሰብ ከባድ ነው:: ይህም፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የጠበቀ ተዛምዶ እንዳላቸው ያሳያል:: Dorson "The performing folk arts-we think primarily of traditional music, dance and drama" (1972:4). ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ስንል በቅድሚያ ባህላዊ ሙዚቃ፣ ጭፈራንና ድራማን ማሰብ ይኖርብናል በማለት የገለፁአቸው እነዚህ ዋነኛ የትውን ጥበባት ንዑሳን ዘርፎች፣ ከሀገረሰባዊ ልማድ ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ጥበባቱን ለመተወን ሲባል፣ ከሚለበሱት አልባሳት፣ ለመጫወቻነት ከሚይዙት ቁሳቁስ እና ትወናውን ከሚፈጽሙበት ቤት፣ አካባቢ ወይም ሜዳ፣ በጥቅሉ ከቁሳዊ ባህል ጋርም የጠበቀ ግንኙነት አላቸው::

### 2.2.2.4 ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህል፣ ሰዎች ስብአዊ የሆኑ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ለመግለጽ፣ እምነታቸውን፣ ርዕዮት ዓላማቸውን፣ ለሥነውበት ያላቸውን አድናቆት እና ጥበባዊ ችሎታቸውን ለማሳየት ሲሉ የሚያበጁት ቁስ ነው::

ቁሳዊ ባህሎች በአንድ ዘመን የነበረውን ማህበረሰብ ማንነት፣ ማህበረሰቡ የደረሰበትን የእድገት ደረጃ፣ ማህበረሰቡ ይከተል የነበረውን ዓለማዊና መንፈሳዊ ፍልሥፍናን ይገልፃሉ:: "Material culture has in common that it is tangible-can be touched, seen, eaten or lived in."(Sims, 2005:13) ቁሳዊ ባህል የጋራ የሆነ ባህሪ አለው:: ይኸውም ይዳሰሳል፣ ይታያል፣ ይበላል ወይም በውስጡ ይኖርበታል:: በባህሪያቸው ተጨባጭ በመሆናቸው ሳቢያም፣ ቁሶቹ የተሠሩበትን ዘመን መንፈስ ጠብቀው ለረጅም አመታት ይቆያሉ:: ቁሳዊ ባህል ሀገረሰባዊ እጅሥራ፣ ሀገረሰባዊ ስዕል፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ሀገረሰባዊ አልባሳት እና ሀገረሰባዊ የምግብ አሠራር የሚባሉ አምስት ንዑሳን ዘርፎች አሉት (ፈቃደ፣1991፣15)::

በእጅ የሚዳሰሱት፣ በአይን የሚታዩት፣ እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች፣ የራሳቸው ልዩ ጠባይ አላቸው:: ይኸውም በፎቶግራፍ ማንሻ ተነስተው፣ በቪድዮ ተቀርፀው እና በፊልም ተቀድተው በቋሚነት መቀመጥ መቻላቸው ነው:: በአንድ ወቅት የመጥፋት እጣፋንታ

ቢገጥማቸው እንኳ እንደሌሎቹ የፎክሎር ቅርፆች (ሥነቃል፣ እምነት ወዘተ) ተረስተው አይኖሩም።

ቁሳዊ ባህሎች ይጠናሉ፤ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድም ይተረጎማሉ። "Material culture reflects human behavior which can be interpreted through scientific classifications, methods and techniques" (Mayo,1984:11). ቁሳዊ ባህል ሳይንሳዊ ምደባ፣ዘዴና ብልሃትን በመጠቀም የሰውን ባሕሪ ያንፀባርቃል ይተነትናልም።

በቁሳዊ ባህል የሚጠኑት ቁሶች ከተምሳሌታዊነት፣ ከባህላዊነት ፣ ከማሕበራዊነትና ከመሳሰሉት አንፃሮች ሊጠኑ ይችላሉ። ከተምሳሌታዊነት ሲባልም ቁሶች ከዘወትራዊ አገልግሎታቸው ባሻገር ለአንድ ነገር ውክልና የመቆም (የመመሰል) ችሎታ አላቸው። ለአብነት ሥልጣንን ፣የሃብት ደረጃን ፣ሃይማኖታዊ ይዘትን ወዘተ. ሊያመለክቱ ይችላሉ።

## 2.3 የፎክሎር አውድ

ፎክሎርን ያለ አውድ ማሰብ ፈጽሞ አይቻልም። ፎክሎርን ለመረዳትም ሆነ ፋይዳውን ለማወቅ፣ ፎክሎሩ የዋለበትን አውድ ማየቱ ተገቢ ነው። ሦስት አይነት አበይት አውዶች አሉ እነዚህም ባህላዊ አውድ፣ ማህበራዊ አውድ እና ታሪካዊ አውድ ናቸው።

### 2.3.1 ባህላዊ አውድ

አንድ የፎክሎር ባለሙያ፣ ፎክሎሩንና የፎክሎሩን ተግባር ከማጥናቱ በፊት ለአንድ ነገር ቅድሚያ መስጠት አለበት። ይኸውም የዚያን የሚያጠናውን ማህበረሰብ ፎክሎር ባህላዊ አውድ መመርመር አለበት። የዚያ ማህበረሰብ ባህል ምንድነው? ያ ማህበረሰብ የሚኖረው ህይወት ምን ይመስላል? የዚያ ማህበረሰብ ቋሚ እሴቶች ምንድናቸው? የማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነት፣ ሀገረሰባዊ የህይወት አተያይ፣ ጠቅላላ የህይወት ፍልሥፍናው እንዴት ይገለፃል? እነዚህ እላይ የጠቀስናቸው ነጥቦች በፎክሎሩ (በዚያ ማህበረሰብ) ውሥጥ ይንፀባረቃሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች መጠየቅና ለጥያቄዎቹም ተገቢ የሆኑ መልሶችን ማፈላለግ ይገባል። Bauman ቀጣዩን ሃሳብ አቅርበዋል፤

> *The most fundamental aspect of cultural context with regard to folklore centers on the problem of understanding. What is the information one needs to know about the culture and the community in order to understand the context, the meaning. What aspects of the people's way of life are expressively represented projected, transformed in their*

*folklore and what systems of belief and value underlie the relations independence (In Dorson, 1983:363).*

*በፎክሎር ውስጥ የባህላዊ አውድ መሰረታዊ ገፅታና ጉዳይ የሚያርፈው በግንዛቤ ማነስ ላይ ነው። ዐውዱን ወይም ፍቺውን ለመረዳት ስለባህሉ እና ስለማህበረሰቡ አጥኚው ሊያውቀው የሚገባው መረጃ ምንድነው፣ የባህላዊ ቡድኑን የአኗኗር ዘይቤ (ስልት) ገፅታ በፎክሎሩ ውስጥ ተወክሏል፣ ኀልቶና ተለውጦ ቀርቧል፣ በተጨማሪም የዚህ ግንኙነት ተደጋግፎ መሰረት የሆኑት የትኞቹ የዕምነትና የዕሴት ሥርዓት ናቸው።*

የአንድ ማህበረሰብ ፎክሎር፣ የባህሉ ነፀብራቅ ነው። የማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ በፎክሎሩ ውስጥ በጉልህ ይታያል። በመሆኑም፣ ባህላዊ አውድን ግምት ውስጥ ያላስገባ የፎክሎር ምሁር፣ የፎክሎሩን ተግባራት በደንብ ሊያውቅ አይችልም። በባህላዊ አውድ ውስጥ የግለሰቦች፣ የቡድኖች፣ እንዲሁም የጠቅላላው ማህበረሰብ (አገር) ባህል መኖሩንም መረዳት ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

### 2.3.2 ማህበራዊ አውድ

በማህበራዊ አውድ፤ እንደ ባህላዊ አውድ ሁሉ የግለሰቦች፣የቡድኖች እና የጠቅላላ ማህበረሰቡ ተሳትፎ ትልቅ ቦታ ሊሰጠው እንደሚገባ Bauman ገልፀዋል (In Dorson, 1983:365). ከዚህም በተጨማሪ ተፈጥሮአዊ አውድ እና ሁኔታዊ አውድ መጠናት እንዳለባቸው አክለው ገልጸዋል።

ነገር ግን ቅድሚያውን የሚወስደው የፎክሎሩ ባለቤት (ተናጋሪው፣ ተራኪው) ነው። የትረካውን እግር ተከትሎ መቼ? እንዴት? ለነማን? በምን አይነት አኳሃን? በምን አይነት ውበት? ቀረበ የሚሉት ተለጣጣቂ ጥያቄዎች ይነሳሉ። ማህበራዊ አውድ ድርጊቱንና ባህሉን ብቻ ሳይሆን፣ ድርጊቱና ባህሉ የቀረበበትን መንገድ፣ ድርጊቱንና ባህሉን ያቀረበውን አካል፣ ድርጊቱን የታደመውን ህዝብ፣ ድርጊቱና ባህሉ የቀረበበትን ቦታና ጊዜ ሁሉ ይመለከታል።

### 2.3.3 ታሪካዊ አውድ

ሌላው ፎክሎር አጥኚው ሊያውቀው የሚገባው አውድ ታሪካዊ የተባለውን ነው። ታሪካዊ አውድ በአንድ ተጠኚ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰትን ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ማህበራዊ እና ባሕላዊ ሁኔታዎችን የሚያሣይ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በየልቦለዱ ፣ በስእል ስራ ላይ አልያም በሌሎች ባህላዊ የጥበብ ስራዎች ላይ ይንፀባረቃሉ (Marwick,1989:10) ። ስለሆነም ታሪካዊ አውዶችም ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

## 2.4 የታሪክ ምንነት

ታሪክ ስለአለፈ ክስተት የሚያጠና የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ነው። በአንድ ወቅት የተፈፀመን ድርጊት አለፈ፤ አከተመ ብለን ልንተወው አንችልም። ምክንያቱም ያ ያለፈው ክስተት አሁን ከምንገኝበት ሁኔታ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ይገናኛል። እንዲሁም የወደፊት አቅጣጫን ያመላክታል። "History is not the past . History is a story about the past, told in the presnt, and designd to be useful in constructing the future" ( Oman 1996,6)። ታሪክ ያለፈ ነገር ማለት አይደለም። ታሪክ ስላለፈ ክስተት አሁን ላይ ሆኖ የሚተርክ፣ የወደፊቱንም ለመገንባት የተዋቀረ ነው። ስለሆነም ወቅታዊ ችግሮችን ለመረዳት፤ ስለወደፊቱም ለማለም ስለ አለፈው ሁነት መሰረታዊ እውቀት ያስፈልጋል። ያም የሚገኘው ከታሪክ ነው።

በርግጥ ሁሉም ያለፈ ነገር የታሪክ መረጃ ሊሆን አይችልም፤ በታሪክ ባለሙያም አያስተናገድም፡ እናም የታሪክ ባለሙያው ተግባር የሚፈልጋቸውን መረጃዎች የቃል፣ የቁስም ይሁን የፅሁፍ ማሰባሰብና ስለ መረጃዎቹ ተገቢነትና ትክክለኝነት እንዲሁም ተአማኒነት ማረጋገጥ ነው። ዓላማውም እውነትን ለማግኘት መሞከር ነው። ለዚህም ነው ታሪክ የምርምር ተግባር ነው የተባለው (Marwick 1989, 18) ።

ታሪክ ሰፊ ሙያ ነው። በታሪክ ግለሰብ፣ ሀገር፣ ህዝብ፣ ባህልና የመሣሰሉት ይጠናሉ፤ ይፃፉሉም። ለዚህም ነው Marwick "Everything has a history, history as a body of knowledge and as a discipline covers every thing" (1989:18). ሁሉም ነገር ታሪክ አለው። ታሪክ እንደ አንድ የዕውቀት ክፍል እና እንደሙያ ሁሉንም ነገር ይዳስሳል ያሉት።

### 2.4.1 የፎክሎርና የታሪክ ትስስር

ፎክሎርና ታሪክ በተለያየ አቅጣጫ የቆሙና ፍፁም የማይገናኙ እንዲያውም የሚፃረሩ ሙያዎች እንደሆኑ አድርጎ የማሰብ ነገር አለ። ነገር ግን ፎክሎርም ሆነ ታሪክ ሰዋዊ ክስተት በመሆናቸው በጥልቀት ሲጠኑ ትስስር እንዳላቸው ማወቅ ይቻላል። " A close look at the origin and nature of history reveals a much closer kinship to folklore than we might suspect at first glance — and in some respects a continued relationship" [Campa,1965:1]. ከመጀመሪያ ቅፅበታዊ ዕይታ ልናገኝ

ከምንችለው ይበልጥ የታሪክ ምንጭ እና ተፈጥሮ በቅርበት ሲጤን ከፎክሎር ጋር የቀረበ ዝምድና እና በአንዳንድ ረገድ ቀጣይነት ያለው ግንኙነትም እንዳለው ይታያል በማለት Campa ሲያስረዱ እነ Sims ደግሞ:-

*The study of folklore touches on every dimension of human experience and artistic expression. In many ways, it is the study of culture, visual and performing arts, sculpture, architecture, music theater, literature, linguistics, and history rolled into one (Sims,2005:3).*

*የፎክሎር ጥናት የሰውን ልጅ የህይወት ልምድና ጥበባዊ ገለፃን በሁሉም አቅጣጫ ይነካል:: በብዙ መንገድ የባህል የሚታዩና የትውን ጥበባት የቅርፃቅርፅ የሥነ ህንፃ የሙዚቃ የትያትር የሥነጽሁፍ ሥነ ልሳን የታሪክ በአንድ አድርጎ የሚያጠና ነው::*

በማለት የፎክሎርን ዘርፈ ብዙ ሙያነት ያስረዳሉ::

ታሪክ የልማዶች፣ የህገረሰብ እምነቶች፣ የባህላዊ ድርጊቶች፣ ሁነቶች እና/ወይም ታሪኮች ሥብስብ ነው:: የሰው ልጅ በኑሮው ሂደት ለራሱ የሚስማማ ህግ ያወጣል፤ ደንቦችን ይደነግጋል:: ለፍርሃቱ መላቀቂያም አማልክቱን ይፈጥራል:: እነዚህ ሁሉ የዚያ ማህበረሰብ ማህበራዊ ታሪኮች ናቸው:: Mayoም ይህን ሃቅ በመያዝ፣ ፎክሎር የቃላዊና የጽሁፋ መዝገብ ሆኖ ወደታሪክ እንደሚለወጥ ጽፈዋል:: “History is a record-oral and written of human actions expressed in series of events, attitudes, values, customs, and views of communities” (1984:12).ታሪክ የሰው ልጅ ተከታታይ ተግባሮች፣ አመለካከቶች፣ ዕሴቶች፣ ማህበራዊ ዕይታ፣ እምነት በተመለከተ የቃልም ሆነ የፅሁፍ ስብስብ ነው::

ሌላው ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ፎክሎር የታሪክ መሠረት ነው? ወይስ ታሪክ የፎክሎር መሠረት ነው? የሚለው ነው:: ይህ ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ የለውም:: እንዲያውም ሲበዛ አከራካሪ ነው:: ለምሳሌ ያህል ታደሰ «የመጀመሪያዎቹ የታሪክ ፀሀፊዎች ትውፊት ሰብሳቢዎች ነበሩ:: የመጀመሪያውም የታሪክ አይነት አፋዊ ታሪክ ነበር» (1973:3) በማለት ከታሪክ በፊት ፎክሎር እንደነበር ጠቁመዋል:: ታሪክ ከመጻፉ በፊት የማህበረሰቦች ተለምዶአዊ ህይወት ነበር:: ያ ልማድ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ሲተላለፍ ኖሯል:: በኋላም በታሪክ ምሁራን ቃላዊ ፎክሎሩ ተለቅሞ ወደ ጽሀፈት ተለውጧል:: Spinosa ደግሞ ፎክሎርን “One of the social sciences that studies and interprets the history of civilization”(In leach ,1950:399) ፎክሎር የማህበራዊ ሳይንስ አንዱ ዘርፍ ነው:: የሚያጠናውና የሚተረጉመውም የሥልጣኔን ታሪክ ነው በማለት

ፎክሎር ከታሪክ አይታ፣ ታሪክም ከፎክሎር ክበብ ውጭ ከመውጣት ፋንታ፣ እርስበርሳቸው የሚደጋገፉ ሙያዎች መሆናቸውን አስረድተዋል::

ታሪክና ፎክሎር በጊዜ ገደብም ቢሆን ተደጋጋፊነት አላቸው:: ብዙውን ጊዜ ፎክሎር የቆየ፣ የጥንት፣ የኋላቀሮች ልማድ ብቻ እንደሆነ፣ ቢነገርም፣ በአንፃሩ የፎክሎር ትምህርት ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር እያደገና እየተለወጠ የሚመጣ ነው:: Christiansen ይህን ሃሳብ ሲያብራሩ፤

*Folklore, however, is not an already completed corpus, composed of survivals and remains; it is a living force developed and formed, with and changing characteristics in each country according to its history and culture (1962, 11).*

*ፎክሎር ያለቀለት፣የሞተ፣ የተቀበረ፣የቅሪትና የርዝራዥ ስብስብ ማለት አይደለም:: ፎክሎር ህያው ነው:: የያንዳንዱን አገር ታሪኩን መሠረት አድርጎ የሚያድግ ነው:: ማለትም በማህበረሰቡ ታሪክና ባህል አይነት ይገለፃል::*

ታሪክም ያለፈ፣ የቆየ፣ የድሮ ማለት አይደለም:: እንደዚሁም፣ ፎክሎር የነተበ፣ ከሞት የተረፈ እና ዝቃጭ ማለት አይደለም:: የሚያድግና የሚለወጥ፣ በማደጉና በመለወጡ ደግሞ አንዳች ፋይዳ የሚያመጣ ነው:: በአንድ ቡድን፣ ጎሳ፣ ማህበረሰብ ወይም አገር ውስጥ ባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የዕድገት ደረጃ ልክ የሚለካ ነው:: ሌላው ፎክሎርንና ታሪክን የሚያመሳስላቸው ነጥብ ሁለቱም መላምታዊ መሆናቸው ነው:: በሁለቱም ውስጥ ያሉ ታሪኮች ከተወሰኑ ገለጻዎችና ድርጊቶች በቀር፣ በምክንያትና ውጤት የተሳሰሩ አይደሉም:: በፎክሎር ውስጥ፣ ሀገረሰባዊ እምነቶች፣ ቃላዊ ሃተታዎች (ሃተታ ተፈጥሮ፣ አፈ-ታሪክ፣ እንስሴተረት) እና ግብታዊ ድርጊቶች (ድግምት፣ ዛር፣ መሃላ፣ ወዘተ) መቼም ቢሆን ማረጋገጫ ሊሰጥባቸው የሚችሉ አይደሉም::

ታሪክም፣ እንደፎክሎሩ አይብዛ እንጂ በግምታዊ ድርጊቶች፣ ሁነቶችና ቃላዊ ትረካዎች የተሞላ ነው:: Oman "History is not a tale of logical processes of necessary evolutions, but a series of happenings like popular slogans and beliefs" (1969:9) ታሪክ የአይቀሬ ለውጦች ምክኒያታዊ ቅደም ተከተል ትረካ አይደለም እንደ ህዝባዊ ዕምነቶችን ያሉት ተከታታይ ክስተቶች እንጂ ቀጥሎም "History is full of 'might-have-beens"(9) ታሪክ በምናልባቶች የተሞላ ነው:: በማለት ነገሩን ይበልጥ አስረግጠው አቅርበውታል::

በአጠቃላይ፣ የታሪክ ፀሀፊዎች ታሪክ ሲጽፉ፣ ከላይ የተገለፀውን የፎክሎርና የታሪክ ዝምድናን ይዘው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ የአንድ ንጉሥን ታሪክ የሚጽፍ ምሁር፣ ስለንግሥና ስርዓቱ፣ በንግሥናው ላይ ስለተደረገው ክዋኔ፣ ስለተለበሰው ልብስ፣ ስለ ደስታውና ህዝቡ ደስታውን ለመግለጽ ስላደረገው ክበራ፣ በጥቅሉ በንግሥና ስርዓቱ ወቅት ስለሚኖረው ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴት መጻፉ አይቀርም፡፡ ይህ ማለት ሰሚውን ወይም ታዳሚውን ለማሳመን ሲባል፣ ንጉሡ የሚደረገውን ንጉሡ የሚናገረውን ባህላዊ ንግግርም ሆነ የሚያደርገውን ተለምዷዊ ስርዓት በመያዝ ሲጽፍ፣ መሠረቱ ወይም መነሻው ፎክሎር መሆኑን ማወቅ ይገባል፡፡ በመሆኑም፣ በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ፎክሎራዊ ጥሬ እቃዎች የመገኘታቸው ምስጢር፣ ይሄው የሁለቱ ሙያዎች ዝምድና ነው፡፡ ፎክሎርና ታሪክ ትስስራቸው ከሞላ ጎደል ይሄን ቢመስልም የሚለያዩበትም ሁኔታ እንዳለ መግለፅ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ሁለቱም የሰውን ልጅ የሕይወት ልምድ መሠረት አድርገው የሚነሱ ቢሆኑም ይዘውት የሚጓዙት እውነታ ከሙያዎቹ ግላዊ ባሕሪ የተነሳ ይለያያል፡፡ የፎክሎር የተለዋዋጭነት ባሕሪ ከታሪክ ለመለየቱ ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡

ይህን በተመለከተ Campa ሲያስረዱ:-

> *The facts of history, are not supposed to change once they are established. On the other hand, the facts of folklore change every time a different person retells a story or sings a ballad (1965:2). የታሪክ እውነታዎች አንዴ ከተረጋገጡ(ከተዋቀሩ) እንዲለወጡ አይጠበቅም፡፡ በአንፃሩ የፎክሎር እውነታዎች በየጊዜው ይለዋወጣሉ፡፡ የተለየ ሠው እንደገና ትረካውን ባቀረበው ወይም ባህላዊውን ዘፈን በዘፈነው ቁጥር ይለወጣሉ፡፡*

በርግጥ አንዳንድ የፎክሎር ሰብሳቢዎች ወይም አጥኚዎች ያልተለወጠውን ፎክሎር ለማሰባሰብ ይሞክራሉ፡፡ ግን አይሳካላቸውም፡፡ ምክንያቱም ፎክሎር ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ በቅርፅም በይዘትም የመጨመር፣ የመቀነስ ፣የመሞት እድሉ የሰፋ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለሁለቱ ሙያዎች መለያየት ተጨማሪ ምክንያት የሚሆነው ሁለቱም መስኮች የያዙትን እውነታ የሚያቀርቡበት መንገድ ነው፡፡ የታሪክ ፀሀፊው ያገኘውን መረጃ በተቻለ መጠን ሳያዛባ፣ ሳያጋንን እንዳለ ማቅረብ ሲጠበቅበት በአንፃሩ ፎክሎር በሚቀርብበት ጊዜ ተራኪው የራሱን የፈጠራ ክህሎት ተጠቅሞና አውዱን ተከትሎ በሚመቸው መንገድ አንዴ እያሞካሸ አንዴ እያጎደፈ ያቀርባል፡፡

### 2.4.2 ፎክሎር በታሪክ ምንጭነት

ታሪክ የምርምር ተግባር እንደመሆኑ መጠን፣ ፀሐፊው ለድርሰቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የሚሰበስብበት የራሱ የሆነ ሳይንሳዊ ዘዴ አለው፡፡ የታሪክ ፀሐፊ መረጃውን ከቀዳማይ እና ከ ካልዓይ ምንጮች ይሰበስባል፡፡ ስለ መረጃ ምንጮቹ ምንነት Marwick ሲያስረዱ:-

*Primary sources are sources which come into existence during the actual period of the past which the historian is studying, they are those relics and traces left by the past, while secondary sources are those accounts written later by historians looking back upon a period in the past (1989,199).*

*ቀዳማይ ምንጮች የታሪክ ባለሙያው በሚያጠናበት ያለፈ ዘመን የነበሩ እና ታሪክ ተመራማሪው የሚያጠናቸው ሲሆኑ ካልዓይ ምንጮች ግን ታሪክ ፀሀፊው ቀደም ባሉ ዘመናት የተፈፀሙ ድርጊቶችን የሚያወሱ ፅሁፎችን መሰረት አድርጎ የሚፅፈው ነው፡፡*

ሁለቱም የመረጃ ምንጭ አይነቶች ለታሪክ ፀሐፊው የሚያስፈልጉ ቢሆኑም በተናጠል ግን ህልውና የላቸውም፡፡ ማለትም በቀዳማይ ወይንም በካልዓይ ምንጮች ብቻ ታሪክ አይፃፍም፡፡ ሁለቱንም ምንጮች በጋራ መጠቀም የግድ ነው፡፡ ይህንን Marwick "Study of primary sources alone does not make history; but without the study of primary sources there is no history" (1989:199) በማለት ቀዳማይ ምንጭ ለታሪክ ፀሐፊው የግዴታ አስፈላጊ መሆኑንና ለብቻው ግን በቂ አለመሆኑን ፀሀፊው በአፅዕኖት ያስረዳሉ፡፡

በቀዳማይ ምንጭነት ከሚጠቀሱት መረጃዎች አንዱ ፎክሎር ነው፡፡ ፎክሎር በራሱ ታሪካዊ ክስተት የመሆን አጋጣሚ ቢኖረውም ለታሪክ ፀሀፊያን መሠረታዊ የሆነ መረጃን በማቀበል ያገለግላል (Georges and Jones ; 1995:84)፡፡ አሮጌ ሕንፃዎችና ፍርስራሾች፣ ሐውልቶች፣ ጥንታዊ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች፣ ልዩ ልዩ ጥንታዊ አልባሳት፣ የጦር መሣሪያዎች፣ ህገረሰባዊ አባባሎች ፣ ህገረሰባዊ ዘፈኖች፣ ቀልዶች፣ ትውፊቶች የመሳሰሉት የፎክሎር አይነቶች ለታሪክ ፀሀፊው ሥለአለፈው ዘመን መረጃ በመስጠት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ Levineም እንዲህ ይላሉ:-

*The historical use of folklore help us to gain some sense of people's angle of vision, to better understand the inner dynamics of a group and the attitudes of its members, and to comprehend their sense of worth(1983:340).*

*ፎክሎር ለታሪክ ያለው ጥቅም ሥለሰዎች የአመለካከት አቅጣጫ በመጠኑም ቢሆን እንድናውቅ፤ ሥለአንድ ቡድን ውስጣዊ ባህሪና ሥለአባላቱ አእምሮአዊ ዝንባሌ የበለጠ እንድንገነዘብና፤የነሱንም ፋይዳ እንድንረዳ ያግዘናል።*

አንድ ማህበረሰብ ማግኘትና ማጣቱን፤ ደስታና ሀዘኑን፤ ጥላቻና ፍቅሩን፣ ቁጣውን፣ ሙገሳውን፣ ባጠቃላይ ስሜቱን ቃላዊ በሆነ ባህሉ ከትውልድ ትውልድ ሲያስተላልፍ ኖሯል። እናም ይሄ ቃላዊ ባህል የሰዎችን አመለካከት፣ ፍልስፍና የመሳሰሉትን ለታሪክ ፀሀፊው በማቀበል ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው።"Without oral traditions we would know very little about the past of large parts of the world,and we would not know them from the inside" (Vansina:1989 :197) ካለ ቃላዊ ባህል (ፎክሎር) የዓለምን ሰፊ ክፍል ያለፈ ሁነት የምናውቀው በጣም በጥቂቱ ነው። እንዲሁም ከውሥጥ (ከሥር) ጀምሮ ልናውቅ አንችልም በማለት Vansina ፎክሎር ለታሪክ ምርመር ያለውን ፋይዳ አስረድተዋል። ታደሰም በበኩላቸው:-

*እንደ ኅብረተሰቡ የእድገት ደረጃ ፤ለማንኛውም ሕዝብ ህልውናና ማንነት ስለ ውስጣዊ አንድነቱና ከአጎራባች ሕዝቦችም ጋር ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ለሚኖረው ግንዛቤ ሁሉ መነሻ የሚሆን በዚህ ከጥንት አባቶች በሚተላለፈው ተረትና ትውፊት በኩል የሚገኘው ባህላዊ ትምህርት ነው ( 1984 ፣71)።*

በማለት ፎክሎር ለታሪክ ቀዳሚ የመረጃ ምንጭነት በመሆን ማገልገሉን ይገልፃሉ። በእርግጥ ፎክሎር ለታሪክ ፀሐፊዎች በታሪክ ምንጭነት ያገለግላል ሲባል ሙሉ በሙሉ እምነት የሚጣልበት መረጃ ነው ማለት አይደለም። ምክንያቱም ፎክሎር በባህሪው ተለዋዋጭ እና ህዝባዊ በመሆኑ ስለአንድ ንጉሥ ስለአንድ ህዝብ ወይም ስለአንድ ክስተት የተነገረውን አምኖ መቀበል ሥህተት ላይ ሊጥል ይችላል። ስለዚህ "That folklore can and should be examined along with available written documents by those attempting to reconstruct history" (Georges and Jones;1995:84) ታሪክን ለማዋቀር የሚሞክር ሰው ፎክሎርን ከፅሁፍ መረጃዎች ጋር ማመሳከር መቻል አለበት በማለት ይመክራሉ።

### 2.4.3 ፎክሎር ለታሪክ አፃፃፍ ያለው ጠቀሜታ

ታሪክ ፀሀፊ ለመረጃው እውነታነት እንደሚጨነቀው ሁሉ ለአፃፃፍ ዘዴውም መጠንቀቅ ይኖርበታል። ታሪኩ ተነባቢ እና አስተማሪ እንዲሁም አይረሴ እንዲሆን የአፃፃፍ ዘዴው ወሳኝነት አለው። ደረቅ እውነታን በደረቅ ቋንቋ የሚያቀርብ የታሪክ ፀሀፊ በደካማነቱ ይጠቀሳል፤ ልፋቱም ከንቱ ሆኖ ይቀራል። "In fact, the historian who writes uninterestingly is to that extent a bad historian" (Gottschalk, 1954: 14). በርግጥ ታሪክን በሚስብ ሁኔታ የማይፅፍ የታሪክ ፀሀፊ በዚያው ልክ ደካማ የታሪክ ፀሀፊ ነው። ስለሆነም ታሪክ ፀሀፊ በድርሰቱ አንባቢውን ቀጥሎ ምን ሆነ፣ ምን ይፈጠር ይሆን በሚል ልብ አንጠልጣይ ስሜት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ይዞ ለመጓዝ ለአፃፃፍ ዘዴውና ለቋንቋ አጠቃቀሙ ትኩረት ሊሰጥ ይገባዋል።

ታሪክ በሦስት ዘዴ ሊፃፍ እንደሚችል Marwick ያስረዳሉ:-

> *Good historical writing should present a balance between narrative and analysis, between a chronological approach and an approach by topic, and it should be added, a balance between both of these, and as necessary, passages of pure description (setting the scene', providing routine but essential information, conveying the texture of life in any particular age and environment (1989:242)* .

> *ጥሩ የታሪክ አፃፃፍ የድርጊቶቹን የጊዜ ቅደም ተከተል በመጠበቅና ርዕሰ ጉዳዩን በርዕስ በርዕስ በመከፋፈል የትረካ እና የትንተና ዘዴን አመጣጥኖ በመጠቀም ታሪኩን መፃፍ አለበት። በተጨማሪም ገለፃው ታሪኩ ስለ ተፈፀመበት ጊዜና ቦታ (መቼት) የሚያወሱት መሰረታዊ መረጃዎች፣ በእያንዳንዱ ዘመን እና አካባቢ የተፈፀሙ የህይወት ገፅታዎችን በሚያሳይ መልኩ መሆን ይኖርባቸዋል።*

ትረካው፣ ትንተናውም ሆነ ገለፃው ለብቻው የሚፈይደው ነገር የለም። የፀሐፊውን ምናባዊነት ይጠይቃሉ። ፀሀፊው በታሪኩ ውስጥ የሚፈፀሙ ድርጊቶችን፣ የድርጊቱን መፈፀሚያ ጊዜና ስፍራ፣ መልዕክቱን፣ ባለታሪኮቹን እና የመሣሠሉትን ዕውነታዎች ምናባዊ ፈጠራውን በማከል፣ ግዝፈት እንዲኖራቸው በማድረግ ትረካው የሚደመጥ፤ ገለፃው የሚታይ በአጠቃላይ ታሪኩ በአንባቢ ህሊና ውስጥ ቦታ እንዲያገኝ አድርጎ ማቅረብ ይኖርበታል። የተዋጣለት የታሪክ ፀሀፊ ትረካው ተፅዕኖ የሚያሳድርና ምስል ከሳች

እንዲሆንለት የምናባዊ ፈጠራ ባለቤት መሆን አለበት፡፡ ታሪክ እንደ ወረደ የሚፃፍ ሳይሆን ዕውነታው በፀሀፊው ምናባዊነት ታግዞ ለአንባቢ የሚስብ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ "...the historian as artist, captivating the reader with the brilliance of his rhetoric. His mastery of metaphor and paradox" (Marwick ,1989 :246).

ሌላው የታሪክ ፀሀፊው ሊያስብበት የሚገባው ጉዳይ የቋንቋ አጠቃቀሙን ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ድርሰቱ ግቡን እንዲመታ ቋንቋው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ቋንቋው ለማንኛውም አንባቢ በሚገባ መልኩ መቅረብ አለበት፤ የረቀቀና የሚያሻማ መሆን የለበትም፡፡ በአጠቃላይ ቀላልና ግልፅ መሆን እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገሮች፣ አባባሎች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች(የተለያዩ የፎክሎር ቅርፆች) ወዘተ... በመጠቀም ትረካው ፍሰቱን ጠብቆ እንዲሄድ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህን መሰሉ የቋንቋ አጠቃቀምም ሥነፅሁፍና የታሪክ ድርሰት የጋራ ባህሪ እንዳላቸው ያሳያል፡፡

> *The historian, like the poet and novelist, is aware of the metaphoric resources of language, and he draws up on them for both meaning and strength, as the scientist and the social scientist may not (Nye,1966:139).*
>
> *ታሪክ ፀሐፊው፤ሳይንቲስትና ማሕበራዊ ሳይንቲስት የማይጠቀሙበትን የቋንቋ አጠቃቀም፣ ልክ እንደ ገጣሚ (ባለቅኔ) እና የልቦለድ ፀሐፊ ለነገሮች ፍቺ ለመስጠትና ለማጠናከር ሲል በቋንቋ ውስጥ ስላሉ ዘይቤያዊ አገላለፆች ግንዛቤ አለው፡፡*

በማለት Nye የሚያስረዱት የታሪክ ፀሀፊ ከሥነፅሁፍ ባለሙያ ባልተናነሰ፣ በቋንቋው መግለፅ፤ የአንባቢን ትኩረት መሳብና ማስተማር የሚችል መሆን እንዳለበት ነው፡፡

ከቋንቋ አጠቃቀሙ ጋር በተያያዘ ለትረካው ፍሰት፤ እንዳይሰለች እና ውበት እንዲኖረው ለማድረግ ፀሀፊው የሚጠቀመው ሌላ ዘዴ አለ፡፡ ይኸውም የተለያዩ የሥነ ቃል ቅርፆችን በመጠቀም ትረካውን ያስኬዳል፡፡ አንዲት ወይም አንድ አዝማሪ እንዲህ አዘመረች/አዘመረ አንዲት አልቃሽ እንዲህ አስለቀሰች/አስለቀሰ በማለት የቃል ግጥሞችን እንዲሁም ተረቶች፣ ቀልዶች እና የመሳሰሉትን የሥነ ቃል አይነቶች በዝርው ትረካው መሀል በማስገባት ሀሳቡን ያጎላል አሊያም ይቋጫል፡፡ እግረ መንገዱንም ለአንባቢ ተዝናኖት ይፈጥራል፤ ያሳርፋልም፡፡ «የቃል-ታሪክ መረጃዎች (ቀረርቶ፣ ዘፈን ፣ ሙሾ ወዘተ) በባህላዊ የታሪክ አፃፃፍና አቀራረብ መሠረት በተዘጋጁት ዜና መዋዕሎች ውስጥ የጭብጥ ማሟያና ማጠናከሪያ እየሆኑ ገብተው ይገኛሉ» በማለት ክነፈ-ርግብ (1973፣ 5) አስረድተዋል፡፡

Nye "History and Literature: Branches of the Same Tree" (1966, 123). ታሪክና ሥነ ፅሁፍ የአንድ ዛፍ ቅርንጫፎች ናቸው በማለት ታሪክና ሥነፅሁፍ የጋራ መሠረት እንዳላቸው ይገልፃሉ:: ሁለቱም መነሻቸው የሰው ልጅ የህይወት ልምድ ነው:: በርግጥ ይህን የሰውን ልጅ የህይወት ልምድ የሚያቀርቡበት መንገድ የተለያየ ቢሆንም የሚዋቀሩበት አላባውያን ተመሣሣይነት አላቸው:: የሥነ ፅሁፍ አላባውያን የሚባሉት ገፀ ባህሪ፣ መቼት፣ ግጭት፣ ጭብጥ፣ ሴራ፣ ታሪክ፣ አንፃር በታሪክ ድርሰትም ውስጥ ይገኛ ሉ:: ይኸውም ታሪኩ የሚፈፀምበት ጊዜና ቦታ፣ ባለ ታሪኩ፣ የታሪኩ መልዕክት፣ ባለታሪኮቹ የሚገቡበት ግጭት (ምክንያትና ውጤት) የመሳሰሉት የታሪክ አላባውያን ናቸው:: ፎክሎር በሥነፅሁፍ ውስጥ እነዚህን አላባውያን ለማሳየት፣ ለማጉላት እንደሚገባ እና የራሱ ፋይዳ እንዳለው ሁሉ በታሪክ ድርሰቶች ውስጥም ተመሳሳይ ተግባር አለው:: ለምሳሌ የአፄ ቴዎድሮስን ሰብዕና ለማሳየትና ለሽፍትነታቸው አንድ መንስኤ በመሆን ኮሶ የመጠጣት ባህላዊ ድርጊት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉ ተገልፃል (ተክለ ፃድቅ፣ 1981፣ 75-79):: ይህን በተመለከተ በምዕራፍ ሦስት በንዑስ ክፍል 3.2.2 መመልከት ይቻላል:: ይሄና ይሄን መሰል ፎክሎራዊ ጉዳዮች በታሪክ ድርሰት ውስጥ ጭብጥ በማጉላት፣ የባለታሪኩን ውስጣዊና ውጫዊ ማንነት በማሳየት፣ ሰበበ ግጭት በመሆን እንዲሁም ለግጭት መፍትሔ በማምጣት እና ታሪኩ የሚፈፀምበትን ጊዜና ቦታ በማሳየት ረገድ እና ለመሳሰሉት ተግባራት ከፍተኛ ሚና አላቸው::

በርግጥ ይህንን ሚና የሚጫወቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የታሪክ ፀሐፊው እንደ ሥነፅሁፍ ደራሲ ከምናቡ አፍልቆ የሚፈጥራቸው ብቻ ሳይሆኑ ክስተቶችም ናቸው:: ድርጊቶቹ ከድርጊትነታቸውም በላይ የራሳቸው ፋይዳ አላቸው:: ይሄንን ነው ፎክሎር የሚያጠናው:: ለምሳሌ ንግር፣ ምልኪ፣ ግዝት የመሳሰሉ ሀገረሰባዊ ልማዶች ታሪክ ፀሐፊው እንደ አንድ ክስተት ቢፅፋቸውም የራሳቸው የሆነ ፎክሎራዊ ፋይዳ አላቸው:: ምናልባትም ለአንድ ንጉሥ መንገሥም ሆነ መሻር መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ:: በመሆኑም በታሪክ ውስጥ የምናገኛ ቸው እነዚህን መሰል ድርጊቶችም ሆኑ አመለካከቶች በታሪክ ፅሑፉ ላይ ጉልህ ሚና አላቸው::

## 3. የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በተመረጡት የታሪክ መፃሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ በሚገኙ የፎክሎር ቅርፆች እና ፋይዳቸው ላይ ትንተና ተሰጥቷል:: ምዕራፉ ሁለት ንዑሳን ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ፎክሎርን ከቅርፅ አንፃር የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ፎክሎር በመፃሕፍቱ ውስጥ ያለውን ፋይዳ የሚተነትን ነው::

### 3.1 የፎክሎር ቅርፅ

Dorson ፎክሎርን (በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው) በአራት ዓበይት ምድቦች (ቅርፆች) ይከፍሏቸዋል:: ይህ ጥናትም የDorsonን ምደባ ተግባራዊ በማድረግ በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ የሚገኙትን የፎክሎር ቅርፆች በአራት መድቦ ይተነትናል:: እነሱም ቃላዊ ፎክሎር (ሥነ ቃል)፣ ህገረሰባዊ ልማድ፣ ቁሳዊ ባህል እና ትውን ጥበባት ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ደግሞ የየራሳቸው ንዑሳን ክፍሎች አሏቸው አራቱም ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል::

#### 3.1.1 ሥነ ቃል

ሥነ ቃል በታሪክ መፃሕፍቱና በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ በተለያየ ቅርፅ ይገኛል:: ተረት፣ አፈታሪክ፣ ቀልድ፣ ቃል ግጥም፣ እንቆቅልሽ (ህ)፣ ስድብ፣ እርግማን መሃላ፣ ምሳሌያዊ ንግግር፣ ሽሙጥ፣ ቀረርቶ፣ ፉከራ፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: እነዚህን ከብዛታቸው በመነሳት እንዲሁም ያላቸውን ተቀራራቢ ቅርፅ ግምት ውስጥ በማስገባት፤ ቃል ግጥም፣ ዝርው ትረካ እና አጫጭር የሥነቃል አይነቶች በማለት በሶስት ከፍያቸዋለሁ::

##### 3.1.1.1 ቃልግጥም

በታሪክ መፃሕፍቱም ሆነ በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ የሚገኘው ማህበረሰብ ክፉውን ለመንቀፍ፣ ደጉን ለማሞገስ፣ ምኞትና ተስፋውን ለመግለፅና ለመሣሡት ተግባራት ቃል ግጥሞችን ተጠቅሟል:: በተለይ የታሪክ መፃሕፍቱ እነዚህን ቃልግጥሞች በስፋት ይዘዋል:: ቃልግጥሞቹ ከመንቶ /ባለ ሁለት መስመር ግጥም/ ጀምሮ እስከ ሃያ ሁለት የስንኝ መስመር የሚደርሱትን ያጠቃልላሉ:: በአምስቱ የታሪክ መፃሕፍትና በሁለቱ ዜና መዋዕሎች ውስጥ የሚገኙትን ቃልግጥሞች ዓይነትና ብዛት በግልፅ ለማሳየት ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ቀርበዋል::

ሰንጠረዥ.1 <u>ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት</u>

| ተ.ቁ. | ገጽ | የቃል ግጥሙ አይነት | የስንኝ ብዛት | የተነገረበት ዐውድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 36 | ሙገሳ | 5 | እቴጌ ምንትዋብ ሲነግሱ |
| 2 | 39 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 4 | ንጉሥ ኢያሱ ሲሞቱ የእቴጌ ምንትዋብ ለቅሶ |
| 3 | 56 | ተቃውሞ | 4 | የጎበናን ጨካኝነት ለመግለፅ |
| 4 | 107 | ጀግንነት | 2 | ደጃች ክንፉ ከግብፅ ጦር ጋር ተዋግተው ማሸነፋቸው |
| 5 | 126 | ስድብ | 7 | ካሣን በመናቅ የተገጠመ |
| 6 | 127 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | የደጃች ጎሹን ሽንፈትና ሞት በተመለከተ |
| 7 | 127 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 3 | ካሣን የሰደበው አዝማሪ በራሱ ላይ ሞት ሲፈርድ |
| 8 | 141 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ደጃች ውቤ በዐፄ ቴዎድሮስ ታስረው ሳሉ ሀዘናቸውን ሲገልፁ |
| 9 | 142 | ሙገሳ | 10 | ዐፄ ቴዎድሮስ ሲነግሡ |
| 10 | 171 | ሙገሳ | 2 | ዐፄ ቴዎድሮስ ሸዋ ሲገቡ |
| 11 | 171 | ተቃውሞ | 2 | ምኒልክ ለዐፄ ቴዎድሮስ ተላልፈው ሲሰጡ |
| 12 | 176 | ላጣ | 2 | የንጉሥ ኃይለ መለኮት እናት ሹመት በመጠየቃቸው |
| 13 | 185 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ዐፄ ቴዎድሮስ ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ሲሞቱ የገጠሙት |
| 14 | 185 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ራስ ዐሊ ልጃቸው ተዋበች ስትሞት የገጠሙት |
| 15 | 186 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 5 | የራስ ዐሊ ሀዘን መግለጫ |
| 16 | 197 | ምፀት | 2 | ዐፄ ቴዎድሮስ የሸዋን ሰው እጅና እግሩን በመቁረጣቸው |
| 17 | 198 | ተቃውሞ | 2 | ዐፄ ቴዎድሮስ በሃይማኖት የተነሳ ብዙ ሰው በመፍጀታቸው |
| 18 | 198 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | አቤቶ ሰይፉ ሲሞቱ |
| 19 | 214 | ፉከራ | 3 | ዐፄ ቴዎድሮስ ወረሂመኑዎችን ለመግዛት ሲዘምቱ |
| 20 | 220 | ሙገሳ | 2 | ዐፄ ቴዎድሮስ ጋረድን አሸንፈው በድል ሲገቡ |
| 21 | 220 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 3 | ጋረድ በመሞቱ ወንድሞቹ ብቻቸውን መቅረታቸውን ለመግለፅ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 22 | 220 | ሙገሳ | 5 | የጎንደር ሊቃውንት የቴዎድሮስን መንገሥ በማድነቅ |
| 23 | 233 | ፉከራ | 11 | ሳህሉ ተሰማ የሚባል ጀግና በቴዎድሮስ ላይ ለመዝመት ሲቀሰቅስ |
| 24 | 245 | ተቃውሞ | 2 | በዐፄ ቴዎድሮስ የቅጣት ርምጃ መከፋት የተነሳ |
| 25 | 246 | ተቃውሞ | 2 | የአዲት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በዐፄ ቴዎድሮስ መቃጠሉን አስመልክቶ |
| 26 | 246 | ተቃውሞ | 4 | የኑሮ ውድነትን አስመልክቶ |
| 27 | 247 | ተቃውሞ | 5 | ረሃብን በተመለከተ |
| 28 | 248 | ተቃውሞ | 2 | የዐፄ ቴዎድሮስን አስፈሪነት አስመልክቶ |
| 29 | 261 | ፉከራ | 2 | መኳንንቱ በንጉሡ ፊት ገዳይነታቸውን ሲገልፁ |
| 30 | 267 | ሙገሳ | 2 | ቴዎድሮስ መምህር አካለ ወልድን ሲያደንቁ |
| 31 | 269 | ሙገሳ | 4 | ንጉሡ ወደ ኢየሩሳሌም የሚያደርጉትን ጉዞ አስመልክቶ |
| 32 | 270 | ሙገሳ | 4 | የኢየሩሳሌምን ጉዞ በተመለከተ |
| 33 | 367 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ደጃች ውቤ በመሞታቸው |
| 34 | 367 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | በደጃዝማች ውቤ ሞት ምክንያት ሰው ሁሉ ለሟች ዘመዱ በማልቀሱ የተገጠመ |
| 35 | 367 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 7 | ደጃች ተድላ ጓሉ ሲሞቱ የተገጠመ |
| 36 | 439 | ጀግንነት | 2 | ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት |
| 37 | 439 | ጀግንነት | 2 | ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ አሟሟት |
| 38 | 439 | ጀግንነት | 2 | ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ አሟሟት |
| 39 | 439 | ጀግንነት | 2 | ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት |
| 40 | 439 | ጀግንነት | 2 | ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት |
| 41 | 439 | ጀግንነት | 2 | ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ አሟሟት |
| 42 | 439 | ጀግንነት | 4 | የእንግሊዞችን ሽንፈት በተመለከተ |
| 43 | 439 | ጀግንነት | 4 | ዐፄ ቴዎድሮስን በሥጋት ይመለከቷቸው ከነበሩ የተሠነዘረ |
| 44 | 440 | ሙገሳ | 2 | ዐፄ ቴዎድሮስ ለመግዛት ያላቸውን ፍላጎት ለመግለፅ |
| 45 | 440 | ተቃውሞ | 3 | የዐፄ ቴዎድሮስን አስፈሪነት ለመግለፅ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 46 | 440 | ተቃውሞ | 4 | የዐፄ ቴዎድሮስን ጨካኝነት ለመግለፅ |
| 47 | 442 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ዐፄ ቴዎድሮስ ቀብር ላይ የተገጠመ |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው 47 ቃል ግጥሞች በመፅሐፉ ውስጥ ይገኛሉ:: በይዘታቸውም ተቃውሞን ፣ ሙገሳን ፣ ሀዘንንና ጀግንነትን የሚገልፁ ናቸው:: ከነዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ተቃውሞ 13 እና የሀዘን እንጉርጉሮ 12 ሲሆኑ የዐፄ ቴዎድሮስን ሥርዓት የሚቃወሙ እና ንጉሡ በፈፀሙት በደል ህዝቡና መኳንንቱ ሀዘናቸውን የገለፁበት ነው:: ስለ ጀግንነታቸው የሚገልፁ ዘጠኝ ቃል ግጥሞች በመፀሐፉ ውስጥ ይገኛሉ::

**ሰንጠረዥ.2 <u>ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት</u>**

| ተ.ቁ | ገጽ | የቃል ግጥሙ አይነት | የስንኙ ብዛት | የተነገረበት ዐውድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 27 | ፉከራ | 2 | ካሳ እና ተክለ ጊዮርጊስ ለጦርነት ሲዘጋጁ |
| 2 | 29 | ሙገሳ | 6 | ራስ አሉላ ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስን በመማረካቸው |
| 3 | 73 | ፉከራ | 5 | አቶ በዛብህንና ምኒልክን የበለጠ ለማጣላት |
| 4 | 75 | ሙገሳ | 2 | አቶ በዛብህ ሲገደሉ በመርካት |
| 5 | 75 | ተቃውሞ | 4 | የአቶ በዛብህ አገር ለአንካሳ ሰው በመስጠቱ የተገጠመ |
| 6 | 151 | ሙገሳ | 5 | የዐፄ ዮሐንስን ጀግንነት ለማውሳት |
| 7 | 180 | ተቃውሞ | 2 | ምኒልክ ለዮሐንስ መገዛቱን ባለመቀበል |
| 8 | 180 | ተቃውሞ | 2 | ምኒልክ እንዴት ንጉሥ ብቻ ይሆናሉ በማለት |
| 9 | 200 | ተቃውሞ | 2 | እስላሙ ሁሉ በግድ ክርስቲያን ሲሆን የተገጠመ |
| 10 | 204 | ሙገሳ | 2 | ራስ ጎበና ራስ ደረሶ ሰብስበው ያስቀመጡትን የዝሆን ጥርስ በመማረካቸው |
| 11 | 204 | ሙገሳ | 2 | የራስ ጎበና እና የራስ ደረሶን ጦርነት በማንሳት |
| 12 | 294 | ሙገሳ | 2 | ምኒልክ ከሐረር ወደ እንጦጦ ሲመጡ በምርኮ ውሻና እርግብ ይዘው በመምጣታቸው |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 13 | 390 | ጀግንነት | 4 | አሉላ ጣሊያኖችን ድል በማድረጋቸው |
| 14 | 390 | ጀግንነት | 4 | ጣሊያን በአሉላ የደረሰበትን ሽንፈት የሚገልፅ |
| 15 | 390 | ጀግንነት | 3 | የአሉላን ጀግንነት ለመግለፅ |
| 16 | 390 | ጀግንነት | 2 | የአሉላን ጀግንነት ለመግለፅ |
| 17 | 390 | ጀግንነት | 3 | የአሉላን ጀግንነት ለመግለፅ |
| 18 | 390 | ሙገሳ | 5 | ኢትዮጵያ የማትደፈር ሀገር መሆኗን የሚገልፅ |
| 19 | 449 | ሙገሳ | 2 | ንጉስ ተክለሃይማኖት ከደርቡሾች ጋር ሲዋጉ ሲሄዱ |
| 20 | 451 | ተቃውሞ | 4 | ምንትዋብ በደርቡሾች በመማረካዋ |
| 21 | 451 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ምንትዋብ በደርቡሾች ተማርካ ስትወሰድና ስትሞት |
| 22 | 463 | ተቃውሞ | 2 | ምኒልክ ለዐፄ ዮሐንስ መገበር የለበትም በሚል |
| 23 | 505 | ተቃውም | 4 | ንጉሡ በጎጃም ላይ የፈፀሙትን ጥቃት በተመለከተ |
| 24 | 529 | ተቃውሞ | 2 | ንጉሡ ከመተማ በሰላም እንደማይመለሱ ለመግለፅ |
| 25 | 530 | ገከራ | 2 | ንጉሡ ወደ መተማ ሲዘምቱ |
| 26 | 548 | ሙገሳ | 12 | የዐፄ ዮሐንስን አሟሟት አስመልክቶ |

በመፅሐፉ ውስጥ 26 ቃል ግጥሞች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ዘጠኙ የሙገሳ፣ ስምንቱ የተቃውሞ ፣አምስቱ የጀግንነት ፣ሦስቱ የፉከራ እና አንድ የሀዘን እንጉርጉሮ ይዘት አላቸው፡፡ ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት የሙገሳ ግጥሞቹ ዐፄ ዮሐንስን እና በርሳቸው ዘመን የነበሩ ራሶች የፈፀሙትን ተግባር ለማወደስ የቀረቡ ሲሆኑ የተቃውሞ ይዘት ያላቸው ደግሞ በዐፄ ምኒልክና በዐፄ ዮሐንስ መካከል የነበረውን የስልጣን ሽኩቻ የሚያሳዩ እና ዐፄ ዮሐንስ በጎጃም ህዝብ ላይ የፈፀሙትን ድርጊት የሚቃወሙ ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ.3 <u>ዐፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u>

| ተ.ቁ | ገጽ | የቃልግጥሙ አይነት | የስንኙ ብዛት | የተነገረበት አውድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 25 | ተቃውሞ | 4 | አቶ በዛብህ ምኒልክን ለመውጋት ሲዘጋጅ |
| 2 | 26 | ተቃውሞ | 6 | በዛብህ ምኒልክን ለመውጋት መሔዱን በመንቀፍ |
| 3 | 256 | ሙገሳ | 2 | ገበየሁ ከጣሊያን ጋር ተዋግተው በማሸነፋቸው |
| 4 | 254 | ፉከራ | 2 | የጣሊያኑ የጦር አለቃ ተመቶ ሲወድቅ |
| 5 | 288 | ጀግንነት | 2 | ሊቀመኳስ አባተ መድፍ በመተኮሳቸው |
| 6 | 597 | ስድብ | 2 | ተበላሽቶ ስለቆመው ባቡር |
| 7 | 598 | ሙገሳ | 5 | ዐፄ ምኒልክ ስልክ እና ባቡር በማስመጣታቸው |
| 8 | 610 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በመሞታቸው የባለቤቸው የወ/ሮ ላቀች ሀዘን መግለጫ |
| 9 | 610 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጅ የደጃች ሥዩም ለቅሶ |
| 10 | 610 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሞት |
| 11 | 611 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሞት |
| 12 | 614 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 6 | ለራስ መኮንን ሞት |
| 13 | 661 | ተቃውሞ | 8 | ጎጃምን ዐፄ ምኒልክ በአግባቡ ባለማከፋፈላቸው የህዝብ ቅሬታ |
| 14 | 666 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 18 | ለዐፄ ምኒልክ ንግሠተ ነገሥታት ዘውዲቱ የገጠሙት |

ተክለ ፃድቅ በዚህኛው መፅሐፋቸው 14 ቃል ግጥሞችን ብቻ ተጠቅመዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ስድስቱ የሀዘን እንጉርጉሮ ሲሆኑ የንጉሥ ምኒልክንና የንጉሥ ተክለሃማኖትን ሞት ምክንያት አድርገው የተገጠሙ ናቸው፡፡ ፀሀፊው የቃል ግጥም አጠቃቀማቸው ከ<u>ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት</u> እስከ <u>ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት</u> እየቀነሰ ነው የመጣው፡፡ ይህም የሚያሳየው ፀሀፊው ከልማዳዊ አፃፃፍ ወደ ዘመናዊ አፃፃፍ፤ ከቃላዊ መረጃ ወደ ፅሁፍ መረጃ መሸጋገራቸውን ነው፡፡

ሰንጠረዥ.4 <u>የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922</u>

| ተ.ቁ | ገጽ | የቃል ግጥሙ አይነት | የስንኝ ብዛት | የተነገረበት ዐውድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 21 | ሙገሳ | 2 | አፄ ምኒልክ ባቡር በማስመጣታቸው |
| 2 | 27 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ራስ በዛብህ ለንጉሥ ተክለ ኃይማኖት ሞት ሀዘን ሲገልፁ |
| 3 | 32 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 8 | ስለ ራስ መኮንን ሞት |
| 4 | 44 | ሙገሳ | 2 | የአፄ ምኒልክን መንግስት ስለመደገፍ |
| 5 | 68 | ሙገሳ | 2 | ፊታውራሪ ታዬ ጉልላቴ ዘውድ ተፋላሚ ስለ መሆናቸው |
| 6 | 77 | ሙገሳ | 2 | የራስ ቢትወደድ ተሰማን አስፈሪነት ለመግለፅ |
| 7 | 88 | ተቃውሞ | 2 | የራስ አባተን መታሰርና የደጃዝማች አብርሃን መፈታት በተመለከተ |
| 8 | 90 | ሙገሳ | 2 | የአቶ ተሰማ እሸቴን ሥራ በማድነቅ |
| 9 | 95 | ሙገሳ | 4 | ልጅ ኢያሱ በጊሚራ ዘመቻ ስለ ፈፀሙት ተግባር |
| 10 | 104 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 16 | ዐፄ ምኒልክ በመሞታቸው የወ/ሮ ዘውዲቱ ለቅሶ |
| 11 | 104 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | እቴጌ ጣይቱ በዐፄ ምኒልክ ሞት ስለ ተሰማቸው ሀዘን |
| 12 | 111 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | የምንጃር ገበሬ ስለ አፄ ምኒልክ ሞት የተሰማውን ሲገልፅ |
| 13 | 149 | ፉከራ | 3 | ከልጅ ኢያሱ አሽከሮች አንዱ ልጅ ኢያሱ ስልጣኑን እንደማይለቅ ሲፎክር |
| 14 | 157 | ሙገሳ | 2 | ደጃዝማች አያሌው ድል አድርገው ሲገቡ የተገጠመ |
| 15 | 211 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 6 | ለዐፄ ምኒልክ በጎንደር በተደረገ የለቅሶ ሥርዓት ላይ የተገጠመ |
| 16 | 211 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 4 | በጎጃም በዐፄ ምኒልክ ለቅሶ ላይ የተገጠመ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 17 | 211 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ለእቴጌ ጣይቱ ሞት የእቴጌ ዘመዶች፣ የጎንደርና የሰሜን ወይዛዝርት ሲያለቅሱ |
| 18 | 211 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ለእቴጌ ጣይቱ ሞት ደጃች አያሌው ብሩ የገጠሙት |
| 19 | 212 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ለእቴጌ ጣይቱ ሞት ወ/ሮ አሰለፈች ወንዴ የገጠሙት |
| 20 | 242 | መማፀን | 2 | ተሰማ እሸቴ ከእስራት እንዲፈቱ የተማፀኑበት |
| 21 | 324 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሞት አቶ ተሰማ እሸቴ የገጠሙት |
| 22 | 352 | ሙገሳ | 39 | ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ልዑል አልጋወራሽን ንጉሥ እንዲሆኑ በመፍቀዳቸው |

መርስዔ ኀዘን 22 ቃል ግጥሞችን በዝርው ትረካው መካከል ጣልቃ እያስገቡ ፅፈዋል፡፡ በመፅሐፉ ወስጥ የሀዘን እንጉርጉሮ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች ከፍተኛውን ቁጥር ይዘዋል፡፡ እነሱም 11 ሲሆኑ የዐፄ ምኒልክን ፣ የእቴጌ ጣይቱን እና የንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱን ሞት ምክንያት በማድረግ የተገጠሙ ናቸው፡፡

## ሰንጠረዥ.5 <u>የኢትዮጵየ ታሪክ ከ 1848 እስከ 1966</u>

| ተ.ቁ | ገጽ | የቃል ግጥሙ አይነት | የስንኙ ብዛት | የተነገረበት አውድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 68 | ስድብ | 2 | የራስ ደረሶ ጦር የዘረፈውን ጥሎ በመሸሹ |
| 2 | 103 | ስድብ | 2 | ሲነግሯት የማትሰማን ሴት ለመገሰፅ |
| 3 | 147 | ሙሾ | 5 | ራስ ጉግሳ ወሌ በተፈሪ በመሸነፉ |

በዘመናዊ የታሪክ አፃፃፍ ስልት ማስረጃ የማይገኝላቸውን መረጃዎች መጠቀም አይመከርም፡፡ ከዚህ በመነሳት በተለይም ቃል ግጥም በባሕሪው ህዝባዊና ተለዋዋጭ በመሆኑ በዘመናዊ የታሪክ አፃፃፍ ተቀባይነቱ አጠያያቂ ነው ፡፡ ለዚህም ይመስላል ባሕሩ በመፅሐፋቸው ሶስት ቃል ግጥሞችን ብቻ የተጠቀሙት፡፡

የታሪክ መፃሕፍቱ ነገስታቱ የኖሩበትን ዘመን ሁለንተናዊ ህይወት (ክፉውንም ደጉንም) ለማሳየት የሚፃፉ በመሆናቸው ክፉውን ለመንቀፍ ደጉን ለማወደስ ሲባል የተነገሩ ቃል ግጥሞችን በስፋት ይዘዋል፡፡እንዲሁም የታሪክ መፃሕፍቱ ረጅም እና ደረቅ ትረካዎች

ለአንባቢ አሰልቺ እንዳይሆኑ ለማድረግ በዝርው ትረካው መሃል እየገቡ ታሪኩን እያዋዙ ለመንገርና አንባቢንም ከምንባቡ ገታ በማድረግ እፎይታ እንዲያገኝ ለማስቻል የተጠቀሙባቸው ናቸው ለማለት ያስደፍራል ።

ሰንጠረዥ. 6 <u>ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ</u>

| ተ.ቁ | ገጽ | የቃል ግጥሙ አይነት | የስንኙ ብዛት | የተነገረበት አውድ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 36 | ተቃውሞ | 2 | ጎሜንሹ ሳይታዘዝ ሰዉን ሁሉ በማስጨረሱ |
| 2 | 51 | ተቃውሞ | 2 | ዐፄ ቴዎድሮስ ምኒልክን ማርከው ሲገቡ ምኒልክን ተከትሎ የዘመተውን ሰራዊት በሽታ ሲጨርሰው |
| 3 | 53 | ተቃውሞ | 2 | ዐፄ ቴዎድሮስ ሸዋ ላይ እጅና እግር ቆርጠው ስለሄዱ |
| 4 | 73 | ሙገሳ | 2 | ዳጃች ወሌ ከወንድሞቹ ጋር ተዋግቶ ድል በማግኘቱ |
| 5 | 73 | ሙገሳ | 2 | ደጃች ወሌ ወንድ ልጅ በመወለዱ |
| 6 | 83 | ጀግንነት | 2 | በሻህ አቦዬ የዐፄ ዮሐንስን ጦር በመምታቱና ምርኮ በማግባቱ |
| 7 | 103 | ፉከራ | 2 | በንጉሥ ምኒልክና በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መካከል ጦርነት ለመቀሥቀስ |
| 8 | 207 | ሙገሳ | 2 | ዐፄ ምኒልክ ግብር በማብላታቸው |
| 9 | 266 | ሙገሳ | 2 | ፊታውራሪ ገበየሁ በጣሊያን ጦርነት በመሰዋታቸው |
| 10 | 314 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 4 | የእቴጌ ጣይቱ እናት ወ/ሮ የውብዳር በመሞታቸው |
| 11 | 324 | የሀዘን እንጉርጉሮ | 2 | ለራስ መኮንን ሞት የተገጠመ |

በዐፄ ምኒልክ ዜና መዋዕል ውስጥ የሚገኙት ቃል ግጥሞች 11 ብቻ ሲሆኑ የሙገሳ፣ የሀዘን እንጉርጉሮ እና የተቃውሞ ይዘት ያላቸው ናቸው። ለቁጥራቸው ማነስ እንደምክንያት የሚቀርበው ዜና መዋዕሎቹ በባህሪያቸው ከቃል ግጥም ይልቅ አፈ ታሪክን ስለሚጠቀሙ ነው።  በዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ውስጥም ተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል።

*ጎጃምን ብንቆጣው በእሳቱ ተቀጣ*

*ወሎን ብንቆጣው በነፍጡ ተቀጣ*

*ይብላኝ ለወራሄ ይብላኝ ለስቆጣ*

*(አስፋው ፤1966 ፤32)*

የሚለው ቃል ግጥም ብቻ ነው የሚገኘው።

### 3.1.1.2 ዝርው ትረካዎች

ዝርው ትረካ ሀተታ ተፈጥሮዎችን ፤አፈ ታሪኮችን፤ ተረቶችን የእንስሳት ሞራላዊ ወጎችን የሚያካትት የሥነ ቃል ዘር ነው። ነገር ግን ከእነዚህ ውስጥ በታሪክ መፃሕፍቱ እና በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ የተገኙት ዝርው ትረካዎች አፈ ታሪኮች ብቻ ናቸው።

አፈ ታሪኮች ታሪክን ተንተርሰው የሚነገሩ ናቸው። የሚነገሩበትም የራሳቸው ዓላማ አላቸው።ጥናቱ ባተኮረባቸው መፃሕፍት ውስጥ ሶስት አፈ ታሪኮች ጎልተው ይታያሉ። የመጀመሪያው የሰሎሞን- ሳባ አፈታሪክ ሲሆን ለነገሥታቱ ሁሉ ዋነኛ የሃይል ሚዛን መጠበቂያ ሆኖ በመፃሕፍቱ ውስጥ ገብቷል። ለምሳሌ «ምኒልክ የቴዎድሮስን ሞት ሲሰሙ "ከይሁዳ ነገዶች ከዳዊትና ከሰሎሞን የምወለደው እኔ ነኝ። ለንጉሠ ነገሥታዊው ዙፋን ከኔ የሚቀርብ የለም» (ተክለ ፃድቅ፤1982፤10) የሚለውን ማየት ይቻላል። ምክንያቱም በኢትዮጵያ የንግሥና ባህል አንድ ሰው ንጉሠ ነገሥት ሊሆን የሚችለው ከሰሎሞናውያን ቤተሰብ ሲወለድ ነው። ካልሆነም በጉልበት ዝርያውን ከዛ መቁጠር ይጀምራል።

ሁለተኛው አፈ ታሪክ ደግሞ የምኒልክን የሸዋ ስርወ መንግስት የሚመለከት ነው። የምኒልክን የዘር ሃረግ በመቁጠር በሰሎሞናውያን የዘር ሃረግ ስልት አገራዊ ስርወ መንግስት አላቸው። ይህንን ሃሳብ በምዕራፍ አራት በሰፊው ስለማነሳው ለአሁኑ አፈ ታሪክነቱን ብቻ ማንሳቱ በቂ ነው።

ሶስተኛው አፈ ታሪክ ዐፄ ቴዎድሮስን የሚመለከት ነው። ዐፄ ቴዎድሮስ ሰሎሞናዊ ዘር የላቸውም ስለሚባል ይህን አፈ ታሪክ የሚተካና እሳቸውን ህጋዊ ንጉሠ ነገሥት የሚያደርግ ሌላ አፈ ታሪክ እንዳላቸው እንመለከታለን። «ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ከወደ ምስራቅ ተነስቶ በዘንግ (ያለ ሰይፍ) ይገባል። የተበላሸውን አስተዳደር አስወግዶ ሺህ አመት

ይነግሣል፡፡ በዘመኑም ሰላምና ትክክለኛ ፍርድ ይሆናል ግዛቱም እስከ ባሕር ነው» (ተክለ ፃድቅ ፣ 1981፣138)፡፡

የአፈ ታሪኩ ምንጭ ፍካሬ ኢየሱስ የተባለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መፅሐፍ ነው፡፡ ‹‹ከምስራቅ በኩል ታሪካዊና ደገኛ የሆነ ንጉሥ ይነሳል፡፡ እሱም ፈቃዴን የፈፀሙትን ከመከራ ያተረፍኳቸውን የሚሰበስብ ነው›› (1966፣ 59) የሚል ነው፡፡

### 3.1.1.3 አጫጭር የሥነ ቃል አይነቶች

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚጠቀሱት አጫጭር የስነቃል ዘሮች ቀልዶች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ፈሊጣዊ ንግግሮች ወዘተ. ሲሆኑ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡
ራስ ዐሊና ደጃች ውቤ (የዘመነ መሳፍንት የመጨረሻዎቹ ባለስልጣኖች ናቸው) መዋጋታቸውን እንጂ የጦርነቱን ውጤት ያልሰማ አንድ ሰው በመንገድ ያገኘውን ሌላ ሰው ሲጠይቀው:-

ጠያቂ - ‹‹እባክህ የራስ ዐሊና የደጃች ውቤ ጦርነት በምን አለቀ?››

መላሽ - ‹‹ከተዋጉ በኋላ ደጃች ውቤ ታሰሩ፣ ራስ ዐሊ ደግሞ ሸሹ››

ጠያቂ - ‹‹ኧረ እባክህ በወግ አድርገህ ንገረኝ?››

መላሽ -‹‹እነሱ ራሳቸው በወግ ያልሆኑትን እኔ እንዴት አድርጌ በወግ ላውራህ?››

(ተክለ ፃድቅ ፣ 1981 ፣ 100)

ምልልሱ ሳቅን የሚያጭር ነው፡፡ በዚህ ክፍል ማሳየት የተፈለገው የፎክሎሩን አይነት ብቻ ስለሆነ ከቀልድነቱ በተጨማሪ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በምዕራፍ አራት እመለስበታለሁ፡፡

ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ፈሊጣዊ ንግግሮች በታሪክ መፃሕፍቱም ሆነ በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የሥነ ቃል ቅርፆች ታሪክ ፀሀፊዎቹ ሃሳባቸውን ለመግለፅም ሆነ ለመቋጨት የሚጠቀሙባቸው ሲሆን ትረካው አሰልቺና ደረቅ እንዳይሆን ለማስቻል እንዲሁም ለቋንቋው ውበት ጉልህ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ በተለይ ፈሊጣዊ ንግግሮች በባሕሩ መፅሐፍ ውስጥ በብዛት ይገኛሉ፡፡ አይነታቸውንም ለማሳየት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ.8 በ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983 ውስጥ ያሉ የሥነቃል አይነቶች

| ተ.ቁ. | ሥነ ቃል | አይነቱ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 1 | የዘመነ መሳፍንት ማርከሻ ሆነ | ፊሊጣዊ ንግግር | 27 |
| 2 | በክፉ ዐይን | ፊሊጣዊ ንግግር | 27 |
| 3 | የሽንፈት ጽዋን ቀመሰ | ፊሊጣዊ ንግግር | 29 |
| 4 | በሽታውን የደበቀ መድሃኒት አይገኝለትም | ምሳሌያዊ ንግግር | 38 |
| 5 | የቁጣው መቅሰፍት ወረደባቸው | ምሳሌያዊ ንግግር | 41 |
| 6 | የጎን እሾክ | ፊሊጣዊ ንግግር | 41 |
| 7 | የሕፃን ጨዋታ | ፊሊጣዊ ንግግር | 51 |
| 8 | በእንግሊዞች የጦር ድግስ ላይ የምፀት ሳቁን ሳቀ | ፊሊጣዊ ንግግር | 43 |
| 9 | ሆደ ሰፊ ሆነ | ፊሊጣዊ ንግግር | 50 |
| 10 | ጆሮ ዳባ ልበስ አሉት | ፊሊጣዊ ንግግር | 52 |
| 11 | የመቅደላን መንገድ ጨርቅ አደረገላቸው | ፊሊጣዊ ንግግር | 53 |
| 12 | አለት ላይ የፈሰሰ ውሃ ሆነ | ምሳሌያዊ ንግግር | 53 |
| 13 | የተፃፈበት ቀለም ገና ሳይደርቅ ምጽዋን ሰጡ | ፊሊጣዊ ንግግር | 58 |
| 14 | የጠላቴ ወዳጅ ከጠላትም ጠላት ነው | ምሳሌያዊ ንግግር | 62 |
| 15 | የጥይት እራት ለመሆን በቃ | ፊሊጣዊ ንግግር | 63 |
| 16 | ባልሞት ባይ ተጋዳይነት | ፊሊጣዊ ንግግር | 77 |
| 17 | አይኗንም አላሸች | ፊሊጣዊ ንግግር | 81 |
| 18 | እርቃኑን ቀረ | ፊሊጣዊ ንግግር | 81 |
| 19 | ቅስሙ ተሰበረ | ፊሊጣዊ ንግግር | 86 |
| 20 | አንጀቱ ራሰ | ፊሊጣዊ ንግግር | 87 |
| 21 | ደጅ ጠናች | ፊሊጣዊ ንግግር | 98 |
| 22 | ከአንገት በላይ | ፊሊጣዊ ንግግር | 99 |
| 23 | እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል | ምሳሌያዊ ንግግር | 122 |
| 24 | እግር ጣለው | ፊሊጣዊ ንግግር | 129 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 25 | እምባ አድራቂ ሆኖ ቀረ | ፈሊጣዊ ንግግር | 131 |
| 26 | በዋል ፈሰስ | ፈሊጣዊ ንግግር | 131 |
| 27 | ቆሌያቸው ተገፈፈ | ፈሊጣዊ ንግግር | 132 |
| 28 | ቅስም ሰባሪ | ፈሊጣዊ ንግግር | 132 |
| 29 | የስልጣን ዝውውሩም በደም ተናደ | ፈሊጣዊ ንግግር | 137 |
| 30 | ወግ አጥባቂዎች | ፈሊጣዊ ንግግር | 140 |
| 31 | ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል | ምሳሌያዊ ንግግር | 142 |
| 32 | ብልጥ ለብልጥ ፍጥጥ | ፈሊጣዊ ንግግር | 153 |
| 33 | አንገት ደፋ | ፈሊጣዊ ንግግር | 159 |
| 34 | የልብ ልብ ተሰማው | ፈሊጣዊ ንግግር | 159 |
| 35 | አይን አወጣ | ፈሊጣዊ ንግግር | 160 |
| 36 | ማቅ ተከናነበ | ፈሊጣዊ ንግግር | 162 |
| 37 | ቆሌው ተገፈፈ | ፈሊጣዊ ንግግር | 163 |
| 38 | የእግር እሳት ሆነ | ፈሊጣዊ ንግግር | 167 |
| 39 | ካለወቁት መልአክ ያወቁት ሰይጣን ይሻላል | ምሳሌያዊ ንግግር | 227 |
| 40 | አይን ገላጭ ነበረ | ፈሊጣዊ ንግግር | 235 |
| 41 | ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም | ምሳሌያዊ ንግግር | 240 |
| 42 | በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ | ምሳሌያዊ ንግግር | 241 |
| 43 | ትልቁን ግንድ ለመቁረጥ መጀመሪያ ቅርንጫፎቹን መልምል | ምሳሌያዊ ንግግር | 245 |
| 44 | የአፍዝ አደንግዝ | ፈሊጣዊ ንግግር | 245 |
| 45 | በቁስል ላይ እንጨት መስደድ | ምሳሌያዊ ንግግር | 243 |
| 46 | ሐሞቱ ፈሰሰ | ፈሊጣዊ ንግግር | 177 |
| 47 | አድራጊ ፈጣሪ | ፈሊጣዊ ንግግር | 218 |
| 48 | ፈላጭ ቆራጭ | ፈሊጣዊ ንግግር | 211 |
| 49 | ዕጣ ፈንታ | ፈሊጣዊ ንግግር | 255 |
| 50 | ጆሯ ተባ | ፈሊጣዊ ንግግር | 255 |
| 51 | እውር ድንብሩን | ፈሊጣዊ ንግግር | 257 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 52 | ዶፍ ያዘለ ደመና | ፈሊጣዊ ንግግር | 258 |
| 53 | የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል | ምሳሌያዊ ንግግር | 259 |

በባሕሩ መፅሐፍ ውስጥ 10 ምሳሌያዊ ንግግሮች እና 43 ፈሊጣዊ ንግግሮች ይገኛሉ።በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው የታሪክ ድርሰት ተነባቢ እና አይረሴ እንዲሆን የቋንቋ አጠቃቀሙ ወሳኝነት አለው። ለዚህም ይመስላል ባሕሩ እነዚህን አጫጭር የስነ ቃል ዘሮች በብዛት የተጠቀሙት።

## 3.1.2 ሀገረሳባዊ ልማድ

ሀገረሰባዊ ልማድ በውስጡ የሚያካትታቸው ነገሮች /ልማዶች/ ብዙ ናቸው። ስምና የስም አወጣጥ፣ ጋብቻንና ሞትን ተከትለው የሚባሉና የሚደረጉ ልማዶች፣ ሹመት ከበራና በዓላት፣ መሐላ፣ ግዝት፣ የባሕል መድሐኒቶች፣ ወዘተ. ጥቂቶቹ ናቸው። በመፃሕፍቱ ውስጥ ከሚገኙት ዋና ዋና ልማዶች መካከል ሶስቱ ለአብነት ከዚህ በታች ቀርበዋል።

### 3.1.2.1 ስያሜ

በኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ ስያሜ ጉልህ ሥፍራ የሚሠጠው ልማዳዊ ድርጊት ነው። ነገሥታቱ፣ መሳፍንቱና መኳንንቱ ከሥልጣን ደረጃቸው ጋር በተያያዘ የንግሥና ፣ የማዕረግ እንዲሁም የፈረስ ስም ይወጣላቸዋል። ስያሜውም በዘፈቀደ የሚሰጥ ሳይሆን የግለሰቡን ተግባርና ባህርይ የሚወክል እንዲሆን ታስቦ ነው።

አንድ ንጉሥ ሲነግሥ የቀድሞ መጠሪያ ስሙን ትቶ አዲስ ስመ መንግሥት ይወጣለታል። ዐፄ ቴዎድሮስ አባትና እናታቸው ያወጡላቸውንና 35 ዓመት ሲጠሩበት የነበረውን ካሣ የሚባለውን ስማቸውን ትተው ቴዎድሮስ ተብለዋል። ዋግሹም ጎበዜም ሲነግሱሡ ተክለ ጊዮርጊስ በሚል ተጠርተዋል። በዝብዝ ካሣም ሲነግሱ ዮሐንስ አራተኛ መባላቸው ይታወሳል። ምኒልክም ዳግማዊ ምኒልክ ተብለዋል። ተፈሪ መኮንንም በክርስትና ስማቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሚል ተጠርተዋል።

ይህንን መሰሉ የስያሜ ለውጥ ባህል ነው ብቻ ተብሎ የሚታለፍ ሳይሆን ስያሜዉ ከመጠሪያነቱ ባሻገር ያለው መልዕክት መጠናት ያለበት ጉዳይ ነው። ካሣ ቴዎድሮስ መባልን የፈለጉት «ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ከወደ ምስራቅ ተነስቶ በዘንግ (ያለ ሰይፍ) ይገባል። የተበላሸውን አስተዳደር አስወግዶ ሺህ አመት ይነግሣል። በዘመኑም ሰላምና ትክክለኛ ፍርድ ይሆናል -ግዛቱም እስከ ባሕር ነው» (ተክለ ፃድቅ ፣ 1981፣138)።

የሚለውን ትንቢት በመከተል የተበላሸውን የዘመነ መሳፍንት ጊዜ የማስተካክለው እኔ ነኝ፤ስሜ ግብሬን ይወክላል ሲሉ ነው።

ዐፄ ምኒልክም አያታቸው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በተነገራቸው ትንቢት "ዓለሙን አደባልቆ አንድ አድርጎ የሚገዛ እርሱ ነው" (ገብረሥላሴ፣1956፣ 42) ሲሉ ስመ መንግሥታቸውን ለልጅ ልጃቸው አውርሰዋል። ኋላም ምኒልክ ሲነግሡ ዳግማዊ ምኒልክ ብለው መጠሪያቸውን ማፅደቃቸው የሰሎሞናዊውን ስርወ መንግሥት ለማፅናትና የቀዳማዊ ምኒልክ ህጋዊ ወራሽ እኔ ነኝ የሚለውን ለማመልከት ነው። የሌሎቹም ነገሥታት የስመ መንግሥት አጠራር በዚሁ ስልት የሚታይ ነው።

በዘመኑ የነበሩ የማዕረግ ስሞችም ከዚሁ ጋር አብረው የሚታዩ ናቸው። ዐፄ፣ እቴጌ፣ ልዑል፣ ራስ፣ ቀኝ አዝማች፣ ግራ አዝማች፣ ባላምባራስ፣ ፊታውራሪ፣ በጅሮንድ፣ ነጋድራስ ወዘተ. የሚሉት የማዕረግ ስሞች እንደ ግለሰቡ ኃላፊነትና የሥራ ድርሻ የሚሰጡ ናቸው። የማዕረግ ስሞቹ ራሳቸውን ችለው የሚጠኑ ስለሆኑ በዚህ ክፍል የስያሜ አይነቶች መሆናቸውን ብቻ ጠቅሼ አልፋለሁ።

በታሪክ እንደሚወሳው ፈረስ ለነገሥታቱ፣ ለመኳንንቱና ለሹማምንቱ የቅርብ ጓደኛና የክብር መገለጫም ነው። ፈረስ ግልቢያም የወንዶች ሙያ እና የጀግንነት መለኪያ ነበር። ለፈረስ ስም ማውጣትና በፈረስ ስም መጠራት፣ በፈረስ ስም መፎከር /መሸለል/ በወቅቱ አንዱ ልማዳዊ መግባቢያ ነበር።

*የፈረስ ስም አባ፤ ወይም አባት የሚለውን ቃል በማስቀደም ባንዲት ቃል ብቻ የተነገረ ቢሆንም ጠለቅ ብለው ሲመረምሩት የባለ ፈረሱን የጠባይ ሁኔታ ምኞቱን ጭምር አጠቃሎ የሚያሳይ ሰፊ ትርጉምና መገለጫ የያዘ ሆኖ ይገኛል /ማኅተመ ሥላሴ፣1961፣5/።*

ስያሜው ለፈረሱ የሚሰጥ ቢሆንም የነገሥታቱን ወይም የመኳንንቱን ደግነት፣ ፍትህ አዋቂነት፣ ጨካኝነት፣ ጀግንነት ወይንም የፈረሱንም መልክ ሊከተል ይችላል። እነዚህን ተግባራትና ባህርያት እንዲወክል ተደርጎ፤ በባለፈረሱ ግለሰብ ባልደረቦች፣ ሎሌዎች አለያም በአዝማሪዎች ሊወጣ ይችላል። አንዳንዶ ባለፈረሱም ራሱ ምኞትና ፍላጎቱን ለመግለፅ የሚያወጣው ስያሜም ይኖራል።

ለጥናቱ በተመረጡት የታሪክ መፃሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ የበርካታ ነገሥታት፤ መኳንንትና ሹማምንት የፈረስ ስሞች ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ የዐፄ ቴዎድሮስ

አባ ታጠቅ፣ የዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ፣ አባ ጆሐድ፣ የዐፄ ዮሐንስ፣ አባ በዝብዝ፣ የዐፄ ምኒልክ አባ ዳኘው፣ የአቤቶ ኢያሱ አባ ጤና፣ የዐፄ ኃይለ ሥላሴ አባ ጠቅል የሚሉት ይገኛሉ።

ከላይ እንደተገለፀው ስያሜው ምክንያታዊ ሲሆን ለምሳሌ ዐፄ ምኒልክ የፈረስ ስማቸው አባ ዳኘው መባሉ "የሁሉም በላይ የሁሉም ጌታ ነህ ባንድ አድርገህ ዳኛቸው። ግዛቸው። በትክክል አስተዳድራቸው" /ዝኒ ከማሁ 1961፤7/ ለማለት ነው። የሌሎቹም ነገሥታት በዚህ መልኩ የወጣ ነው።

የፈረስ ስም ወኔ መቀስቀሻ፣ ጀግንነት መግለጫም ይሆናል። ታሪኩ በሚጠራው ዘመን በሰልፍ፣ ባዳራሽ፣ በግብርና በመሳሰሉት ስፍራዎች በንጉሡ ወይም በመኳንንቱ ፊት እየተንጎራደዱ የእገሌ ጌታ እያሉ መፎከር የተለመደ ነበር።

*አካኪ ዘራፍ፣ አካኪ ዘራፍ፣*
*ዘራፍ የጠቅል ሎሌ /2/*
*በሰፊው አውድማ የተበጠረው*
*ገለባው ሄዶ ምርቱ የቀረው*
*ገለባው ሄዶ ምርቱ የቀረው*
*/ዝኒ ከማሁ፤8/*

ጠቅል የኃይለ ሥላሴ የፈረስ ስም ሲሆን እርሳቸውን ለማወደስ የቀረበ ፉከራ ነው። በዘመኑ ይህንን መሰል ቀስቃሽ ፉከራዎችና ሽለላዎች በስፋት ይቀርቡ ነበር።

### 3.1.2.2 ሀገረሰባዊ መድኃኒት

የታሪክ መፃሕፍቱና ዜና መዋዕሎቹ በሚወክሉት ዘመን ዘመናዊ ሕክምና በአገራችን የተስፋፋ ስላልነበረ ሕብረተሰቡ ከህመሙ ለመፈወስ፣ ወታደሩ ቁስሉን ለማከም በሀገረሰባዊ ሕክምና ይጠቀሙ ነበር።

በወቅቱ ከነበሩት እና አሁንም ድረስ ጥቅም በመስጠት ላይ ከሚገኙ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች አንዱ የኮሶ ፍሬን የመጠጣት ባህላዊ ህክምና ነው። የኮሶ ፍሬ የኮሶ ትል ለተጣባው ህመምተኛ የሚሰጥ መድሃኒት ሲሆን የራሱ የሆነ የአወሳሰድና የአዘገጃጀት ልማዳዊ ሥርዓት አለው። አዘጋጃጀቱ "...ፍሬው ተለቅሞ ሲደርቅ ተፈጭቶ፣ ተልሞ በውሃ ተበጥብጦ በዋንጫ ወይም በብርጭቆ ተለክቶ በባዶ ሆድ ይጠጣል" /(ተክለ ፃድቅ ፤ 1981 ፤76/ ይህን ሲመስል የመድሃኒቱ አወሳሰድም የራሱ ባህላዊ ሥርዓት አለው።

*ባል ኮሶ ሲጠጣ ሚስቱን፣ ሚስት ባሏን፣ ልጆች አባትና እናታቸውን ይሰናበታሉ። ንጉሥም ቢሆን ንግሥቲቱን፣ ጭፍራም እንደሆነ አለቃውን ይሰናበታል። ይሰናበታል ማለት "ደህና ሁኑ" ብሎ ይሄዳል ማለት ሳይሆን ዛሬ ኮሶ ስለጠጣሁ በሻርሁ ጊዜ ምግቤን ከናንተ ወይም ከአንተ እጠብቃለሁ ማለት ነው (ዝኒ ከማሁ ፣76)።*

በተጨማሪም ጠጪው ልሞትም እችላለሁ ብሎ ስለሚፈራ ቤተሰቡን ይሰናበታል። በዚህም ልማድ መሠረት እንደ በሽተኛው ማህበራዊ ደረጃ፣ ለጋባገፍ እንዳለው ቅርበትና ፍቅር ግብዣ ይዘጋጃል። ኮሶው ለመጠጣት መራራ ስለሆነ ልጆችም ጨክነው እንዲጠጡ «ዶሮ ማታ! ዶሮ ማታ!» እያሉ አባትና እናት ያደፋፍሯቸዋል። በዚህ ሁኔታ የባህላዊ ህክምና ሥርዓቱ ይፈፀማል። ሌላው በዘመኑ ተከስቶ የነበረውን የትኩሳት በሽታ ለመፈወስ ጥቅም ላይ የዋለ ባህላዊ ህክምና ነበር። " ይኸውም የኘንጥላ መገተሪያ ብረት በእሳት አግሎ የበሽተኛውን ገላ በተኰሱት ጊዜ ይንጣጣ ነበርና ከዚያ የተነሣ የበሽታውም ስም ጣጣቴ ተባለ" /መርስዔ ኅዘን፣1999፣ 122)። በማለት ስለ ህክምናው ዕፈዋል። በመፃሕፍቱ ውስጥ ሌሎች ሀገረሰባዊ መድኃኒቶች የሠፈሩ ሲሆን በተለይም የዘመኑ ወታደር ቁስለኛ የሚያክምበት ልዩ ልዩ ሥራሥርና ቅጠላቅጠል እንደነበሩ ተጠቅሶ ይገኛል።

### 3.1.2.3 ሀገረሰባዊ ዕምነት

ሀገረሰባዊ ዕምነት ማህበረሰቡ የሚያምንባቸው፣ ክፉውን ለማራቅና ጥሩውን ለማቅረብ ሲል የሚተገብራቸው ዕምነቶች ናቸው። ለምሳሌ ጥንቆላ፣ ዛር፣ ትንቢት፣ ህልም፣ እርግማን፣ ልዩ ልዩ አምልኮ ወዘተ. የመሣሠሉትን ያካትታል። ጥናቱ ባተኮረበት ዘመንም ነገሥታቱም ሆኑ ህፃዘቡ ከዚሁ እምነት ጋር በእጅጉ የተቆራኙ እንደነበሩ የታሪክ መፃሕፍቱ ያወሳሉ። ለንግሥና፣ ዘመቻ ለመሔድ፣ ድል ለማግኘት፣ ህዝብን ለማስተዳደርና ለመሣሠሉት ተግባራት ነገሥታቱም ሆኑ ህብረተሰቡ ከሀገረሰባዊ ሃይማኖቱ የሚጠብቀው አንዳች ምላሽ ነበር። ዐፄ ቴዎድሮስና ዐፄ ምኒልክ ለጉሥነት መታጨት አንዱ ምክንያት ትንቢትና በህልም መገለፅ የሚሉት ሀገረሰባዊ ዕምነቶች እንደነበሩ ከመፃሕፍቱ መረጃ መጥቀስ ይቻላል።

ጥንቆላ፣ ዛር፣ ርግማን፣ ምርቃን፣ ትንቢት፣ ድግምት፣ ምልኪ እና ሌሎች በርካታ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ለጥናቱ በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ ይገኛሉ። ሁሉንም ዘርዝሮ ማሳየት ባይቻልም ለአብነት የሚከተሉትን አቅርቤአለሁ።

ዐፄ ቴዎድሮስ የምሥራቅ ወሎ ገዢ የነበሩትን ወ/ሮ ወርቂት ለመምታት ወደ ወረሂመኑ ይዘምታሉ። በዚህን ጊዜ አንድ ጠንቋይ ለወ/ሮ ወርቂት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንደሚከተለው ይነግራቸዋል።

*ወረሂመኑ አምራ ገደል ከሚባለው አገር አንድ ቃልቻ ነበር። ስሙም ሼህ ያሲን ይባላል። ይኸንን ንጉሥ አላስመጣውም ብሎ ወዳኛ ያዘ። ሶስት ቀን በሆነ ጊዜ መልአክ ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ ጦር ይዞ ለሁሉ መቅጫ ያወረደውን /ቴዎድሮስን/ ግደልልኝ አልሁ?......አሁን ከምድር ጋር በስፋሁህ! ብሎ አስፈራራኝ በማለት.......በነጋታውም መቅደላ መጥቶ ወይዘሮ ወርቂትን አንቺም ሸሺ እኔም አልሆንልኝም። እኔም ዛሬ ሌሊት ልሞት ነበር። ይህ ሰው ከአላህ የተላከ ነው.... (አስፋው፣1966 ፣19)።*

በማለት ጠንቋዩ ለወ/ሮ ወርቂት እንደነገራቸውና እርሳቸውም እንደሸሹ ዜና መዋዕሉ ያስረዳል። በርግጥ ወ/ሮ ወርቂት የሸሹበት ትክክለኛ ምክንያት ጠንቋዩ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ባይቻልም (የጥናቱም ዓላማ አይደለም) ህገረሰባዊ ዕምነቱ በዘመኑ የነበረውን ገፅታ ያሳያል።

ዐፄ ምኒልክም ህመማቸው ፀንቶ በአልጋ ከዋሉ በኋላ መንግሥታቸውን ለልጅ ኢያሱ ለማውረስ የኑዛዜ ቃላቸውን ይሰጣሉ። ኑዛዜያቸውንም የሚያፀኑት በእርግማን ነበር።

*.... ከፉ ሥራ እሠራለሁ የሚል ሰው እረግሜዋለሁ። የይሁዳ ርግመት የአርዮስ ግዝት ይድረስበት። ይሄን ቃል ያፈረሰ ሰው መሬት ይከዳው፣ ጥቁር ውሻ ይውለድ፣ ያሳደግኋችሁም.... ከኔ ፈቃድ የወጣ ሰው ረግሜዋለሁ.... (ተክለ ፃድቅ፣ 1985፣63)*

በማለት ዐፄ ምኒልክ ሥልጣናቸውን አስተላልፈዋል። በዘመኑ ህዝቡ አንድም የንጉሥ ቃል በመሆኑ ሌላም ርግማኑን /ከዕምነት አንፃር/ በመፍራት የልጅ ኢያሱን ንግሥና መቀበሉን እንረዳለን። ህገረሰባዊ ሃይማኖት ከዕምነትነቱ ባሻገር ከላይ የተጠቀሱትን የመሰሉ ሥልጣን መያዥያ፣ ህዝብ ማስተዳደሪያ ውስጣዊ ተልዕኮም ነበራቸው።

ሌሎች ህገረሰባዊ ዕምነቶች በተለይም በመርስዔ ኅዘን መፅሐፍ ውስጥ በስፋት ይገኛሉ። ለምሳሌ አዶከብሬ (ገጽ 122)፣ ጋኔን፣ ደንቃራ (ገጽ 58)፣ ንግርት (ገጽ 58፣76) ምርቃት (ገጽ 192) ማየት ይቻላል።

## 3.1.3 ትውን ጥበባት

ትውን ጥበባት ባህላዊ አልባሳት ተለብሶ፣ በህገረሰባዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ታጅቦ በልዩ ልዩ ሥርዓቶች ላይ የሚቀርቡ ባህላዊ ትዕይንቶች ናቸው። እነዚህ ትውን ጥበባት በመፃሕፍት ውስጥ ሲቀርቡ ስለማይታዩና ስለማይደመጡ ለስሜት የራቁ ይሆናሉ። ቢሆኑም አንባቢ ፅሁፉን አንብቦ በአዕምሮው የሚያስቀረው አንዳች ምስል ይኖራል። ከዚህ አንፃር በታሪክ መፃሕፍቱና በዜና መዋዕሉቹ ውስጥ ለንግሥና በዓል፣ ለታቦት ንግሥ፣

ለእንግዳ አቀባበል፣ ለሞትና ለመሣሠሉት ዝግጅቶች በህዝቡ የቀረቡ ትውን ጥበባት ይገኛሉ።

በመፃሕፍቱ የሚገኙ ትውን ጥበባት በአብዛኛው በሀገረሰባዊ አልባሳትና በሀገረሰባዊ የሙዚቃ መሣሪያ የታጀቡ ልዩ ልዩ የሰልፍ ትዕይንቶችና በታቦት ንግሥ በዓላት ላይ የሚከወኑ ጥበባት ናቸው። ከዚህ በመቀጠል በመፃሕፍቱ ውስጥ የሚገኙ ትውን ጥበባት ምን ገፅታ እንዳላቸው ለማሳየት ሶስት የተለያዩ ክስተቶችን አቀርባለሁ።

ዐፄ ዮሐንስ የሸዋውን ንጉሥ ምኒልክ ሲቀበሉ የነበረውን ትዕይንት ተክለ ፃድቅ እንደሚከተለው ገልፀውታል «....ልብሰ መንግሥት ለብሰው፣ ዘውድ ጭነው፣ በትረ መንግሥታቸውን ይዘው ወታደሮቻቸውን ቀኝና ግራ አሰልፈው ምኒልክ ሲደርሱ፣ መድፍ እያስተኮሱ፣ እምቢልታና መለከት እያስነፉ በታላቅ ክብር ተቀበሏቸው »(ተክለ ፃድቅ፣1982 ፣ 177)።

ከጥቅሱ የምንረዳው ታሪኩ በወከለው ዘመን የነበረውን የክብር ማሳያና የእንግዳ አቀባበል ሥርአት ነው። ልብሰ መንግሥት መልበስ፣ ዘውድ መጫንና በትረ መንግሥት መያዝ ሀገረሰባዊ አልባሳት ሲሆኑ እምቢልታና መለከት ማስነፋቱ ትዕይንቱን ማድመቂያ ሀገረሰባዊ የሙዚቃ መሣሪያ ናቸው። ትውን ጥበቡም የእንግዳ አቀባበል ሥርዓቱን ለማድመቅና ክብር ለማስጠት እንዲሁም የዐፄ ዮሐንስን የበላይነት የሚያሳይ ፖለቲካዊ ፋይዳም ያለው ነው።

የአንድ መንግስት ሃይል እና ጥንካሬ ከሚለካባቸው መስፈርቶች መካከል የወታደሩ አቋምና ወታደራዊ ሥርዓት ተጠቃሽ ናቸው። ስለሆነም በየዘመኑ የነበሩ ነገሥታት የወታደራቸውን ጤናማነትና ብቃት ለአገር ውስጥ ገዥዎችም ሆነ ለውጭ መንግሥታት ለማሳወቅ ወታደሩ በጦር መሣሪያና በሀገረሰባዊ ሙዚቃ /መለከት፣ ጥሩንባ/ ታጅቦ እንዲሰለፍ ማድረጋቸው በታሪክ መፃሕፍቱ ሰፍሮ ይገኛል። የመርስዔ ኀዘንን መፅሐፍ ገጽ 97፣ 192፣ 297፣ 318፣356 መመልከት ይቻላል። ሌላው በመፃሕፍቱ በስፋት የሚታየው በሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ላይ የሚከወነው ትውን ጥበብ ነው። ቀሳውስት እና ምዕመናን ልዩ ልዩ ሀገረሰባዊ አልባሳትን ለብሰው በባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ /በከበሮ፣ በፅናፅል ወዘተ/ ታጅበው በዝማሬ፣ በሽብሸባ በዓሉን ያከብራሉ። በሆሳዕና በዓል ላይ የነበረውን ትውን ጥበብ መርስዔ ኀዘን እንደሚከተለው ገልፀውታል።

*ልብስ ተክህኖ የለበሱ ቀሳውስትና ዲያቆናት በዐውደ ምሕረቱ ላይ ከመዘምራኑ በስተኋላ ተሰለፉ። መዘምራኑ በድርብና በአብደላከኒ ቀሚስ አጊጠውና ተሰልፈው በስተፊት ቆሙ። የቀሩት ካህናት ግን በዐውደ ምሕረቱ በምንጣፍ ላይ ተቀመጡ።*

*ቆመው ያሉትም መዘምራን ተጽዒኖ ዲበ ዕዋል ኢየሩሳሌም በአ በክብር የሚለውን የያሬድን ዜማ በዝማሜ ስልት እያቀነቀኑና በዝግታ እርምጃ እየተራመዱ ወደ ተቀመጡት ካህናት መጡ። በየዜማውም መጨረሻ መቋሚያቸውን ደቅ እያደረጉና እጅ እየነሡ ቀረቡ /1999፣33-34/።*

ልብስ ተክህኖ የለበሱ /ሀገረሰባዊ አልባሳት/ ዲያቆናትና ቀሳውስት በሀገረሰባዊ የሙዚቃ ስልት መቋሚያቸውን ደቅ በማድረግና በማሸብሸብ ትውን ጥበቡን አሳይተዋል። በዚሁ በመርስዔ ኅዘን መጽሐፍ ውስጥ በተለይ ለዐፄ መስቀል ክብረ በዓል የተከወኑ ትውን ጥበባት በዝርዝር ቀርበዋል። ለምሳሌ በገጽ /103፣131፣294፣297፣376 ላይ መመልከት ይቻላል።

በሞት፣ በሹመት በጋብቻና በመሣሠሉት ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚከወኑ ትውን ጥበባት በመፃሕፍቱ ውስጥ አልፎ አልፎ ይገኛሉ። ለአብነት በለቅሶ ሥርዓት ላይ የሚከወን ትውን ጥበብ እንመልከት:-

*የመሞታቸውም መርዶ ለግርማዊት ንግስትና ለልዑል አልጋ ወራሽ ሲነገር መድፍ ተተኩሶ ነጋሪት ተጎሸመ።... ሬሣቸውን በክብር አሸክመው፣ ጥሩምባው እምቢልታው የሀዘን ዜማ እያዜመ ወታደር በቀኝና በግራ ተሰልፎ ካህናት የጉዞ ፍትሐት እያደረሱ ወደ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ጉዞ ሆነ /1999፣ 323-324/።*

የሞቱት ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ነበሩ። እላይ የተገለፀው ትውን ጥበብ የተከወነው በእርሳቸው ሞት ምክንያት ነው። የመድፉ መተኮስ፣ የነጋሪቱ መጎሸም፣ የጥሩምባውና የእምቢልታው መነፋት እንዲሁም የወታደሩ ስልፍ ሥርዓት ቀብሩን አድማቂ እና ለሰውየው የተሰጠውን ክብር አመላካች ትውን ጥበባት ናቸው።

### 3.1.4 ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህሎች በባህሪያቸው ተጨባጭ ናቸው። ይታያሉ፣ ይዳሰሳሉ፣ ይጨበጣሉ። በዚህ ጥናት የሚጠኑት ቁሳዊ ባህሎች ግን ይህንን ባህሪይ ሙሉ ለሙሉ የሚያሟሉ አይደሉም። ምክንያቱም ከመፃሕፍት ተለቅመው የወጡና የማይዳሰሱ፤ የማይጨበጡ ስለሆኑ ስሪያቸውንም ሆነ ተጠቃሚያቸውን በአካል አግኝቶ ማጥናት አይቻልም። ቢሆንም ቁሶቹ የማህበረሰቡን ባህል፣ የዘመኑን መንፈስ፣ የህብረተሰቡን አመለካከት፣ ፍልስፍናና ፍላጎት ወዘተ. ከመወከልና ከማሳየት አንፃር ያላቸውን ፋይዳ ማጥናት ይቻላል።

ጥናቱ ባተኮረባቸው መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች በርካታ ናቸው። ለማሳየት እንዲመች አልባሳት፣ መገልገያ ቁሶችና ምግብ በሚል ከፍያቸዋለሁ። በአልባሣት ሥር የንግሥና፣ የማዕረግ፣ የሀዘን፣ የታቦት ንግሥ፣ የሰርግ፣ የወታደር፣ የተራው ማህበረሰብ፣ የገበሬ ወዘተ. በመገልገያ ቁሶች ሥር ደግሞ ማህተም፣ ማብሰያ፣ መጠለያ፣ የጦር መሣሪያዎች፣ ዙፋን፣ ወዘተ. ሲሆኑ ግብር፣ የወታደሩ ስንቅ፣ የዘወትር ምግብ /የተራው ህዝብ/ ምግብ በሚለው ሥር ይካተታሉ። ለአብነት የተወሰኑት ቀጥሎ ቀርበዋል።

## 3.1.4.1 አልባሳት

ነገሥታቱ፣ መኳንንቱ፣ ሹማምንቱ እንዲሁም ተራው ማህበረሰብ የራሱ መለያ የሆነ የአለባበስ ዘዬ አለው። በዐፄ ምኒልክ ዘመን የነበረው የአንድ ንጉሥ የማዕረግ አልባሳትን ማኅተመ ሥላሴ ሲገልፁ:-

*የራስ ዘውድ:- በወርቅና ባልማዝ የተሠራ ርባን ሥራ*

*ላንቃ:- በጣም ረዥም ሊቀ መኳሶች የሚደግፉት ሙካሽ ሥራ*

*ካባ ላንቃ:- ወርቅ ጥልፍ ባለ ዘርፍ መደቡ አረንጓዴ ከፋይ*

*ካባ:- በሙካሽ የተሠራ ከፋይ ሙሉ ወርቅ ጥልፍ እስከ ትከሻው የወረደ*

*ቀሚስ:- እጅጌው በሙካሽ የተሠራ ዐብደላ ካኒ*

*ሱሪ:- አረንጓዴ ከፋይ ወርቅ ጥልፍ ሙካሽ ሥራ*

*የሚጣፋ ልብስ:- ድርብ ኩታ*

*ድግ:- አረንጓዴ ሐር*

*ጥላ:- ቀይ ከፋይ ባለወርቅ ጥልፍ ሙካሽ ሥራ*

*ጋሻ:- በወርቅና ባልማዝ የሆነ ርባን ሥራ ልብሱ አረንጓዴ ከፋይ*

*/1942፣ 677/*

በማለት አልባሳቱን እስከ መሠሪያ ቁሳቸው አስፍረዋል።

በርግጥ አልባሳቱ እንደየ ሁኔታው ለንግሥና በዓል፣ ለአዘቦት ቀን፣ ለክብረ በዓላት፣ ለእንግዳ አቀባበል ለመሣሠሉት ሊለያዩ ይችላሉ። ለምሳሌ ዐፄ ቴዎድሮስ ምቾትና ቅንጦት የማይሹ፤ ለአለባበሳቸውም የማይጨነቁ እንደነበሩ የታሪክ መጻሕፍቱ ያወሳሉ(ባሕሩ፣1999፣28)። ይሁንና ንጉሡ ህልማቸውን እውን እንደሚያደርግላቸው የተማመኑበት የእንግሊዝ መልዕክተኛ ቆንስል ኬምሮን ሲመጣ አለባበሳቸውን አሳምረው ድል ያለ ድግስ ደግሰው ይቀበሉታል «.... ልብሰ መንግሥትዎን እንደለበሱ፤ ዘውድዎን በራስዎ ደፍተው ግራና ቀኝ አራቱ ሊቀ መኳንንቶች ንጉሡ እንደለበሱት ያለ ካባ ላንቃ ለብሰው ራሶችም ራስ ወርቃቸውን እያሰሩ .....» (ተክለ ፃድቅ፣ ፣1981፣ 289) በዚህ መልኩ

ንጉሡ የራሳቸውንም ክብርና ሃያልነት ለማሳየት እንዲሁም ለመልእክተኛውና /ለእንግሊዝ መንግስት/ ያላቸውን ክብር ለመግለፅ አልባሳቱን ተጠቅመዋል፡፡

በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን የነበረው ወታደርና ነጋዴም ልብሱ ካንድ ነጠላና ካጭር ሱሪ አያልፍም /ዝኒ ከማሁ፣ 277/ ሲሉ ተክለ ፃድቅ ጠቅሰውታል፡፡ በተመሳሳይ የዐፄ ምኒልክ ወታደርም አለባበሱ «... አብዛኛው አጭር ሱሪና ጥብቆ ለብሶ በዚያ ላይ ነጠላውን ደርቧል፡፡ የሚራመደው በባዶ እግሩ ከደንጊያና ከእንጨት እንቅፋት ጋር እየታገለ ውስጥ እግሩን እሾህ በሙቀት ጊዜ ረሞጫ እያቆሰለው ነው»( ዝኒ ከማሁ፣ 1985፣227)፡፡አልባሳቱ በዘመኑ የነበረውን ወታደር ውጫዊ አቋሙን ፣ ውስጣዊ ጥንካሬውንና የዓላማ ፅናቱን ያሳያሉ፡፡

ከማዕረግ አልባሳቱ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ኒሻን ነው፡፡ ኒሻን በታማኝነት፤ በቅንነት መንግሥታቸውን ላገለገሉ፤ ለጦር ሜዳ ጀግኖች፤ በጥበብ ሥራ አስተዋፅኦ ላበረከቱና ይህን መሠል ተግባር ለፈፀሙ የሚሠጥ ሽልማት ነው፡፡ ኒሻን የተለያየ ደረጃ እና አይነት አለው፡፡ የሰሎሞን ኒሻን፣ የንግሥተ ሳባ ኒሻን፣ የዳግማዊ ምኒልክ ኒሻን፣ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኒሽን ወዘተ. /ማኅተመ ሥላሴ፥1942፣683-688/ ጥቂቶቹ ሲሆኑ ለጥናቱ በተመረጡ መፃሕፍት ውስጥ ነገሥታቱ ተጠቅመውባቸዋል፡፡ «ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ራስ ወርቅ አስረውና ትልቁን የሰሎሞን ኮርዶን ኒሻን አድርገው በወርቅ ወምበር ተቀምጠው ለሕዝቡ ተገለፁና...» (መርስዔ ኀዘን፣1999፣148) ተፈሪ መኮንን የልጅ ኢያሱን ከዙፋን መውረድ እና የወ/ሮ ዘውዲቱን ንግሥተ ነገሥትነት እንዲሁም የራሳቸውን የአልጋ ወራሽነት ሹመት በተመለከተ አዋጅ ሲያስነግሩ የሰሎሞን ኮርዶን ኒሻንን አጥልቀው ነበር፡፡

የሰሎሞን ኒሻን የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት ሲሆን ኮርዶን አንዱ ነው፡፡ ኒሻኑ ለነገሥታትና ለነገሥታት ልጆች፣ የነገሥታትነት ዘር ላላቸው በሰላምም በጦርነትም ጊዜ በብዙ ሥፍራ ላይ ታላቅነታቸውና ታማኝነታቸው የተመሰከረላቸው መሳፍንቶች የሚሰጥ ነው (ማኅተመ ሥላሴ፣1961፣671)፡፡ኒሻኖቹ ከሽልማትነታቸው በተጨማሪ የሰሎሞናዊው ስርወ መንግሥት ገላጭ ትዕምርት ናቸው፡፡ ነገሥታቱ የሚመኩባቸው በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ የያዙት የነገደ ይሁዳ ቅርንጫፎች ዳዊትና ሰሎሞን ናቸው፡፡ የሚቀመጡበትን ዙፋን መንበረ ዳዊት ማለታቸው ኒሻኑን በሰሎሞን መሰየማቸው ፀሎቱ ሁሉ የዳዊት መዝሙር መሆኑ ከዚሁ ዕምነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ በጫኑበት ዕለት ያጠለቁት የሰሎሞን ኒሻን ምን እንደሚመስል እንመልከት፡-

*...መልኩ በቀኝ ንግሥተ ሳባ ወደ ሰሎሞን እንደቀረበች በግራ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር እንደዘረጋች ሆኖ ተስሎበታል፡፡ ከፍ ብሎ ሁለት አንበሶች የኢትዮጵያን*

*ንጉሥ ነገሥት ዘውድ እንደያዙ ሆነው የወርቁን ሠንሠለት እያይዘው ይታያሉ (ገዘኔ ከማሁ ፣684)።*

### 3.1.4.2 ልዩ ልዩ መገልገያ ቁሶች

በዚህ ንዑስ ክፍል የማነሳው ጥናቱ ባተኮረበት ዘመን ነገሥታቱም ሆኑ ተራው ማህበረሰብ በዕለት ተዕለት ኑሮው የተጠቀምባቸውን መገልገያ ቁሶች ነው። ቁሶቹ እጅግ በርካታ በመሆናቸው ጥቂቶቹን አንስቼ ለማለፍ እገደዳለሁ። ማህተም እያንዳንዱ ንጉሥ በስመ መንግሥቱ የሚያዘግጀውና ሃይልና ስልጣኑንን የሚገልፅበት አንዱ ቁስ ነው። ነገሥታቱ በሚለዋወጡዋቸው የፅሁፍ መልዕክቶች ላይ ማህተማቸውን ማሳረፍ ግዴታ አለባቸው። አለበለዚያ መልዕክቱ ተቀባይነት አይኖረውም። ነገሥታቱ ሥልጣን እንደያዙ ቀዳሚ ሥራቸው በስማቸው ማህተም ማስቀረፅ ነው። ማህተሙም / ከአፄ ቴዎድሮስ በቀር/ ሞዓ አንበሳ ዘእምነገዳ ይሁዳ የሚል ሀረግ እና የአንበሳና የመስቀል ምስል ያለበት ነው። ነገሥታቱ ሰሎሞናዊ ዘር ያላቸው፣ የይሁዳ ልጆች መሆናቸውን የሚያሳውቅ ነው።

ሌላው የነገሥታቱ መቀመጫ ዙፋን ነው። ዙፋን መንበረ ዳዊት በመባል ይጠራል። ዙፋን ከመቀመጫነቱ ባሻገር የሀይል መገለጫ ነው። ወንበሩ ላይ የተቀመጠ ሰው እንዲገዛና እንዲያስተዳድር ከፈጣሪ የተሰጠው ሃይል እንዳለው ይታመናል።

ነገሥታቱ በተለያየ ጊዜ በአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ አገር መንግስታት ጋር የተለዋወጧቸውን ገጸ በረከቶች በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ በስፋት እናገኛለን። ለምሳሌ ዐፄ ምኒልክ ለጣሊያኑ ንጉሥ ዑምቤርቶ የላኩት ስጦታ፡-

> *... ሰላሣ የሚሆኑ የዝሆን ጥርሶች ፣ያጌጡ ኮርቻዎች፣ የጠጅና የድቁስ ቀንዶች፣ ከበሮና የወርቅ መስቀል፣ አክሊል፣ ሙሉ ወታደራዊ የንጉሥ ልብስ፣ ጦርና ጋሻ፣ በወርቅ የተዘመዘመ የአንበሳና የነብር ቆዳ፣ የዝሆን ግልገል ፣በቅሎዎችና ፈረሶች ከሙሉ ዕቃዎች ጋር ይገኙበታል ( ተክለ ፃድቅ፣ 1985፣ 57)።*

ነገሥታቱም ይሁኑ መኳንንቱ የሚያበረክቷቸው ገጸ በረከቶች ከቁስነታቸው በተጨማሪ የግለሰቦቹን አስተሳሰብ ፣ዓላማ እንዲሁም ማንነት የሚጠቁሙ ናቸው። ዐፄ ምኒልክ ከጣሊያን መንግስት ጋር ለመመስረት የፈለጉትን መልካም ግንኙነትና ምኞት ለመግለፅ እና አገራቸው የምትገኝበትን የኑሮ ሁኔታ ለማሳየት ነበር ከላይ የተጠቀሱትን ቁሶች ለጣሊያኑ ንጉሥ የላኩት።

### 3.1.4.3 ምግብ

የምግብ አዘገጃጀት፣ የመመገቢያ ቁሶች እንዲሁም ምግብ ማህበረሰባዊ ደረጃን፣ የሰዎችን አመለካከትንና ፍልስፍናንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ከማሳየት አንፃር ይጠናል ። በዚህ ጥናት የምግብ ማዘጋጃው ቁስና የአዘጋጃጀት ስልቱን ማሳየት አይቻልም። ቢሆንም የዘመኑን መንፈስ ፤ የህብረተሰቡን ደረጃና አመለካከት ከማሳየት አንፃር ያለውን ፋይዳ ለማሳየት ተሞክሯል።

በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ ጎልቶ የሚታየው የምግብ ሥርዓት ግብር የተባለው ነው። ግብር የተባለበትን ምክንያት ማኅተመ ሥላሴ ሲገልጹ

*ንጉሡ ዘወትር መኳንንቱንና የቤት ልጁን ከልፍኝ ወይም ከልፍኝ አዳራሽ በታላላቅም በዓል ቀን ሰራዊቱን ካዳራሽ ያለማቋረጥና ያለ ማስተጓጎል በተለመደው ሰዓት የሚያበላ ነውና፤ ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ ምንም አስገባሪ ቢሆን ራሱም በበኩሉ ለህዝቡ የሚያስበውና የሚደክመው ከግብር ይቆጠራልና፤ በዚሁ ልማድ ግብር ተብሎ ሲነገር ይኖራል / 1942 ፣38/ብለዋል።*

ግብር በቤተመንግሥት በንግሥና በዓል፣ በልዩ ልዩ ክብረ በዓላትና ሹመት ሲኖር እንዲሁም በአዘቦት ቀን ይሰናዳል። በዘመኑ ንጉሡና መኳንንቱ ህዝቡን ለማቅረብ፤ ጦር ሰራዊቱን ለማደራጀት የሚጠቀሙበት አንዱና ዋንኛው ዘዴ ነበር።

ግብር ዓይነት አለው። ለነገሥታቱ፣ ለሹማምንቱ እንዲሁም ለተራው ህዝብ የሚዘጋጀው ምግብ፣ የመመገቢያ ሥፍራ እንዲሁም አቀማመጥ ደረጃ አለው። ከአንደኛው መሶብ የሚቀመጡ ልዑላን መሳፍንት ሲሆኑ ከሁለተኛው መሶብ የሚቀመጡት ደግሞ ራሶች ናቸው። በሶስተኛ ደረጃ የሚቀመጡ ቢትወደዶችና ንቡረ እዶች ሲሆኑ በዚህ መልኩ እንደ ማዕረግ ደረጃቸው ይቀመጣሉ። በዘመኑ የመሶብ አቀማመጡ ከነ እገሌ እነስ ተብሎ ቅራኔ ይነሳ ስለነበረ ለአቀማመጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረግ ነበር።

ጥናቱ ባተኮረባቸው መፃሕፍት ውስጥ ከሚገኙ በርካታ የግብር ሥርዓቶች አንዱን ለአብነት እንመልከት። ግብሩ የተዘጋጀው የንግሥት ዘውዲቱን የንግሥና በዓል ምክንያት በማድረግ ነበር።

*የማዕርግ ስፍራዎች በነበረ ቀለማቸው ተለይተው በሚታወቁ መጋረጃዎች በየደረጃው ተከፍለዋል። መጋረጃዎቹም ነጭ ሐር መጋረጃ፣ አረንጓዴ ሐር መጋረጃ፣ ኮች ሐር ባለወርቅ ጥብጣብ መጋረጃ፣ ሽሐኒ መጋረጃ እየተባሉ ተመድበዋል። ...ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በመንበረ ዳዊት ተቀምጠው በሚገኙበት*

*በነጩ ሐር መጋረጃ ውስጥ በመንበረ ዳዊት ቀኝ የራስ ወልደ ጊዮርጊስ መሶብ ቀረበ:: ደግሞም በቀኝና በግራ የአዋልደ መንግሥት ወይዛዝርት መሶብ እንደ ማዕረጋቸው ቀረበ:: ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ካሉበት ከአረንጓዴው መጋረጃ ውስጥ በመጀመሪያው መሶብ .... መብሉ መጠጡ በያይነቱ ለሁሉም ቀረበ:: ሥጋም ለመኳንንቱ በአስቶራጭ ተይዞ ቀረበላቸው (መርስዔ ኀዘን፣ 1999፣ 195)::*

በጥቅሱ እንደተመለከተው የግብር አቀማመጥ ሥርአቱ ደረጃን የተከተለ ሲሆን ትዕምርታዊም ነው:: የመጋረጃ አሰቃቀሉ የቤተክርስቲያን ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል:: ዙፋኑ ያለበት የመጀመሪያው መጋረጃ ግቢ እንደ መቅደስ ሁለተኛው እንደ ቅድስት የሶስተኛው መጋረጃ እንደ ቅኔ ማሕሌት ይቆጠራል /ማኅተመ ሥላሴ ፣ 1962 ፣39/::

በዘመኑ የቤተ መንግስት ግብር ልዩ ክብር ያለውና በረከት የሚገኝበት ተደርጎ ስለሚታሰብ ተራው ህዝብ ተጋፍቶ፤ ዱላውንና ርግጫውን ተቋቁሞ ያገኘውን በልቶ ይወጣል:: እግረመንገዱንም ለንጉሡ ያለውን ታማኝነትና አገልጋይነት ለማሳየት ቀረርቶ፣ ሽለላና ፉከራ ማስማት የተለመደ ነበር::

ግብር ከምግብ ሥርዓትነቱ በተጨማሪ ከፍተኛ የሆነ ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ነበረው:: ነገሥታቱ ሃይላቸውን ለማደራጀትና የአገዛዝ ሥርዓታቸውን ለማፅናት አይነተኛ /ቁልፍ/ መሳሪያ አድርገው ተጠቅመውበታል:: ለምሳሌ ምኒልክ በአድዋ ዘመቻ ወታደራቸው ደክሞት ሲቀመጥና ሲዘናጋ «... የምኒልክ ወሮታ፣ የጮማው የጠጁ ይህ ነውን እየተባባለ እንደገና እየተነሳ ይዋጋ ነበር» (ገብረ ሥላሴ፣1959 ፣262):: በማለት የግብሩን ፋይዳ ገልፀውታል::

ዐፄ ምኒልክ አስተዳደራቸው የተረጋጋና በህዝቡም ዘንድ ፍቅር አግኝተው እምዬ እስከመባል ከደረሱበት ምክንያት አንዱ በየጊዜው ህዝቡን ሰብስበው ግብር በማብላታቸው ነበር:: በዚህ ተግበራቸውም

*ቀድሞም ጠቢብ ነበር ሰሎሞን አባቱ*
*ምኒልክ ይበልጣል ሰው ይዞ መብላቱ*
*(ዝኒ ከማሁ፣207)*

ተብሎ ተገጥሞላቸዋል::

## 3.2 የፎክሎር ፋይዳ

በታሪክ መፃሕፍቱና በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ ከሚገኙት የፎክሎር ቅርፆች መካከል የተወሰኑት የታሪክ ተዋንያኑን ማንነት በማሳየት ፣ በታሪኩ ውስጥ ለተከሰቱ ግጭቶች

መንስዔና ውጤት በመሆን ፣በመረጃ ምንጭነት ፣የታሪኩን ጭብጥ በማጉላት፣እንዲሁም የዘመኑን መንፈስ በማሳየት ረገድ ላቅ ያለ ድርሻ አላቸው፡፡ ይሄው ፋይዳቸው በሚቀጥሉት ንዑስ ክፍሎች በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 3.2.1 የታሪክ ተዋንያንን ማንነት ማሳየት

በተመረጡት ሰባት መፃሕፍት ውስጥ ታሪክ ፀሀፊዎቹ ስለነገሥታቱ፣ ስለ መኳንንቱ ፣ ስለጀግኖቹ ወዘተ. ማንነት በተለይም ስለውስጣዊ ማንነታቸው ደግ ወይም ጨካኝ ከማለት ሌላ ብዙም የገለፁት ነገር ጎልቶ አይታይም፡፡ የታሪክ ተዋናያኑን ስሜታዊና ስነልቦናዊ ማንነት ምን ይመስላል? ርዕያቸው ምንድው? ፍልስፍናቸውስ ምንድነው? ለሚለው ምላሽ አፅንኦት አግኝቶ ጎልቶ እንዲወጣ ፎክሎር የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ የሥነቃል አንድ ዘርፍ የሆነው ቃል ግጥም የታሪክ ተዋንያኑን ውስጣዊና ውጫዊ ማንነት በማሳየት ረገድ የላቀ ድርሻ አበርክቷል፡፡

የተለያዩ ታሪክ ፀሀፊዎች ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ ውስጣዊ ማንነት በርግጠኝነት ለመግለፅ ሲቸገሩ ይታያል፡፡ ቴዎድሮስ አንድ ጊዜ ጨካኝ ፣አንድ ጊዜ ርህሩህ ወደ መጨረሻ ዘመናቸው ደግሞ እብድ እስከ መባል ደርሰው እንደነበር በየታሪክ መፃሕፍቱ ተገልፆ ይገኛል፡፡ ይህን መሰሉን ባህሪያቸውን የዘመኑ ሰው በቃል ግጥሙ አማካኝነት ከትውልድ ትውልድ አስተላልፎታል፡፡

*እሳት መጥቶ ከቋራ*
*ድፍን አበሻን ሊበላ*
*እንግሊዝ መጥቶ አጠፋው*
*ለእግዜር እግዜር አለው*

*(ተክለ ፃድቅ፣ 1981፣ 440)*

ገጣሚው ተለዋጭ ዘይቤን በመጠቀም ቴዎድሮስን ‹‹እሳት›› በማለት ገልጿቸዋል፡፡ ‹‹እሳት›› የሚለውን ደግሞ ‹‹ሊበላ›› በማለት የእሳትን ክፉ ጎን አንስቷል፡፡ እሳት ብርሃን በመስጠት፣ ምግብን በማብሰል፣ ብርድን በመግፈፍ በኩል ያለውን ትርጉም በመተው በአቃጣይነቱ፣ በአጥፊነቱ፣ በመአትነቱ ነው የተወሰደው፡፡ ከቋራ መጣ የተባለውም እሳት የዐፄ ቴዎድሮስን ባህሪ የሚገልፅ ሲሆን በየደረሱበት ሲገርፉ፣ ሲቆርጡ፣ ሲገድሉ፣ ሲያቃጥሉ፣ አገርና ሰውን ሲያጠፉ መኖራቸውን ያሳያል (ተክለ ፃድቅ፣ 1981፣247)፡፡ የታሪክ መፃሕፍቱ በተለምዶ አጠራር ‹‹ ጨካኝ›› ብቻ ብለው ቢያስቀምጡት ኖሮ

የጭካኔውን አይነትና መጠን በሚገባ አይገልፀውም ነበር። ቃል ግጥሙ ግን ባህሪያቸውን አጠንክሮ ገልፆታል። የመከራውን እሳት የሚያጠፋ በማስፈለጉም ግጥሙ

እንግሊዝ መጥቶ አጠፋው
ለእግዜር እግዜር አለው

በማለት በእሳት የተመሰሉትን ንጉሥ ሊያጠፉ (ሊገድሉ) እንግሊዞች መምጣታቸውን ይነግረናል። እንግሊዞቹ ‹‹ነፃ አውጪ›› ሆነው ተስለዋል። በሌላ በኩል

*በመቅደላ በኩል ጩኸት በረከተ*
*የሴቱን አናውቅም ወንዳንድ ሰው ሞተ*
*(ተክለ ፃድቅ፣ 1981፣439)*

የሚለው ደግሞ የቴዎድሮስን ሌላኛ ባህሪ የሚመሰክር ነው ‹‹ሴት›› የሚለው ቃል ባዮሎጂካል ፆታን የሚያመለክት ብቻ አይደለም። በጀኔራል ናፒየር የሚመራው የእንግሊዝ ጦር የመቅደላን በር ሰብሮ ወደ ውስጥ ሲገሰግስ ብዙ ሰው ሸሽቷልና ፣ብዙ ሰውም እጁን ለእንግሊዞች ሰጥቷልና፣ ብዙዎችም የእንግሊዝ አጋር ሆነዋልና ያንን ሁሉ ሃሞተ ፍስሱነት ለመግለፅ ነው ‹‹ሴት›› የሚለው የገባው። በጦርነቱ ሰበብ ብዙ ሰው ቢያልቅም ኩራት ያለው ሞት የሞተው ግን እሱ ብቻ ነው ለማለት ‹‹ወንድ›› ብሏቸዋል።

*ዳር እስከ ዳር ይዞ የገዛው ንጉሥ*
*እንዲህን ስሱ ነው (እንደዚህ ስስታም ነውን)*
*ጠበንጃ እሚጎርስ*
*(ተክለ ፃድቅ ፣1981፣ 439)*

ዐፄ ቴዎድሮስ ለጠላት እጄን አልሰጥም ብለው በገዛ ሽጉጣቸው እራሳቸውን ማጥፋታቸው በየታሪክ ድርሳናቱ ተፅፎ ይገኛል። ንጉሡ በመጨረሻ ሰዓት የወሰዱት እርምጃ ጀግንነታቸውን የሚገልፅ ተደርጎም ቀርቧል። ነገር ግን ከላይ የቀረበውን ቃል ግጥም ስንመረምረው የሚነገረን የቴዎድሮስ ውስጣዊ ማንነት አለ። «እንዲህን ስሱ ነው» የሚለውን ሀረግ ብናየው ንጉሡ ከሚታወቁበት የጭካኔና የጀግንነት ባህሪ በተቃራኒው ለካንስ የዋህ ናቸው፣ለካንስ ሆደ ባሻ ናቸው የሚል መልእክት እናገኛለን።

የታሪክ ዓላማ የሆነውን እውነት ማሳየት ወይም መንገር በመሆኑ ‹‹አሸነፈ››፣ ‹‹ተሸነፈ›› ወይም ‹‹ደመሰሰ›› ብሎ ያልፈዋል። ወይም በጥቅል አጠራሩ ‹‹ጀግና›› የሚለውን ቃል በመጠቀም የሰውዬውን ጀግነነት ይተርካል። የአሉላ አባነጋ የጀግንነት ተጋድሎ

በዝርው ትረካ ከቀረበ በኋላ ይበልጥ ጀግንነታቸውን አጉልቶ ለማሳየት የሚከተለው ቃል ግጥም ቀርቧል፡፡

*መብቱን ዮሐንስ ለአሉላ ቢሰጠው*
*እንደቀትር እሳት ቱርክን ገላመጠው*

*ጣሊያንም ወደቀ እያንቀጠቀጠው*
*አጭዶና ከምሮ እንደገብስ አሰጣው*
*(ተክለ ፃድቅ፣ 1982፣ 390)*

የተዋናዩ ሃይለኛነት በቀትር እሳት ተመስሏል፡፡ የቀትር እሳት ሲበዛ የሚያቃጥል፣ እንኳንስ ሰውነት ላይ አርፎ ወላፈኑም የሚፋጅ ነው፡፡ ለዚህም ነው ‹‹ገላመጠው›› መባሉ፡፡ አሉላ የማይደፈር፣ የማይያዝ፣ የማይሸነፍ ስለሆነ ነው ‹‹እሳት›› መባሉ፡፡ እሳት አካል የለውም፡፡ የድምፁን (የፉከራውን፣ የቀረርቶውን፣ የሽለላውን) አስፈሪነቱንና አስደንጋጭነቱን ደግሞ ከአንበሳ ግሳት ጋር በማነፃፀር አቅርበውታል፡፡ አሉላ ያደረሱትን ጥቃት ለመግለፅና የጀግንነታቸውን መጠን አጉልቶ ለማሳየትም አንድ ገበሬ አዝመራውን አጭዶ እንደሚከምረው ሁሉ አሉላም በጎራዴው ጣሊያኖችን እንደረፈረፋቸው እና እሬሳቸውም እንደተከመረና ከባድ ሽንፈትም እንደደረሰባቸው ቃል ግጥሙ ያስረዳል፡፡

ይህ ግጥም በታሪክ መፅሐፉ ውስጥ መኖሩ የተዋናዩ ስሜታዊና ሙያዊ ማንነት ጎላ ብሎ እንዲቀርብና አንባቢም ሰውዬውን በቅርብ ሆነው እንዲያዩት ያደርጋል፡፡ አሉላ ማንን ነው ያሸነፈው? በማን ላይ ነው የነገሠው? እንደ ገብስ የሚታጨዱት የሚከመሩትስ እነማን ናቸው? ብሎ ለሚጠይቅና የሰዎቹን ማንነትና ምንነት ለማወቅ ለሚሻ አንባቢ መልስ ይሰጣል፡፡

ቀጥሎ ያለው ቃል ግጥም የተዋናይቱን ሥነልቦናዊ ማንነት የሚያሳይ ነው፡፡ ግጥሙ በዘመኑ የነበረውን ሃይማኖታዊና ባህላዊ አመለካከት በአንዲት ሴት ሰበብነት አጉልቶ አቅርቧል፡፡ ግጥሙ እንዲህ ይላል፤

*ጎጃም የምትሄዱ እንደኔ የማትቀሩ*
*እርኩስ አርማ ሞተች ብላችሁ ንገሩ*
*(ተክለ ፃድቅ፣ 1982፣ 451)*

ደርቡሾች የጎጃሙን ንጉስ የተክለ ሃይማኖትን ጦር አሸንፈው ልጃቸውን ምንትዋብ አዳልን ይማርካሉ፡፡ ልጅቱም የሙስሊም ምግብ አልበላም ብላ በረሀብ መሞቷ በመፅሀፉ ተመልክቷል፡፡ ግጥሙ ከመሞቷ በፊት ተናግራው የነበረው ቃል እንደነበርም ተገልጿል፡፡ ግጥሙ የገጣሚዋን ሥነልቦናዊ ማንነት ይሰብካል፡፡ ‹‹እርኩስ እርማ›› የሚለው ሃረግ እርኩስ ነገርን እርም ብላ፣ የማልበላውን አልበላም ብላ፣ የማልሆነውን አልሆንም ብላ ሞተች ለማለት ነው፡፡ ነገሩን አንዲት ሴት (ተዋበች) ታቅርበው እንጂ ሃሳቡ ወይም ፍልስፍናው ግን የአንዲት ሴት ብቻ አይመስልም፡፡ በዘመኑ የነበሩት ገገር ዐፄ ዮሐንስም ቢሆኑ ከስልጣኔ ይልቅ ለሃይማኖት ተቆርቋሪና አጥባቂ ነበሩ በሃይማኖት የተነሳም ጦር ተማዝዋል በመጨረሻም ለህልፈታቸው መንስዔ ሆኗል (ተክለ ፃድቅ፣ 1982፣429)፡፡ ስለዚህ ሃሳቡ ታሪኩ በተጠራበት ዘመን ለነበሩ ክርስቲያኖች ወኪል የሚሆን ነው ለማለት ያስደፍራል ፡፡ ‹‹እርም›› ማለት እንደ ግለሰብ ጣጣ ሳይሆን እንደ ተቋም (የክርስትናው ሃሳብ) ሆኖ ነው የቀረበው፡፡

## 3.2.2 ለግጭት መንስዔና ውጤት መሆን

ለጥናቱ በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ ለተፈጠሩ ግጭቶች (የሀሳብ፣ የጦርነት ወዘተ.) ፎክሎር እንደ አንድ መንስዔና ውጤት በመሆን አገልግሏል፡፡ ለምሳሌ ዐፄ ቴዎድሮስን ለሽፍትነት ካነሳሷቸው ምክንያቶች አንዱ ሀገረሰባዊ ልማድ መሆኑ በተክለ ፃድቅ መፅሐፍ ተገልጿል (1981፣ 75-78)፡፡ በዘመኑ ኮሶ የጠጣ ሰው እራቱን ብሎ ወደ ወዳጅ ዘመዶቹ በላከ ጊዜ ክብሩን የሚመጥን ድግስ ይዘጋጅለታል፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስም ኮሶ ጠጥተው ወደ አማቻቸው ዘንድ እራቱን ብለው በላኩ ጊዜ የተላከላቸው የወርች ሥጋ ክብራቸውን ዝቅ የሚደርግ ነበር፡፡« ካሣ ለሽፍትነት ያበቃቸው ከዚህ ወራዳ መስተንግዶ ላይ ነው»፡፡(ዝኒ ከማሁ፣ 76) በማለት ተክለ ፃድቅ ለሽፍተነታቸው መንስዔ ከሆኑ ምክኒያቶች አንዱ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

ሥጋ ደረጃ አለው፡፡ በጣም ክብር ላለው ሽንጥ ፣ከዚያም ታናሽ ፣ ጎድን ተዳቢት የሚል ተዋረድ አለው፡፡ ወርች ሥጋም ከዚህ አንፃር ደረጃው ዝቅ ያለ የማይበስል ፣ የማይታኘክ ፈላጊ የሌለው ነው፡፡ እናም ከአማቻቸው ለአንተ የሚገባህ ይሄ ነው ተብሎ የተላከው ወርች ሥጋ ቀድሞም በካሳ ልብ ውስጥ ታፍኖ የቆየውን አመፅ ገንፍሎ እንዲወጣ ያደርገዋል፡፡ ከዛም«... እንግዲህ ሥጋይቱን እንደቆራረጥናት እኛም ልባችን ይቁረጥ... »(ዝኒ ከማሁ ፣78)፡፡ ብለው ወደ ሽፍትነት መግባታቸውን ከታሪክ መፅሐፉ እንረዳለን፡፡

ከዐፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ስልጣን ላይ የወጡት ንጉሠ ነገሥት ተክለ ጊዮርጊስ ወታደሬ እንደዚህ ጤፍ ቁጥር የለውም ሲሉ በስልቻ ሞልተው ለንጉሥ ዮሐንስ ይልካሉ። ዮሐንስም ወታደርህ እንደዚህ ቢበዛ በጥይት ቆልቼ ነው የምሰደው ሲሉ ጤፉን ቆልተው ይመልሱላቸዋል (ተክለ ፃድቅ፣ 1982፣ 27-28 ) ይህ አፈ ታሪክ ነው። አፈ ታሪኩ በሁለቱ ንጉሦች መሃል የነበረውን ውጥረት የሚያሳይና እንዲዋጉም የሚቀሰቅስ ነው። የግጭቱ ጡዘትም በንጉሥ ዮሐንስ አሸናፊነት (እንደረገበ) እንደተደመደመ እናያለን።

በዝብዝ ካሳ ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስን አሸንፌው ንጉሠ ነገሥትነታቸውን ቢያስከብሩም፣ በሌላ በኩል የሸዋው ንጉሥ ዐፄ ምኒልክ ከሰሎሞናዊው የዘር ሀረግ የምወለድ ብቸኛው የኢትዮጵያ የሥልጣን ወራሽ እና ገገር እኔ ነኝ በማለት እራሳቸውን «ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ» ብለው ተቀምጠዋል። በዚህም የተነሳ ከዐፄ ዮሐንስ ጋር ግጭት ውስጥ መግባታቸው አልቀረም። ምኒልክን አስጠርተው ስለጉዳዩ ይወያያሉ። በመጨረሻም ምኒልክ ‹‹ንጉሠ ነገሥት ሸዋ›› ተብለው እንዲጠሩ፣ ዐፄ ዮሐንስ ደግሞ ‹‹ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ›› እንዲሰኙ ይስማማሉ። የነገሩ አዝማሚያ ያላማራቸው የምኒልክ አሽከሮችም፡-

*ሲሆን ተክናንብ ሳይሆን አጣፋው*
*መታጠቅ (ማደግደግ) አይሆንም ለእንዳተ ያለሰው*
*(ተክለ ፃድቅ፣ 1985፣ 180)*

በማለት ዐፄ ምኒልክ በዐፄ ዮሐንስ መረታታቸውን እና ኩታቸውን አደግድገው ለዐፄ ዮሐንስ ማደራቸውን ተቃውመዋል። እንዳንተ ያለ መሪ የበታች ሆኖ ለሌላ ንጉሥ መገበር ማደግደግ አይገባውም። ካልሆነም በጦርነት ድል አድርገህ ሥልጣንህን አስመልስ የሚል መልዕክት በማስተላለፍ ዐፄ ምኒልክ የበታችነታቸውን እንዳይቀበሉ የቀሰቀሱበት ነው።

የታሪክ ጉዞው በቀጠለ መጠን የሁለቱ ነገሥታት የስልጣን ውክቢያ የበለጠ ያይላል። ሁለቱም በጥርጣሬ ስለሚተያዩ ለሚያደርጉት ነገር ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር። የኋላ ኋላ ዐፄ ዮሐንስ በብዙ አቅጣጫዎች በጦርነት መወጠራቸውን የተረዱት የሸዋው ንጉሥ ከእንግዲህስ ዝግጁ ነኝ ይላሉ። የንጉሥ ምኒልክን ሃሳብ የሚያውቁ አሽከሮችም፡-

*አይሆንም እንጂ ተሆነማ*
*ተመጋዞ ይሻላል ጉልማ*
*(ተክለ ፃድቅ፣ 1982፣ 463)*

በማለት ይፎክራሉ፡፡ ‹‹መጋዞ›› ዘመኑ በተጠራበት አገር (ሸዋ) ጭሰኛ ማለት ነው፡፡ ‹‹ጉልማ›› ደግሞ ቁራሽ የርስት መሬት ነው፡፡ ግጥሙ ምኒልክ የንጉሠ ነገሥቱ ጭሰኛ (አገልጋይ) የሚሆኑበት ጊዜ ማብቃቱን የሚጠቁም ነው፡፡

ሰምኒልክ አገዛዝ አስጊና እንቅፋት ከነበሩት ሰዎች አንዱ አቶ በዛብህ (በዙ አባ ድከር) ነበሩ፡፡ በጀግንነታቸውም በዐፄ ቴዎድሮስ ዘንድ ዝናን ያተረፉ ናቸው፡፡ ሰምኒልክም አልገዛም ብለው ሸፍተው ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ በእርቅ ሊገቡ ችለዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ በሁለቱ መካከል ተፈጥሮ የነበረውን ቅራኔ ለመቀስቀስና ለማጋጋል እንዲሁም ሁለቱ በጠላትነት እንዲቀጥሉ ለማድረግ ህዝቡ በግጥምና በሽለላ እንዲህ ይል ነበር፡፡

*መቼ ኮረብታው መች አፍቀራ ነው*
*መቼ ፈረሱ መች በራ ነው*
*መቼ መሣሪያው መች ጠብንጃው ነው*
*በዙ አባ ድከር እሱን ያኮራው*
*ሐሞቱ እንጂ ነው ባንድ የተሠራው*
*(ተክለ ፃድቅ፣ 1982፣73)*

የበዛብህን ሀሞተ መራራነት ምኒልክም አይክዱትም፡፡ እናም እንደዚህ አይነቱ ሰው ጤና ስለማይሰጥ ወደ እርምጃ ያመራሉ፡፡ አቶ በዛብህ እንዲያዙ ያደርጋሉ፡፡ በተያዙበትም ወቅት ሽጉጣቸው ጥይት ጎርሶ በመገኘቱ ሞት ይፈረድባቸዋል፡፡ አላይ እንደተገለፀው ቃል ግጥሙ በሁለቱ ሰዎች መካከል ተፈጠረውን ግጭት በማክረር በመጨረሻም በሞት እንዲደመደም የራሱን ድርሻ አበርክቷል፡፡

ሌላው አቤቶ ኢያሱ ከሥልጣናቸው እንዲወርዱ በዋናነት ከቀረቡት ምክንያቶች አንዱ ሃይማኖት ቀይረዋል (ሰልመዋል) የሚል ነበር፡፡ በአቤቶ ኢያሱ ላይ ሃይማኖታቸውን ስለመቀየራቸው ከቀረበው ማስረጃ አንዱ አለባበሳቸው ነበር፡፡ «...ቀይ ከፋይ ባለወርቅ ሰገጥ ካባ ለብሰው በወርቅ ኮርቻ እና በወርቅ መጣምር...» (መርስዔ ኀዘን፣1999፣ 134)፡፡ አቤቶ ኢያሱ የደመራን በዓል በጃንሜዳ ባከበሩበት ዕለት ነበር ቀይ ካባ የለበሱት፡፡ ቀይ ካባ መልበስ በዘመኑ ለንጉሥ የተገባ ስላልነበረና የእስልምናም መለያ ስለነበር ሁኔታው አድማ ቀስቃሾቹ ቀድሞ የነበራቸውን ጥርጣሬ በማጉላት ተቃውሞውን ያጠናክረዋል ፡፡ በዚህ መልኩ የኢያሱ አለባበስ በኢያሱና በህዝቡ መካከል የነበረውን ግጭት እንዲካረር ማድረጉ በመርስዔ ኀዘን መፅሐፍ ተገልጿል (1999፣13)፡፡

## 3.2.3 የዘመኑን መንፈስ ማሳየት

በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ ያሉት አንዳንድ የፎክሎር ቅርፆች መፃሕፍቱ የሚጠሩትን ዘመን መንፈስ ከማሳየት አንፃርም ላቅ ያለ ሚና ተጫውተዋል። ታሪኩ እነስ ያደረገውን እውነት ተለቅ፣ታሪኩ ሸሽግ ያደረገውን ምስጢር ገለጥ! ታሪኩ ደበስበስ አድርጎ ያለፈውን ጉዳይ ገለጥለጥ እያደረጉ የታሪኩን ወይም የታሪኮቹን ጭብጦች አጉልተዋል። ከዚህ በታች በቀረቡት ንዑስ ርዕሶች ስር የተጠቀሱትም የዘመኑን መንፈስ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ እውነታዎችን ከማሳየት ፋይዳቸው በተጨማሪ ጭብጥም የመሆን አቅም ያላቸው ናቸው።

### 3.2.3.1 ፖለቲካዊ ሁኔታ

በዚህ ክፍል ውስጥ ሁለት ንዑሳን ርዕሶች አሉ። እነዚህም ፎክሎር የስልጣን መሳሪያና የድጋፍና ተቃውሞ መግለጫ ሲሆን የሚሉት ናቸው።

#### 3.2.3.1.1 የስልጣን መሳሪያ ሲሆን

በሰባቱም የታሪክ መፃሕፍት ውስጥ ዋናው የስልጣን ምንጭ አፈ ታሪክ ነው። ቀደም ብለን በ 3.1.1.2 እንደዚሁም ወደፊት በምዕራፍ አራት እንደምናየው አፈ ታሪክ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ አለው። ከአክሱም ዘመነ መንግስት ጀምሮ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከስልጣን እስከሚወርዱበት ድረስ ያለው የኢትዮጵያ ታሪክ በሰሎሞናዊ ስርወ መንግሥት አፈ ታሪክ የሚመራ ነው። የዛጉዌ ነገስታትና ዐፄ ቴዎድሮስ ‹‹ ያለቦታቸው›› የተባሉትም የዚህ ቤተሰብ አባላት አይደሉም በሚል ነው። ‹‹ዘመነ መሳፍንት›› በሚባለው ዘመን ውስጥ በየክልሉና በየአውራጃው በራሳቸው ፈቃድ ለነገሡት ራሶች ምክንያቱ ይኸው አፈ ታሪክ ነው። ራሶቹ ብንነግሥም የሰሎሞን ዘር የለንምና ማን ይቀበለናል ብለው ስለሚያስቡ ለይስሙላ ‹‹ንጉሠ ነገሥት›› ብለው የዚያ ቤተሰብ ተጠሪ የሆነን ሰው አንግሠዋል።

### 3.2.3.1.2 ፖለቲካዊ ድጋፍና ተቃውሞ መግለጫ ሲሆን

ፎክሎር የየዘመናቱን ፖሊቲካዊ አቅዋም ለማሳየት አይነተኛ ስልት ነው። መልካሙን በግነት በማሞገስ ያመስግናል። መጥፎውን ምፀት ወይም አሽሙር ባዘለ ወቀሳ ይተቻል። ሙገሳዎቹ ወይም ወቀሳዎቹ የተመሰገነውን ወይም የተወቀሰውን ሰው ማንነትና ተግባር ከመግለጽ አልፈው ሰውየው የኖረበትን ዘመን ያሳያሉ። ለምሳሌ

*አባባ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥቱ*
*እንኳን የሰውን ልጅ አውሬን የገዙቱ*
*ልጅን ያለ አንቀልባ ያሳደግሁበት*
*ቤቱን ያለመዝጊያ የተኛሁበት*
*እንኳን በቁመናው ዛሬ እንኳን በሙቱ*
*በምኒልክ ሲባል ይረጋል መሬቱ*
*(መርስዔ ኀዘን ፣1999፣ 211)*

ዐፄው ሲሞቱ አንዲት አልቃሽ ደግነታቸውን፣ አባትነታቸውን፣ ሰላም ወዳድነታቸውንና ተከባሪነታቸውን በማንሳት ያንጎራጎረችው ነው። የሀዘን እንጉርጉሮው ከላይ ሲታይ ስለ ዐፄ ምኒልክ የሚናገር ቢሆንም ግጥሙ ግን ምኒልክ የገዙበትንም ዘመን የሚወክል ነው። የሰላምና መረጋጋት እንዲሁም የአንድነት ሃሳቦች በዐፄ ቴዎድሮስ ቢጀመሩም፣ ዘለቄታ ያገኙት ግን በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ነው። እላይ የቀረበው ግጥምም ይህን ሰላምና መረጋጋት ‹‹አውሬን የገዙቱ››፥ ‹‹ቤቱን ያለ መዝጊያ›› እና ‹‹ልጅን ያለ አንቀልባ›› በሚሉት ሃረጎች ተገልጿል። ቤት ሳይዘጋ የሚታደረው አገሩ ምን ያህል ሰላማዊ ቢሆን ነው? ገጣሚዋ ‹‹በምኒልክ ሲባል ይረጋል መሬቱ›› ስትልም የህዝቡን ለንጉሡ ታዛዥ መሆን በተለዋጭ ዘይቤ ተገልጿል።

*ብንታረቅም አሁን በካሣ ነው*
*ሰጥተውኛልና ሥላሴ ፈርደው*
*እህሉም በቅሎ እንዳይጠፋ*
*ዝናመ ምሕረት ካሣን*
*በኢትዮጵያ አዘነምኸው*
*(ተክለ ፃድቅ፣1981 ፣142)*

ይህኛው ውዳሴ ደግሞ ዐፄ ቴዎድሮስ «ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ›› ተብለው በደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሚነግሡ በአንድ ደብተራ የተገጠመ ነው። በግጥሙ ውስጥ እንደ ‹‹ካሣ››፣ ‹‹ዝናም›› እና ‹‹ፈርደው›› ያሉትን ቃላት ፍካሬያዊ ትርጉም ብንመረምር ግጥሙ ስለ ቴዎድሮስ ብቻ ሳይሆን ቴዎድሮስ ስለነበሩበት ዘመንም ጭምር መሆኑን እንረዳለን። ‹‹ካሣ›› (በፍካሬያዊ ትርጉም) ካለ በደል፣ በደል ካለ ደግሞ በዳይና ተበዳይ አለ ማለት ነው። በደሉ በዘመነ መሳፍንት የተፈፀሙ ‹‹ወንጀሎች›› ናቸው። በዳዮቹ የዚህ ዘመን እንደራሴ የሆኑት መሳፍንትና መኳንንት ናቸው። ተበዳዩ ደግሞ በደብተራው ወገን የተሰለፉት ህዝቦች ናቸው። ዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያ በጎን ተከፋፍላ የኖረችበት ወቅት ነው። ራሶች በማን አለብኝነት ያሻቸውን የሰሩበት፣ የጠሉትን አልይህ ያሉበት፣ ለወደዱት አገር ቆንጥረው የሰጡበት ዘመን ነው። ከዚህ በተጨማሪም ስርአት አልበኝነት የሰፈነበት፣ ህግና ደንብ የሌለበት ነበር። በዚሁ መፅሐፍ በገጽ 100 ላይ የቀረበው ‹‹እነሱ ራሳቸው በወግ ሳይሆኑ›› የሚለው ቀልድ ዘመነ መሳፍንት በሚገባ ይገልጸዋል። ዘመኑ ወግ አልባ፣ ስርአት አልባ፣ ለዛ የለሽ ፣ ፍቅር የለሽ፣ ወዘተ. ተብሎ ሊገለጽ ይችላል።

ደብተራው ይህን ሁሉ አስቦ ነው ቴዎድሮስን ‹‹ካሣ›› እና ‹‹ዝናመ ምህረት›› ያላቸው። ኢየሱስ ራሱን ካሳ አድርጎ እንደሰጠ ሁሉ ቴዎድሮስም መሳፍንቱ ለበደሉት ሁሉ ራሳቸውን ካሣ አድርገው ሰጡ። በዚህ ስልት የዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን ከዘመነ መሳፍንት ዘመን የተሻለ መሆኑ ተወስቷል።

የውዳሴውን ያህል በነገስታቱ ላይ የተጣሉ የተቃውሞ ግጥሞችም ከነገሥታቱ በተጨማሪ ነገሥታቱ የወከሏቸውን ዘመናት የሚያሳዩ ናቸው። ለምሳሌ

*አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ*
*እንደዚህ አንድዶ ለብልቦ ይፍጃችሁ*

*(ተክለ ፃድቅ፣1981 ፣245)*

በማለት ምንትዋብ የተባለች ሴት ብሶትና ተቃውሞዋን ገልፃለች። ዐፄ ቴዎድሮስ ለንግሥና የሚያበቃ የሰሎሞናዊው የዘር ሃረግ የላቸውም ስለሚባል እና ለእናት ለአባታቸው ብቸኛ ልጅ በመሆናቸውን «አንድ እግር» ስትል ገልፃቸዋለች። ቀጥላም በበርበሬ ትመስላቸዋለች። አቃጣይና አስለቃሽ ለማለት። የቴዎድሮስን ብቸኝነቱን እየወቃችሁ እንዴት ማስወገድ ያቅታችኋል? የሚል ጥያቄ ባዘለ ግጥሟ ለነገሡ ያላትን ጥላቻ ገልፃለች። በርግጥ የግጥሙ

መልዕክት የምንትዋብ ብቻ ሳይሆን በዘመኑ በቴዎድሮስ አገዛዝ የተንገፈገፈውን ህዝብም የሚወክል ነው ማለት ይቻላል።

### 3.2.3.2 ማህበራዊ ሁኔታ

ጥናቱ ባተኮረባቸው መፃሕፍት ውስጥ የተጠቀሰውን ዘመን ማህበራዊ ገፅታ በማሳየት ረገድ አንዳንድ የፎክሎር ቅርፆች የበኩላቸውን ድርሻ አበርክተዋል። የተለያዩ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን ለምሳሌ ትምህርት፣ ሃይማኖት፣ የስልጣኔ መስፋፋት የመሳሰሉትን ማህበራዊ ጉዳዮች ያሳያሉ ።

ዐፄ ምኒልክ ሥልጣኔን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ረገድ ግንባር ቀደም መሪ ናቸው። በእርሳቸው ዘመን የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ለምሳሌ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ ባንክ ፣ሥልክ ፣ መኪና፣ ባቡር የመሳሰሉት የተከፈቱና ግልጋሎት መስጠት የጀመሩ ሲሆን ንጉሡም ይህን በማድረጋቸው ይወደሱ ነበር።

*ባቡሩም ተጫነ ስልክም ተናገረ*
*ይኼ በማን ጊዜ ተደርጎ ነበረ*
*ምኒልክ ነብይ ነው ሆዴ ጠረጠረ*
*የሐበሻው ንጉሥ ምኒልክ ነብይ ነህ*
*ኃላፊውን ትተህ መጪውን ታውቃለህ*

*(ተክለ ፃድቅ ፣1985 ፣598)*

ከዐፄ ምኒልክ በፊት የነበሩት ነገሥታት ሥልጣኔን ቢፈልጉም (በተለይ ዐፄ ቴዎድሮስ) ሳያገኙት በማለፋቸው ገጣሚው «ይኼ በማን ጊዜ ተደርጎ ነበረ» በማለት አወድሷቸዋል። በአገሪቱ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቀውን የስልክና የባቡር ግልጋሎት በማስጀመራቸውም ህዝቡ ከመልአክ ጋር በማነፃፀር ስሜቱን ገልጿል። ቃል ግጥሙ በዝርው የቀረበውን ሃሳብ በማጎልበት የዘመኑን ማህበራዊ እንቅስቃሴ ያሳያል።

ሌላው ከማህበራዊ ጠንቆች አንዱ የሆነው ሙስና በዐፄ ምኒልክ ዘመን የነበረውን ገፅታ የሚሳይ ነው። አፈ ንጉስ ነሲቡ መስቀሎ በዐፄ ምኒልክ ዘመን ዳኛ ነበሩ። በሙያቸው የተከበሩ ቢሆኑም ጉቦኛ ነበሩ። አንድ ቀን ሁለት ሰዎች በይፍረዱልኝ ስሞታ አቤት ሊሉ ወደኚህ ሰው ይሄዳሉ። ሰውየው ጉበኛ መሆናቸውን ያወቁት ሁለት ባለጉዳዮች አንዱ ጥሬ ብር፣ ሌላው ደግሞ በቅሎ ይሰጣል። በኋላ ላይ አፈ ንጉሡ በቅሎ ለሰጠው

ሲፈርዱ የተበሳጨው ሌላው ባለጉዳይ ‹‹ምነዋ ጌታዬ ብር ብዬ መጥቼ ነገሬም አልነበረም ወይ?›› ይላቸዋል፡፡ እሳቸውም በማሾፍ አይነት እንዲህ አሉት «አንተ ብር ብለህ ብትመጣ እሱ (ባለ በቅሎው) መጭ ብሎ ቀደመሃ›› (መርስዔ ኀዘን፣1999፣40)፡፡

በዚህ ታሪክ መፅሐፍ ውስጥ ስለዘመኑ ሰዎች ኢኮኖሚያዊ መጠን (ደረጃ) እና ማህበራዊ ተግባቦት እንዲህ ነው ተብሎ ባይቀርብም የፎክሎር ቅርፆቹ በታሪኩ ሂደት ጣልቃ እየገቡ ዘመኑን አሳይተዋል፡፡ ነገሥታቱ የእግዚአብሔር እንደራሴዎች ናቸው ተብሎ በሚታመንበት ዘመን ጉቦኝነት ነበር ለማለት የቸገራቸው የታሪክ ፀሀፊዎች አልፎ አልፎ ጣል በሚያደርጓቸው የፎክሎር ቅርፆች ዘመኑን በመጠኑም ቢሆን እንድናይ አድርገዋል፡፡

በአንፃሩ ዐፄ ዮሐንስ ከሥልጣኔ ይልቅ ለሃይማኖት ተቆርቋሪ ነበሩ፡፡ ዋና ፍላጎታቸውም ሁሉም ክርስቲያን በተዋሕዶ እንዲያምን ፣ ሁሉም እስላም በክርስትና እንዲጠመቅ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት ሙስሊሙ ሁሉ ወደየአቅራቢያው ቤተክርስቲያን እየሄደ እንዲቆርብ አስገድደዋል፡፡ በዘመኑ ይፈፀም የነበረውን ሃይማኖታዊ ጫና በመቃወመው አንድ የዕስልምና ዕምነት ተከታይም ፡-

*ታናሽ ታላቅ በላን ከርካ አደባባይ*
*ክርስቲያን ሆይ አለልብ ሥጋ ይጣፍጣል ወይ*
*(ተክለ ፃድቅ ፣1982 ፣200)*

በማለት ሃሳቡን ገልጿል፡፡ ቃል ግጥሙ በዘመኑ የነበረውን ሃይማኖታዊ ገፅታ የሚያሳይ ሲሆን «አለልብ ሥጋ ይጣፍጣል ወይ» ማለቱም ህዝቡ አለፍላጎቱ ተገዶ ዕምነቱን በመቀየሩ በሰላም ተገዝቶ ሊኖር እንደማይችል የሚጠቁም ነው፡፡ በወቅቱ «ለመኖር» ሲሉ ዕምነታቸውን የቀየሩ ሙስሊሞች ቢኖሩም ገሚሶቹ ወደ ጎረቤት ሀገር ሸሽተው በመሄድ በመጨረሻ በዐፄ ዮሐንስ ላይ በተከፈተው ጦርነት ተባባሪ በመሆን ለህልፈት ዳርገዋቸዋል፡፡ በዚሁ ዘመን ዐፄ ዮሐንስ «ትምባሆ ሲጠጣ የተገኘ አፍንጫውና መላሱ ይቆረጥ» (ገዚ ከማሁ ፣200) የሚል አዋጅ አስነግረው ነበር፡፡ አዋጁን ተላልፈው በተገኙት ላይም ቅጣቱ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ቃል ግጥሙም ሆነ አዋጁ በዐፄ ዮሐንስ ዘመን ሰፍኖ የነበረውን የማህበራዊ ህይወት ጫና የሚያሳዩ ናቸው፡፡

### 3.2.3.3 ባህላዊ ፋይዳ

የፎክሎር ቅርፆች የበቀሉበትን ዘመንና ቦታ ባህላዊ ሃሳብና ድርጊት ያንፀባርቃሉ። በታሪክ መፃሕፍቱና በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ ያሉት የፎክሎር ቅርፆች ለዚህ አባባል ምስክር መሆን ይችላሉ። ለዚህ አይነት ተግባር የዋሉት ብዙ ቢሆኑም ባህልን የማሳየት አቅማቸው ከፍተኛ የሆኑትን ሁለት ነጥቦች ጠቅሼ አሳያለሁ።

በተለምዶ አጠራር ‹‹ሸፈተ›› ሲባል ‹‹ጠፋ››፥ ‹‹ከዳ›› ወይም ከቃል ወጣ ህግ ተላለፈ ማለት ነው። ቃሉ አሉታዊ ትርጉም አለው። ጥናቱ ባተኮረባቸው መፃሕፍት ውስጥ ያለው ፍቺ ግን ከዚህ የተለየ ነው። መሸፈት ጀግንነት ነው። አንድ ሰው ከሸፈተ ተጠርቶ ይሾማል እንጂ አይቀጣም። ለዚህ የቀረበው ምክንያት ደግሞ ሽፍትነት የጀግንነት መገለጫ ተደርጎ መቆጠሩ ነው። ሽፍትነት የጎበዝ ሙያ ነው። ተክለ ፃድቅ ስለዚህ ጉዳይ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ፤

> *በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሽፍትነት ስራ በተለይ በዚያን ዘመን እንደ ወንድነት ሙያ እንጂ እንደ ወንጀል እምብዛም ስለማይቆጠር አንዱ መኮንን በደጅ ጥናትና በህጋዊ መንገድ ያላገኘውን የጋብቻ ወይም የሹመት መብት ብዙ ጊዜ ከሽፍትነት በኋላ ያገኘዋል።*
>
> (ተክለ ፃድቅ፣ 1981 ፣ 63)

ለዚህም እንደ አብነት የምናነሳው የዐፄ ቴዎድሮስን መሸፈት ነው። ልጅ ካሣ የቋራን ሰው ሁሉ ይዘው በራስ ዐሊና በእቴጌ መነን ላይ በሸፈቱ ጊዜ ያዘው፣ እነቀው፣ግደለው አልተባሉም። ከዚያ ይልቅ ‹‹ይህን መሳይ ጎበዝ መኮንን›› ድረን ሸልመን እናባብለው ነበር የተባሉት። ዐፄ ምኒልክም በተደጋጋሚ እየሸፈተ ያስቸገራቸውን ራስ በዛብህን አባብለው፣ ድረውና ሸልመው ሲለቁት አይተናል። ይህ የሚያሳየን ነገር በዘመኑ የነበረው ባህላዊ አስተሳሰብ ነው። ለሽፍትነት የሚሰጠው ባህላዊ ትርጉም ዛሬ እንዳለው አይነት አለመሆኑ ነው። ሽፍትነትና እሱን ተከትለው የሚመጡ እንደ ዝርፊያና ግድያ አይነቶቹ የወንድነት ተምሳሌቶች ናቸው። ዘረፋና ብዝበዛ በመንግሥት ወይም በንጉሥ ትዕዛዝ ሲሆኑ አያስከፋም።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ባህላዊ አስተሳሰብ እጅና እግርን የመቁረጥ ‹‹ጀግንነት›› ነው። ዐፄ ቴዎድሮስ ከሸፍቶች ጋር ይማማላሉ። ሰዎቹ ግን መሃላቸውን ሽረው

የራስህ ጉዳይ አንተም ለራስህ እወቅ እኛም ለራሳችን እናውቃለን ሲሏቸው ይቆጣሉ። ከዚያስ? «ጎራዴ መዘው ያዘው ባሉ ጊዜ ሰባ ጋሻ የሚሆኑት ሸሹ። ሰባት ተያዙ። ልጅ ካሳም ተጉልበታቸው ቆረጧቸው። የልጅ ካሳ የመጀመሪያ ድል ያደረጉት ይህ ነው» (አስፋው፣1902፣ 7)።

ደራሲው ድርጊቱን የገለፁት በማድነቅ ነው። ካሣን ጀግና ለማለት የእጅና የእግር ቆረጣውን በማስረጃነት አቅርቧል ። በሌላ ጊዜም ካሣ ከደረስጌ ሲመለሱ ያለ እሳቸው ፈቃድ ድሃውን ገንዘብ የዘረፉ ወታደሮቻቸውን ይዘው ‹‹ አንዳንድ እጃቸውን አንዳንድ እግራቸውን ቆረጧቸው›› (ዝኒ ከማሁ፣ 19) የሚል እናገኛለን። ድርጊቱ ፍርድም ጭምር ነው። በቴዎድሮስ እና በምኒልክ ዜና መዋዕል የምናየው ይህንኑ ተመሳሳይ ባህል ነው።

### 3.2.4 ፎክሎር ለታሪክ መረጃ ምንጭነት

አፈ ታሪክ፣ቃል ግጥም፣ ጥንታዊ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች፣ አሮጌ ሕንፃዎችና ፍርስራሾች፣ ሐውልቶች እና የመሳሰሉት የፎክሎር ቅርፆች ለታሪክ ተመራማሪዎች እና ፀሀፊዎች በቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት ያገለግላሉ።

ለጥናቱ በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ እነዚህ የመረጃ ምንጮች ከባሕሩ የኢትዮጵያ ታሪክ በስተቀር በጥቅም ላይ ውለዋል። ከፎክሎር ቅርፆቹ በተለይም አፈ ታሪክ በመፃሕፍቱ ውስጥ በመረጃ ምንጭነት በስፋት አገልግሏል። ለምሳሌ ለዐፄ ቴዎድሮስ ፣ለዐፄ ምኒልክ ፣ለዐፄ ኃይለ ሥላሴ እና ለሌሎቹ ነገስታት የንግስና መንስዔ አፈ ታሪክ እንደሆን በምንጭነት ተጠቀሷል። በተለይም በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ ፀሀፊዎቹ በዋና የመረጃ ምንጭነት የተጠቀሙት አፈ ታሪክን ነው። በ 3.1.1.2 እና በምዕራፍ አራት ውስጥ መመልከት ይቻላል።

በተጨማሪ ታሪክ ፀሀፊዎቹ ሙገሳና ተቃውሞን ገላጭ የሆኑ ቃል ግጥሞችን አንዲት አልቃሽ ወይም አዝማሪ እንዲህ አለች/አለ በማለት በመረጃ ምንጭነት ተጠቅመውባቸው እናገኛለን። ለምሳሌ መርስዔ ኅዘን የንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ሞት በአቤቶ ኢያሱ ዘመን ተደብቆ መኖሩን ገልፀው ወሬው ግን በህዝቡ ዘንድ ቀስ በቀስ መዛመቱን ለማሳየት አንድ የምንጃር ገበሬ በጤፍ ውቂያ ላይ የገጠመውን ግጥም በመረጃነት ተጠቅመውበታል። ግጥሙም እንዲህ የሚል ነበር፡-

*እምዬ ምኒልክ ገንዘብ ስጠኝ ብዬ አላስቸግርህም*
*እምና ነበር እንጂ ዘንድሮስ የለህም*
***(1999፣111)***

ተክለ ፃድቅም ቃል ግጥሞችን እና አፈ ታሪኮችን በመረጃ ምንጭነት በሦስቱም መፃሕፍት ውስጥ ተጠቅመዋል። ዐፄ ቴዎድሮስ በመጨረሻ የአገዛዝ ዘመናቸው የቅጣት በትራቸው እየከፋ መሄዱንና ህዝቡም በጣም መማረሩን ለማሳየት በወቅቱ ይነገሩ ከነበሩ አፈ ታሪኮች አንዱን በመረጃነት እንዴት እንደተጠቀሙ ቀጥሎ ከቀረበው ጥቅስ እንመልከት።

> *ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ወታደር ከባልደረቦቹ ተለይቶ አንድ ፈረስና ሁለት የተጫኑ አህዮች ይዞ እየነዳ በሚሄድበት ጊዜ ፈረስ ለብቻው ደክሞት እየወደቀ ከአህዮቹም አንደኛው ጭነቱን እየጣለበት ወታደሩ የሚያደርገው ጠፍቶት ወደ አምላኩ በሐዘን ሲያማርር ቴዎድሮስ ከኋላው ደርሰው «ለምን ፈጣሪህን ታማርረዋለህ?«ይህን ንጉሥ ግደልልኝ እንዳርፍ ብለህ ለምነው እንጂ» ቢሉት ወታደሩ መልሶ «ጃንሆይ አልሰማኝ አለ እንጂ እኔስ ለመንሁት አላቸው»። እርሳቸውም «እውነትህን ነው» ብለው ዝም ብለውት ሄዱ።(1981፣247)*

የአፈ ታሪኩን እውነትነት ማረጋገጥ ባይቻልም ፀሀፊው በዘመኑ የነበረውን ብሶት ለማሳየት እንዲሁም ዐፄ ቴዎድሮስ ወታደሩን በዝምታ በማለፋቸው ርህሩህ እና መሐሪነታቸውን ለማሳየት ተጠቅመውበታል።

በርግጥ እነዚህን መሰል የፎክሎር ቅርፆች ትክክለኛ ማስረጃ ሊቀርብላቸው ስለማይችል የተአማኒነት ጥያቄ ያስነሳሉ። ለዚህም ነው ታሪክ ተመራማሪው እነዚህን መሰል የመረጃ ምንጮች ሲጠቀም ከሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች ጋር በማመሳከር እንዲጠቀም የሚመከረው።

## 4.1 በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ቅርፃች

በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ ካሉት የፎክሎር ቅርፃች ጎልተው የሚታዩት አፈ ታሪኮች ናቸው:: የዜና መዋዕሎቹን ባህሪ ተከትለው የገቡት እነዚህ አፈ ታሪኮች የነገስታቱን ጥቅም የሚያስጠብቁ ናቸው። ለመሆኑ አፈ ታሪክ ምንድ ነው? አፈ ታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ የስነቃል አይነት ነው። አፈ ታሪክ ማረጋገጫ ወይም ማስረጃ የለውም። ነገር ግን ማስረጃ ማቅረብ ስለማይቻል ተብሎ ጠቅላላውን ውሸት ወይም ፈጠራ ነው ሊባልም አይችልም። የሆነ ሆኖ የእኔ ትኩረት የአፈ ታሪኩን እውነተኛነት ወይም ተአማኒነት ማረጋገጥ ሳይሆን ደራሲዎች አፈ ታሪክን ለምን ፋይዳ ተጠቀሙበት የሚለውን መመርመር ነው::

በዐፄ ምኒልክ ዜና መዋዕል ውስጥ በተደጋጋሚ የሚነሳው የሰሎሞን ሳባ አፈ ታሪክ ነው:: አፈ ታሪኩ ከክብረ ነገሥቱ አፈ ታሪክ የተወሰደ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ይህን ለምን እንዳልኩኝ ላሳያለሁ። ክብረ ነገሥቱ እንደሚተርከው፣ ያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች ነበሩት። ሊሞት ሲል አስራሁለቱንም ጠርቶ ወደፊት ሊገጥማቸው የሚችለውን እጣፈንታ ይነግራቸዋል። በዚህ መሰረት መንግሥትን (ስልጣንን) ለይሁዳ ይሰጠዋል። የይሁዳ መንግሥት እንደ አንበሳ አሸናፊ ትሆን ዘንድ ይባርክለታል። በዚህም ይሁዳ ይነግሣል። ሲያረጅም ለልጁ ለፋሬስ ያወርሰዋል። ከዚያም ፋሬስ ለኤሮስም ኤሮስም ለአርኒ፣ አርኒ ለአራም... እያለ ስልጣን ከአባት ወደ ልጅ እየተወራረሰ እሴይ ላይ ይደርሳል። እሴይም ለዳዊት ዳዊት ደግሞ ለሰሎሞን ያወርሳል (ስርግው፣ 1994፣ 9) ።

በዚህ ጊዜ ነው የክብረ ነገሥቱ አፈ ታሪክ ጥንስስ የሆነው የንግሥት ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ፣ ከንጉሥ ሰሎሞን መፅነስና የቀዳማዊ ምኒልክ መወለድ የተመሰረተው። ይህ አፈ ታሪክ ነው በዜና መዋዕሉ ውስጥ ላለው አፈ ታሪክ መነሻ የሆነው።

እንደ ልማድ (ትውፊት፣ ባህል) ሆኖ ኢትዮጵያን ማስተዳደር ወይም መግዛት ያለበት የሰሎሞን ዘር ያለው ሰው ብቻ እንደሆነ ይታመን ነበር። ትውልዱ ወደ ኋላ ሲቆጠር ቀዳማዊ ምኒልክና ንግሥት ሳባ ላይ ማረፍ አለበት። እነግሣለሁ ቢል እንኳ በመኳንንቱና በመሳፍንቱ እንዲሁም በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም። ለዚህም ነው ዐፄ ምኒልክ ‹‹የዐፄ ቴዎድሮስን ሞት ሲሰሙ ከይሁዳ ነገዶች ከዳዊትና ከሰሎሞን የምወለደው እኔ ነኝ ለንጉሠ ነገሥታዊው ዙፋን ከኔ የሚቀርብ የለም (ተክለ

ፃድቅ፣1982፣10) ብለው ወደ አፈ ታሪኩ የዞሩት፡፡ ምክንያቱም ከዚህ አፈ ታሪክ መውጣት ማለት ከፖለቲካዊውና ከሃይማኖታዊው ስርአት ውጭ መሆን ማለት ነው ተብሎ ይታሰባልና፡፡

የዐፄ ምኒልክ ዜና መዋዕል ደራሲ የሰሎሞን -ሳባን አፈ ታሪክ ለየት ባለ ስልት አበጅተውታል፡፡ ምኒልክ ከመቅደላ እስር ቤት ባመለጡበት ጊዜ ዋናው ጉዳይ ኢትዮጵያን መግዛት ሳይሆን የአባቶቻቸውን አገር፣ሸዋን፣ በእጃቸው ማስገባት ስለነበር፣ በሰሎሞናዊው ስርወ መንግሥት ትይዩ የሸዋ ስርወ መንግሥትን በማቆም፣ ምኒልክን ወደዚያ ስልጣን ለመውጣት መብት እንዳላቸው ይሰብካሉ፡፡ ደራሲው የአንኮበርን ከተማ ከመሰረተው ከአብዬ ተነስቶ አምሀ ኢየሱስን፣ አስፋ ወሰንን፣ ወሰን ሰገድን፣ ሳህለ ሥላሴንና ሃይለ መለኮትን በመጥቀስ በመጨረሻ ላይ ‹‹ ትንቢት የተነገረለት ሱባኤ የተቆጠረለት ምኒልክ ተወለደ›› (ገብረ ሥላሴ፣ 32-41) ይላሉ፡፡

የሁለቱ አፈ ታሪኮች ፋይዳ የዜና መዋዕሉን ባለቤት ፖለቲካዊ መብት ማስጠበቅ ነው፡፡ የሸዋው ስርወ-መንግሥት አፈ ታሪክ ሸዋን ዐፄ ቴዎድሮስ በሸዋ ላይ ከሾሙት፣ ከአቶ ባዛብህ እጅ ነጥቆ ለምኒልክ ለመስጠት፣ በዚህም የሸዋ ህዝብ ድጋፍ እንዲሰጥ ለማድረግ ነው፡፡ የሰሎሞን-ሳባ አፈ ታሪክ ደግሞ ምኒልክ ሸዋን ባስተማማኝ ሁኔታ በቁጥጥር ስር ካደረጉ በኋላ የመላው ኢትዮጵያን ግዛት ለመውረስ እንዲያስችላቸው የሚያደርግ ነው፡፡ ሌሎች ለምሳሌ ዐፄ ምኒልክንና ዐፄ ዮሐንስን ለማስታረቅ (ገጽ80) ፣የእንጦጦ ከተማ አመሰራረት (ገጽ 97) ፣የደብረታቦር ከተማ አመሰራረትና ስያሜ (ገጽ 120) ስለ አዲስ አበባ መቆርቆር (ገጽ 138)ን የመሳሰሉ አፈ ታሪኮች በምኒልክ ዜና መዋዕል ውስጥ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ፣ የዐፄ ምኒልክ ዜና መዋዕል በአፈ ታሪክ የተሞላ ነው፡፡ አጀማመሩ በአፈ ታሪክ ነው (ገጽ 13)፡፡ በዜና መዋዕሉ ውስጥ ያሉ ድርጊቶች እና ሁነቶች በአፈ ታሪክ የተደገፉ ናቸው (ገጽ 55፣62፣66...)፡፡ ሌላው ቀርቶ የዜና መዋዕሉ አጨራረስ እንኳ ፎክሎር ነው፡፡ ደራሲው

> *በዚህም ቀን የዳዊት ልጅነትዎን አስታወቁ፡፡ ዳዊት ገና በሕይወቱ ሳለ ልጁን ሰሎሞንን በከተማው አዙሮ ከርሱ በኋላ የሚነግሰው ሰሎሞን እንደሆን ለእስራኤል አስታውቆ ነበርና ጃንሆይም እንዲህ አደረጉ፡፡ (ዝኒ ከማሁ ፣347)*

በማለት መፅሐፍ ቅዱሳዊ ጠቃሽ ዘይቤን በመጠቀም ዐፄ ምኒልክን በንጉሥ ዳዊት፣ ልጅ ኢያሱን በሰሎሞን መስለው አቅርበዋቸዋል። የስርወ መንግሥቱን ቀጣይነትም አሳይተዋል።

በዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል የሚገኘው አፈ ታሪክ ከላይኛው አፈ ታሪክ የተለየ ነው። የቴዎድሮስ ዘሮች በንግሥና ላይ የቆዩ አልነበሩም። አባቱም ቢሆኑ ቋራ በምትባል አገር ላይ ከመሾም ያለፈ ታሪክ አልነበራቸውም። ስለዚህ የሰሎሞን-ሳባ ወይም የሸዋ ስርወ መንግሥትን በአፈ ታሪክነት መጠቀሙ ቴዎድሮስን ወደ ስልጣን ለማምጣት የሚበጅ አይደለም። ስለሆነም የቀደመውን አፈታሪክ የሚሽር ሌላ አፈ ታሪክ እናገኛለን። «...በስም ክርስቲያን ተብለው በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ፈንታ አስማት፣ ምንዝር፣ ዒልት፣ ጥመት ባደረጉ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ቀናኢ ነውና ንጉስ ቴዎድሮስን አስነሳ፤ ሁሉን የሚቀጣ» (አስፋው፣ 1902፣ 3)። (የተሰመረበት የእኔ ነው)

ደራሲው ‹‹እነሱ›› እያለ የሚጠራቸውን የዘመነ መሳፍንት ገገርዎችን እግዚአብሔር ሃይልን ቢሰጣቸው ሌሎቹን ለማጥፋት ተጠቀሙበት ፤ ስልጣን ቢሰጣቸው በስልጣኑ ባለጉበት፣ ነገረ እግዚአብሔርን ለህዝቡ አስተምሩ ብሎ ወንጌልን ቢሰጣቸው ወንጌሉን በሃጢያት አረከሱት፤ በማለት ወቀሳ ባዘለ ቋንቋ ይገስፃቸዋል። እግዚአብሔር ቃሉ ባለመከበሩ፡ ቃሉን የሚያስከብር ሰው መላኩንም ይሰብካል። ቴዎድሮስ ስልጣን የያዘው በክብረ ነገሥቱ አፈ ታሪክ አይደለም ።አፈ ታሪኩን በመከተል ስልጣን ላይ የወጡ ነገሥታትን ለመቅጣት እንጂ።

የቴዎድሮስ ወደ ስልጣን መውጣት ትንቢት የተነገረለት ሰባኤ የተቆጠረለት ጉዳይ ነው ልክ እንደምኒልክ ሁሉ። ልዩነቱ የቴዎድሮስ ትንቢት መነገር ከተለመደው የስርወ መንግሥት አፈ ታሪክ ውጭ በመሆኑ ነው። በፍካሬ ኢየሱስ መፅሐፍ ውስጥ እንደምናየው ‹‹ከምስራቅ በኩል ታሪካዊና ደገኛ ንጉስ ይነሳል። እሱም ፈቃዴን የፈፀሙትንና ከመከራ ያተረፍኳቸውን የሚሰበስብ ነው›› (ተስፋ፣1966፣ 59) የሚል ትንቢት ነበር። በሁለቱ ዜና መዋዕሎች ውስጥ የቀረቡት አፈ ታሪኮች አይነት ይለያይ እንጂ በይዘት ግን ተመሳሳይ ናቸው። የሁለቱም አፈ ታሪኮች ዓላማ ወይም ጠቀሜታ የነገሥታቱን ክብር መጠበቅ፣

መንግሥታቸው የተገባ መሆኑን መስበክ፣ ነገሥታቱ የእግዚአብሔር ልዑካን መሆናቸውን በማሳየት የተገኙዎቻቸውን እና /ወይም የተከታዮቻቸውን መገዛት ማረጋገጥ ነው።

## 4.2 በታሪክ መፃሕፍት ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ቅርፆች

የአፈ ታሪክ ጉዳይ እንደ ዜና መዋዕሎች አይሁን እንጂ በታሪክ መፃሕፍቱ ውስጥም ይገኛል። ቢሆንም ግን በታሪክ መፃሕፍቱ ውስጥ ከአፈታሪኮቹ ይልቅ ሌሎች የሥነቃል ዘሮች ማለትም ቃላዊ ግጥሞች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ፈሊጣዊ ንግግሮች ወዘተ. በብዛት ይገኛሉ።

የታሪክ መፃሕፍት፣ ስለታሪክ እንጂ ስለ ነገሥታት ክብር የቆሙ ባለመሆናቸው፣ ነገሥታቱ በነገሱበት ዘመን የሆነውን ሁሉ የተነሳውን ጠብና ክርክር፣ ነገሥታቱ ጠብና ክርክሩን ለመፍታት የወሰዱትን እርምጃ፣ እርምጃውን ተከትሎ ህዝቡ ለነገሥታቱ ያለውን ነገር (ተቃውሞውን፣ ድጋፉን፣ እርግማኑን፣ ሙገሳውን ወዘተ...) ያካትታሉ።
ለምሳሌ፡-

*በላይኛው ጌታ በባልንጀራው*
*በቅዱስ ሚካኤል በጋሻ ዣግሬው*
*በጻላተ ሙሴ በነጭ አበዛው*
*ጎጃምን ይማሩት ፈሪም አንልው*
(ተክለ ፃድቅ፣1982 ፣504-505)

የሚለውን ብንወስድ፣ በታሪክ መፃሕፍት ውስጥ ያሉ የፎክሎር ቅርፆች እንደዜና መዋዕሎቹ ውዳሴ ብቻ እንዳልሆኑ እንረዳለን። ዐፄ ዮሐንስ ንጉሥ ተክለሃይማኖት (የጎጃሙ) በመክዳታቸው ንጉሡ የተደበቁበትን ተራራ በመድፍ ማፈራረስ ይጀምራሉ። አልሆን ሲላቸው ወደ ጎጃም መለስ ይሉና መዝረፍን፣ መግደልንና አገርን ማቃጠልን ስራዬ ብለው ይያያዙታል። በዚህ ጊዜ ነው አንዲት ከብቷ የታረደባትና ልብሷ የስተገፈፈባት ሴት እላይ የቀረበውን ግጥም የገጠመችው።

ግጥሙ ከላይ ሲታይ ሙገሳ ወይም ውዳሴ ይመስላል። የላይኛውን ጌታ ጓደኛ፣ የጌታውን ዋና አገልጋይ (ሚካኤልን) የእሳቸው ጠባቂ፣ የሙሴን ታቦት የእድላቸው መታያ

በማድረግ ንጉሱ ቅዱስ መሆናቸውን ያሳያል። ነገር ግን ድምፀቱ ምፀት ነው:: ግጥሙ ለማን አቤት ይባላል? አቤት የሚባልለት እግዜሩ ሳይቀር ባልንጀራዎ ከሆነ ለማን ይከሰሳሉ? ተው ባይ፣ ከልካይ የለብዎ! መልዕክትን የያዘ ነው። ይህ አይነቱ የተቃውሞ ጩኸት በሌላኛው የታሪክ መፅሐፍ ውስጥም አለ።

*ልብሴንም ገፈፈው ለበሰው እርዘኛ*
*በሬዬንም ነዳው አረደው ነፍጠኛ*
*እህሌንም ዘረፈው በላው ቀለብተኛ*
*ንጉስ የቀረዎ ጥቂት አማርኛ*
*ምነው ሆድ አይዘርፉ አርፌ እንድተኛ*

(ተክለ ፃድቅ፣1981 ፣247)

መቼም የንጉሥ ባለሟሎች ‹‹እርዘኛ›› የታረዙ ወይም የተራቡ እዳልሆኑ አይካድም። አባባሉ ምፀት አዘል ነው:: መግፈፍ፤ መዝረፍ፣ መግደል ልማድ ሆኖብዎ እንጂ ምን አጣሁ ብለው ይዘርፉናል? ልማድ መጥፎ አይደል! ሆድንም ይዘርፉ ዘንድ ይወዱ ነበር ኮ ! የሚል ድምፀት አለው። ዐፄ ቴዎድሮስ ሰዎች በየአቅጣጫው እየሸፈቱ ሲያስቸግሯቸው ጊዜ በየሀገሩ እየዞሩ ይቀጡ ጀመር። እላይ የቀረበው ግጥምም ንጉሡ በጎንደር፣ በደብረ ታቦር፣ በዘጌ፣ በደምቢያ፣ በሜጫና በወገራ አካባቢዎች እየዞሩ ሲዘርፉ፣ ሲገርፉ፣ ሲገድሉና አገርም ሲያቃጥሉ የተገጠመ ነው። የገጣሚዋ መልዕክት ባዶ ቤት ይገፍ ያውም በባዶ እጀ ከምቀመጥ (ከምራብ) መሞት በምን ጣእሙ የሚል ነው። በተለይም በዐፄ ምኒልክ ዜና መዋዕል ውስጥ የተነሳ የሸዋ ስርወ መንግሥት አፈ ታሪክ ነበር። በዚያ አፈ ታሪክ መሰረት ምኒልክ ከመቅደላ እስር ቤት አምልጠው ወደ አባታቸው (ወደ ሃይለ መለኮት) ግዛት (ወደ ሸዋ) ይሄዳሉ። ያኔ ሸዋን ይገዛ የነበረው አቶ በዛብህ ምኒልክ ሸዋ እንዳይገባ ለመውጋት ይነሳል። በዚህ ጊዜ አንዲት ነገር አዋቂ ሴት

*ማነው ብላችሁ ነው ጋሻው መወልወሉ*
*ማነው ብላችሁ ነው ጦራችሁ መሾሉ*
*ማነው ብላችሁ ነው ካራችሁ መሳሉ*
*የጌታችሁ ልጅ ነው አረ በስመ አብ በሉ*

(ተክለ ፃድቅ፣1985 ፣28)

በማለት ተቀኙት ይባላል፡፡ ገጣሚዋ «የጌታቸሁ» ማለቷ የምኒልክን አባት፣ ሃይለ መለኮትን መጥቀሷ ነው፡፡ ሃይለ መለኮት ዐፄ ቴዎድሮስ ሸዋን እስከሚቆጣጠሩ ድረስ የሸዋ ንጉሥ ነበሩ፡፡ በመሆኑም የገኘው ልጅ ሲመጣ መከልከሉ ምንድ ነው? ሸዋ የምትጠብቀው እሱን አይደለምን? በዛብህ ቢነግሥ ለጊዜው ተሹሞ (የሰሎሞን-ሸዋ ስርወ መንግሥት የማይመለከታቸው ቴዎድሮስ የሸዋ ስርወ መንግሥት የማይመለከተውን ሰው ሾሙ ለማለት ነው) ነው እንጂ የሸዋ ገዥ ሊሆን ይችላል እንዴ? በማለት የሰውየውን ለጦር መጋበዝ ትወቅሳለች- ገጣሚዋ፡፡ ግጥሙ አፈ-ታሪኩን የሚመለከት ነው፡፡

ምኒልክ ከነገሡ በኋላ የጎጃሙ ንጉሥ ይሞታሉ፡፡ ጎጃሜዎች ጎጃምን ለጎጃም ብለው ሲጠብቁ ንጉሠ ነገሥቱ ግን በጎጃም ላይ ሌላ ሹም በመሾማቸው እንዲህ ተብሎ ተገጠመባቸው፡፡

*እሳት ቢያንቀሳቅሱ ገለባ ነበኘው*
*የአባ ጠናን አገር ማነው የተመኘው*
*ምን ያለ ንጉስ ነው ቂሙን የማይረሳ*
*የአባ ጠናን አገር ሰጠው ለኮሳሳ*

*(ተክለ ፃድቅ፣1985 ፣ 661)*

ዐፄ ምኒልክ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ጠቅላላ ግዛት ላንዱ ልጃቸው ወይም ለሶስቱም ልጆቻቸው ሳያከፋፍሉ በመቅረታቸው ይባስ ብለው ጎጃምን ለሌላ ሰው በመስጠታቸው ነው የጎጃም ሰው ተቃውሞውን የገለጠው፡፡ ‹‹ቂሙን የማይረሳ›› የሚለው ሃረግ ንጉሠ ነገሥቱ ከንግሥናቸው በፊት ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር ያደረጉትን ጦርነት ለመግለጽ ነው፡፡

መርስዔ ኀዘን ደግሞ እሳቸው ‹‹ህዝቡ›› የሚሉት ያነሳውን ተቃውሞ እንዲህ አቅርበውታል፡፡

*ንግስት ዘውዲቱ እንዳማረብዎ*
*አያሌ ገስግሷል ይቀባ ራስዎ*
*እግርን ወደራስነ ራስን ወደታች*
*ማድረግ አይመችም አትድከሙ ሰዎች*

*(1999፣ 352-353)*

ተቃውሞው የተነሳው በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ላይ ነው። የተቃውሞው ምንጭ ደግሞ ‹‹ይቀባ ራስዎ›› በሚል ቅኔያዊ ስልት የቀረቡት ራስ ተፈሪ ናቸው። ራስ መሆናቸው ይብቃ፣ ይንገሱ፣ ነው መልዕክቱ። ሰውየው ከንግሥተ ነገሥቷ በአስተሳሰብም ሆነ ከሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት መሻላቸውን ለመግለጽም ‹‹ራስን ወደታች.. ማድረግ አይመችም›› የሚል ሃሳብ ቀርቧል። ዘውዲቱን በእግር ተፈሪን ደግሞ በጭንቅላት በመመሰል አቅርበዋቸዋል።

በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ ያሉት የፎክሎር ቅርፆች ስሜታቸው ወይም መንፈሳቸው አንድ አይነት ነው። በዝርውም ይቅረቡ በግጥም፣ በልማድም ይቅረቡ በቁሶች ላይ ባረፉ ምልክቶች መንፈሳቸው ነገስታቱን ማወደስና የተመረጡና የተቀደሱ መሆናቸውን መስበክ ነው። አቅጣጫቸው አንድ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የፎክሎሩ ባህሪ ሳይሆን የዜና መዋዕሎቹ የራሳቸው ባህሪ ነው። በታሪክ መፃሕፍቱ ውስጥ ያሉት ግን አቅጣጫቸው ሁለት አይነት ነው። በታሪክ ውስጥ ክፉና ደግ፣ ጥቁርና ነጭ፣ ውድቀትና ትንሳኤ፣ ሹመትና ሽረት ስላሉ የፎክሎር ቅርፆችም የዚሁ ነፀብራቅ ናቸው። እላይ የቀረቡትም የሚያሳዩት ይህን እውነት ነው። እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ይነሳ ይሆናል፣ ተቃውሞዎቹ ሁሉ የቀረቡት በቃል ግጥም ብቻ ነውን? በእርግጥ አይደለም። ቃላዊ ግጥሞች ገነው ስለሚታዩ እንጂ ተቃውሞዎቹ በተረትና ምሳሌዎችም ፣ በቀልድም ቀርበዋል። ቀልዱን ለአብነት ላንሳ፤ ቀልዱ የተጠራበት ዘመን ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው በፊት የነበረው ዘመነ መሳፍንት ነው። ራስ ዐሊና ደጃች ውቤ ከተዋጉ በኋላ የጦርነቱን ወሬ ያልሰማ አንድ መንገደኛ ወሬውን የሰማውን ሰው ይጠይቀዋል።

*‹‹እባክህ የራስ ዐሊና የደጃች ውቤ ጦርነት በምን አለቀ?››*

*መላሽ- ‹‹ ከተዋጉ በኋላ ደጃች ውቤ ተማርከው ታሰሩ ፤ ራስ ዐሊ ደግሞ ሸሹ››*

*ጠያቂ - ‹‹ ኧረ ባክህ በወግ አድርገህ ንገረኝ››*

*መላሽ ‹‹ እነሱ ራሳቸው በወግ ያልሆኑትን ፡ እኔ እንዴት አድርጌ በወግ ላውራህ!›› አለውና እየሳቀ መንገድን ቀጠለ።*

*(ተክለ ፃድቅ፣1981፣100)*

ቀልዱ በራስ ዐሊና በደጃች ውቤ ስም ይቅረብ እንጂ በተለይ ስለነሱ ብቻ የተባለ አይደለም። ሁለቱን ሰዎች ተመርኩዞ ስለዘመኑ ጠቅላላ ሁኔታ የተባለ ነው። ራስ ዐሊ ርዕሰ መሳፍንት በመሆናቸውና የሹም ሽሩ ባለቤት በመሆናቸው እሳቸውን የዘመኑ ተጠሪ ማድረግ ይቻላል።እንዲሁም ራስ ዐሊ የዘመነ መሳፍንት የመጨረሻው ወኪል በመሆናቸው እሳቸውን የዘመኑ ተጠሪ ማድረጉ ያስኬዳል። ራስ ዐሊና ደጃች ውቤ የአንድ ዘመን ሰዎች ቢሆኑም እርስበርስ ተዋግተዋል። ‹‹ራሳቸው በወግ ያልሆኑትን›› የሚለው ሀረግ ከሁለቱ ሰዎች መጣላት ባለፈ ዘመኑ የበታቹ የበላዩን አንቆ የሚገድልበት፣ ሀገርና ህዝብ ዋጋ አጥተው ሁሉም እንዳሻው እየተነሳ ‹‹ዘራፍ›› የሚልበት፣ ያሰህግ የወደደውን የሚሾምበትና የጠላውን የሚሽርበት መሆኑን ማሳያ ነው። ቀልዱ ቀልድ ብቻ ሳይሆን መራራ ትችትም ነው።

እንደ ትችቱ ሁሉ ሙገሳም በታሪክ መፃሕፍቱ ውስጥ ቀርቧል። ልዩነቱ በታሪክ መፃሕፍቱ ውስጥ ያሉት የሙገሳ ሃሳቦች የቀረቡት በቃል ግጥም ሲሆን በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ ያሉት ደግሞ በጥሬው (በዝርው- በትረካ፣ በአስተያየት)፣ መቅረባቸው ነው።

ዜና መዋዕሎች የነገሥታት ክብር መጠበቂያዎች በመሆናቸው ያንኑ ክብር ለማጉላት ሲባል አፈ ታሪኮች ጥቅም ላይ ይውላሉ። የታሪክ መፃሕፍት ደግሞ ነገሥታቱ የኖሩበትን ዘመን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች በቦታውና በጊዜው ላልነበረ ሰው ስለሚዘግቡ፤ ለዚህ ዓላማ የመረጧቸውን ቃላዊ ቀልዶች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ልማዶች በውስጣቸው ይዘዋል።

## 5. ማጠቃለያና አስተያየቶች

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የፎክሎርን ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መፃሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ በመመርመር ላይ ያተኮረ ነው። የተክለ ፃድቅ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት ፣ ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፣ ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት የመርስዔ ኀዘን፣ የዘመን ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት ከ1896-1922 ፣ የባሕሩ ዘውዴ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1966 የተሰኙት የታሪክ መፃሕፍት እንዲሁም የገብረ ሥላሴ ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ እና የአለቃ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ ዜና መዋዕሎች በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል።

በተመረጡ የታሪክ መፃሕፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ አራቱም የፎክሎር ቅርፆች ተገኝተዋል። እነሱም ሥነ ቃል ፣ህገረሰባዊ ልማድ፣ ቁሳዊ ባሕል እና ትውን ጥበባት ናቸው። እነዚህ የፎክሎር ቅርፆች በመፃሕፍቱ ውስጥ በሁለት መንገድ ገብተው ይገኛሉ። አንደኛው ታሪክ ፀሀፊው ሆን ብሎ ሃሳቡን ለመግለፅ የሚፅፋቸው እንደ ምሳሌያዊ ንግግሮችና ፈሊጦች ያሉት ሲሆኑ ሌላው ደግሞ ፀሀፊው እንደ አንድ ክስተት ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ዘግቧቸው የሚገኙ ናቸው። በወቅቱ እንዲህ ተነገረ ፣ተዘፈነ፣ ተበላ፣ ተጠጣ፣ እንዲህ አይነት ዕምነት ነበር በማለት የፃፏቸው ናቸው።

በመፃሕፍቱ ውስጥ የተገኙት የሥነቃል ቅርፆች ቃልግጥም ፣አፈ ታሪክ፣ ቀልድ፣ ፈሊጣዊ ንግግሮችና ተረትና ምሳሌዎች ናቸው። ከፍተኛውን ቁጥር የያዙትም ቃልግጥሞች ሲሆኑ 125 (አንድ መቶ ሃያ አምስት)ያህል ናቸው። ቃል ግጥሞቹ በብዛት የተገኙት በታሪክ መፃሕፍቱ ውስጥ ሲሆን 113 (አንድ መቶ አሥራ ሦስት) ይደርሳሉ። ዋና ይዘታቸውም ድጋፍና ተቃውሞን መግለጽ ነው። ከታሪክ መፃሕፍቱም እነዚህን ቃል ግጥሞቹ በስፋት የተጠቀሙት ተክለ ፃድቅ ሲሆኑ በተለይም በ ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት መፅሐፍ ውስጥ 47 ያህል ቃል ግጥሞች ይገኛሉ። በአንፃሩ በባሕሩ የአትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1966 ውስጥ ሦስት ቃል ግጥሞች ብቻ ጥቅም ላይ ውለዋል። ለቃል ግጥሞቹ ማነስ እንደምክንያት ማቅረብ የሚቻለው የፎክሎር ቅርፆቹ ማን? ፣ የት?፣እንዴት?ና በምን ሁኔታ? እንደተናገሯቸው በተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ ስለሚያስቸግርና የተአማኒነት ጥያቄ ስለሚያስነሱ በዘመናዊ የታሪክ ፀሀፊያን ዘንድ ተቀባይነታቸው አነስተኛ በመሆኑ ይመስላል።

የታሪክ መፅሐፍ ተነባቢና አይረሴ እንዲሆን ቋንቋው ከፍተኛ ሚና አለው። በመሆኑም ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ፈሊጣዊ ንግግሮች እና ዘይቤዎች በታሪክ መፃሕፍቱም ሆነ

በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በተለይም ባሕሩ 43 ፈሊጣዊ ንግግሮችን እና 10 ያህል ምሳሌያዊ ንግግሮችን በታሪክ ድርሰታቸው ውስጥ ተጠቅመዋል፡፡ ፀሀፊው እነዚህን የሥነ ቃል ቅርፆች በመጠቀማቸው ቋንቋው ቀላልና በየትኛውም የእውቀት ደረጃ የሚገኝ አንባቢ ታሪኩን እንዲረዳው አስችሎታል፡፡

በታሪክ መፃሕፍቱም ይሁን በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ የሚገኙት አፈ ታሪኮች ለታሪክ ድርሰቱ በዋናነት በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉ ናቸው፡፡በተለይ የሰሎሞን ሓባን አፈ ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ መሰረት እንደሆነ በመረጃነት ተጠቅመውበታል፡፡ ይህን መሰሉን አፈ ታሪክ በመረጃ ምንጭነት የመጠቀም ሁኔታ በባሕሩ መፅሐፍ ውስጥ አይታይም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ማስረጃ ማቅረብ የማይቻልበትን ነገር ከመጠቀም ለመቆጠብ ይመስላል፡፡

ሀገረሰባዊ ልማዶችም እንደሥነ ቃሎቹ በተለያየ ቅርፅ ለጥናቱ በተመረጡት መፃሕፍት ውስጥ ገብተዋል፡፡ የተለያዩ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች፣ ስያሜዎችና ሀገረሰባዊ መድሃኒቶች በዋናነት በመፃሕፍቱ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ትንቢት፣ ህልም ፣ዛር፣ ጋኔን፣ አደ ከብሬ፣ ጥንቆላ የመሳሰሉት ሀገረሰባዊ ዕምነቶች የታሪክ መፃሕፍቱ በወከሉት ዘመን በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ግልጋሎት እንደነበራቸው ከመፅሐፍቱ ተለቅመው የወጡት ጥቅሶች ያስረዳሉ፡፡

ስያሜዎቹም ስመ መንግሥት ፣ክርስትና ስምና የፈረስ ስም ሲሆኑ ከነገሥታቱ እና ከመኳንንቱ ግላዊ ባሕሪ ፣ ተግባር እና ከወደፊት ዓላማቸው ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጥናቱ በተገደበበት ዘመንም ዘመናዊ ሕክምና ባለመስፋፋቱ ባሕላዊ ሕክምና በስፋት ጥቅም ላይ ውሎ እንደነበር በመፃሕፍቱ ሰፍሯል፡፡

ቁሳዊ ባሕልን በመፅሐፍ ውስጥ ለማጥናት አመቺ ባይሆንም የተለያዩ አልባሳትን ፣ ልዩ ልዩ መገልገያ ቁሶችንና የምግብ ሥርዓቶችን በመመርመር የዘመኑን ገፅታ እና አስተሳሰብ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በተለይም ግብር ከምግብ ሥርዓትነቱ በተጨማሪ ፖለቲካዊ ፋይዳው የጎላ እንደነበር በጥናቱ ተመልክቷል፡፡

በሰባቱም መፃሕፍት ውስጥ የሚገኙ ትውን ጥበባት የማይታዩ እና የማይደመጡ በመሆናቸው ከስሜት የራቁ ናቸው፡፡ ይሁንና ለልዩ ልዩ በዓላት፣ ለሠርግ ፣ለለቅሶ ለልዩ ልዩ የሰልፍ ትዕይንቶችና ለመሳሰሉት ጉዳዮች የተከወኑ ትውን ጥበባት በመፃሕፍቱ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

በመፃሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የፎክሎር ቅርፆች የራሳቸው ፋይዳ አላቸው። ይኸውም የታሪክ ተዋንያኑ ስሜታዊና ስነልቦናዊ ማንነት ምን ይመስላል? ርዕያቸው ምንድው? ፍልስፍናቸውስ ምንድነው? ለሚለው ምላሽ አፅንኦት አግኝቶ ጎልቶ እንዲወጣ ፎክሎር የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። በተለይ የሥነቃል አንድ ዘርፍ የሆነው ቃል ግጥም የታሪክ ተዋንያኑን ውስጣዊና ውጫዊ ማንነት በማሳየት ረገድ የላቀ ድርሻ አበርክቷል። እንዲሁም የመረጃ ምንጭ በመሆን ፣ ጭብጥ በማጉላት፣ ለግጭት መንስዔ እና ውጤት በመሆን የዘመኑን መንፈስ በማሳየት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አበርክተዋል።

በታሪክ መፃሕፍቱ እና በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ቅርፆች በንፅፅር ሲጠኑ አንድነትና ልዩነት እንዳላቸው መረዳት ይቻላል ። አንድነታቸው በሁለቱም የፅሁፍ አይነቶች ውስጥ አራቱም የፎክሎር ቅርፆች መገኘታቸው ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ የፎክሎር ቅርፆቹን በስፋት ከመጠቀም ላይ ነው። በታሪክ መፃሕፍቱ ድጋፍና ተቃውሞን ገላጭ ቃል ግጥሞች ጎልተው ሲታዩ በዜና መዋዕሎቹ ውስጥ ደግሞ አፈ ታሪኮች ትልቁን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ። ዜና መዋዕሎች የነገሥታቱን የቀን ተቀን ውሎ፣ የውጊያ ጀብዱ፣ ወዘተ.እያጋነኑ የሚተርኩ በመሆናቸው፣ በውስጣቸው ያሉትም የፎክሎር ቅርፆች ይህንኑ የሚያጎሉ ናቸው። የነገሥታቱን «አይነኬነት»፣ «አይደፈሬነት»እና«አይከሰሴነት» ያጎሉት ነገሥታቱ በአምላክ የተመረጡ መሆናቸውን በመስበክ ነው። ስለሆነም ለልዩነቱም ምክንያቱ የፅሁፍ አይነቶቹ ግላዊ ባሕሪ መሆኑ በጥናቱ ታመልክቷል።

በአጠቃላይ ፎክሎርና ታሪክ በእጅጉ የተሳሰሩ የሙያ ዘርፎች መሆናቸው በጥናቱ ተመልክቷል።

## 5.2 አስተያየት

- የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያወሱ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች በየቤተመዘክሩ ተቀርስው ይገኛሉ። ከነዚህ ቁሶች ጋር ተያይዞ የነገሥታቱን የአገዛዝ ሥርዓት ፣የአኗኗር ባህልና ጥበብን የሚናገሩ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በርካታ ናቸው። ለምሳሌ የነገሥታቱ የአልባሳት አይነቶች፣ ደረጃቸው፣ ጠቀሜታቸው፣ የተሰሩበት ቁስና የመሳሰሉት እንዲሁም ልዩ ልዩ ስያሜዎችና የግብር ሥርዓቶች በዝርዝር ተጠንተው ቢቀመጡ በታሪክ ሰነድነት ከሚሰጡት ፋይዳ በተጨማሪ የአሁኑም ሆነ ቀጣዩ ትውልድ ከመረጃዎቹ የሚቀስማቸው ቁም ነገሮች ይኖራሉ የሚል ዕምነት አለኝ። ስለዚህ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት እንደ ባሕልና ቱሪዝም፣ ቅርስ ጥበቃ ቢሮዎች፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተገቢውን ትኩረት ቢሰጡት መልካም ነው እላለሁ።

- የኢትዮጵያን ነገሥታትና መሪዎች በተመለከተ የተነገሩ ቃል ግጥሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተረሱ እንደውም ጨርሶ እስከ መጥፋት እየደረሱ በመሆናቸው ቃል ግጥሞቹ ከፅሁፍ ሰነዶችም ይሁን በወቅቱ ከነበሩ ግለሰቦች ተሰብስበው ተቀርሰው ቢቀመጡ በቅርስነት ብሎም የዘመኑን ታሪክ በማሳየት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። በመሆኑም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንደነዚህ አይነት የፎክሎር ቅርፆችን ቢያሰባስቡና ቢያስጠኑ መልካም ነው እላለሁ።

- ፎክሎር በቀዳማይ የታሪክ መረጃ ምንጭነት ማገልገሉ ይታወቃል። ይሁንና የፎክሎርን አንዳንድ ቅርፆች በተለይም ዘመናዊ ታሪክ ፀሀፊዎች ማስረጃ አይገኝላቸውም በማለት ጨርሶ ያለመጠቀም ሁኔታ ይታያል። ነገር ግን እነዚህ የፎክሎር ቅርፆች በተለይም ማህበራዊ ታሪክን ለመፃፍ የሚሰጡት ጠቀሜታ ከፍ ያለ በመሆኑ በድፍኑ «ተረትና ቀልድ» ነው ብሎ ከመተው ከሌሎች መረጃዎች ጋር በማጣቀስ ለታሪክ ምርምርና ፅሁፍ ቢጠቀሙበት የተሻለ ይሆናል ። እንዲሁም የታሪክ ድርሰቱ የአንባቢን ስሜት የሚማርክ እንዲሆን እንደ ምሳሌያዊ ንግግር ያሉትን የሥነቃል ቅርፆች ትኩረት ሰጥተው ቢጠቀሙባቸው መልካም ነው።

## ዋቢ መጻሕፍትና ፅሁፎች

### የአማርኛ ምንጮች


መርስዔ ኅዘን ወልደ ቂርቆስ። የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት። አዲስ አበባ ፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፤1999።

ማኅተመ ሥላሴ። ዝክረ ነገር ። አዲስ አበባ፤ ነጻነት ማተሚያ ቤት፤ 1942።

______________። የኢትዮጵያ ባህል ጥናት።ቼ፡በለው ። አዲስ አበባ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ፤ንግድ ማተሚያ ቤት ፤ በ1961።

ስርግው ገላው (ተርጓሚ)። ክብረ ነገስት ግዕዝና አማርኛ። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፤ 1994።

ባህሩ ዘውዴ(ተርጓሚ) ። የኢትዮጵያ ታሪክ ከ 1848 እስከ 1966። አዲስ አበባ ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ 1989 ።

ተስፋ ገብረ ስላሤ። ፍካሬ ኢየሱስ። አዲስ አበባ፤ ተስፋ ማተሚያ ቤት፤ 1966።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት። አዲስ አበባ 1981። ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤ 1981።

______________ ። ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት። አዲስ አበባ ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤ 1982።

______________ ። ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት። አዲስ አባባ ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ፤ 1985።

ታደሰ ታምራት። ‹‹ተረትና ታሪክ በኢትዮጵያ›› ውይይት። ቅፅ 1፣ ቁጥር 2 ፤ በኢትዮጵያውያን የዩኒቨርሲቲ መምህራን ማህበር የሚታታም መጽሄት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤1984።

______________። «አፋዊ ታሪክ፤ መሠረቱ፣ ዘይውና ምስክርነቱ»። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ። (1973)።

አስፋው ተፈራ (ተርጓሚና አዘጋጅ)። የቴዎድሮስ ታሪክ (ዜና መዋዕል)። አዲስ አበባ ፤ ቼምበር ማተሚያ ቤት፤ 1966።

እሸቴ ዳምጤ:: «ስለ አፄ ቴዎድሮስ አፄ ዮሐንስና ምኒልክ የተነገሩ የአማርኛ ቅኔያት ይዘት ንጽጽራዊ ጥናት» በቋንቋዎች ጥናት ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፤1995::

ክነፈ-ርግብ ዘለቀ:: «የቃል ታሪክ»:: ለትውፊት ሰሚናር የቀረበ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርመር ኢንስትቲዩት፤ 1973::

ያለው እንዳወቀ:: የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር:: ባህርዳር ፤ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፤ 1998::

ገብረ ስላሴ ወልደ አረጋይ:: ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ:: አዲስ አበባ ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ሊሚትድ፤ 1956::

ፈቃደ አዘዘ:: የሥነቃል መምሪያ:: አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት ፤ 1991::

## የእንግሊዘኛ ምንጮች

Bahru Zewde. "Ethiopian Historiography: Retrospect and Prospect" roceedings of the symposium. Institute Of Ethiopian StudiesI.Addis Ababa AAU; 1988.

Campa, Arthur L. "Folklore and History". Online. Available at://www.jstor.org/journals/. 1965.

Christiansen, Reidar Th. European Folklore in America. Oslo;1962.

Dorson, Richard M. Folklore and Folklife: An Introduction. London, University Press of Kentucky; 1972.

Georges, Robert A. and Michael Owen Jones. Folkloristics: An Introduction. Bloomington and Indianapolish ; Indiana University Press, 1995.

Gottschalk, Louis. Understanding History. New York: University of Chicago; 1945.

Leach, M. Standard Dictionary of Folklore, Mythology and Legend. New York: Funk and Waqgnells Company; 1950.

Levine, Lawrence W. "How to Interpret American Folklore Historically" In Richard M.Dorson,ed, HandBook of American Folklore. Bloomington:Indiana University Press;1983.

Luthi, Max. The European Folktale. London: University of Chicago; 1986.

Marwick, Arthur (3rd ed). The Nature of History. London; 1989.

Mayo, Edith.."Focus on Material Culture." In American Material Culture: The Shape of Things Around Us. Edith Mayo (ed.) Bowling Green: Bowling Green Sate University Popular Press; 1984.

Nye, Russel B. " History and Literature: Branches of The Same Tree" In Essays on History and Literature .Robert H.Bremner (ed.) Ohio State University Press; 1966.

Oman, Charles. On The writing of History. London: Barnes and Nobel,inc;1969.

Oring,Elliot. Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction.Logan,Utha: Utah University Prees, 1986.

Sergew Hable Sellassie. Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270. United Printers, Addis Ababa,1972.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions, Utah State University Press, United State of America, 2005.

Vansina, Jan. Oral Tradition as History. Great Britain, 1985.

አባሪ

## ቃልግጥሞች

### ዐፄ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት

- አሁን ወጻች ገ'ምበር፣ ተሸሸጋ ነበር።
  አሁን ወጻች ጨረቃ፣ የምትለን ፍርድ ይብቃ
  ደስ ይበልህ ዘመድ፣ ከነገሰች በዘውድ
  ደስ ይበልህ ባለጌ ከነገሠች ይተጌ
  ደስ ይበልህ ጐንደር ቀድሞ ከፍቶህ ነበር /36/

- አያ በስቀላህ ውሃ መላ ፤በስቀላህ ውሃ መላ
  የተራበ ዘመድ እንዳይበላ፣ በስቀላህ ውሃ መላ
  ወይ እርሱ ሳለ ቀሊስ ኢያሱ ለጋሡ
  አንተ የወፍላ ንጉሡ/39/

- ባልቴቲቱ በምን ትጦሪ
  ሳዱላይቱ /ልጃገረዲቱ/ በምን ትዳሪ
  ጎጃም ሄደና እንጀራው ዶሪ
  ጎበና መጣ ቋንጃ አስመታሪ/56/

- የክንፉ ጐራዴ ጥቁር የነበረ
  እየቀላ ሔደ ቱርክ እየመሰለ/107/

- አያችሁት ብያ የኛን ዕብድ
  አምስት ጋሞች ይዞ ጉር አምባ ሲወርድ።
  ያንጓብባል እንጂ መች ይዋጋል ካሣ
  ወርደህ ጥመድበት በሸምብራው ማሳ።
  ወዶ ወዶ በሴቶቹ በነጉንጭት ለምዶ።
  ሐሩ ቋዱ፣ ለውዙ ገውዙ አለ ቋራ
  መንገዱ ቢጠፋ እኔ ልምራ።/126/

- ጎሹ እንደ አርዮ፣ ዐሊ እንደ ዳዊት
  ከጥንት አይደለሞይ ተልኮ መሞት።/127/

- አወይ ያምላክ ቁጣ ፤አወይ የግዜር ቁጣ
  አፍ ወዳጁን ያማል ሥራ ሲያጣ
  ሽመል ይገባዋል ያዝማሪ ቀልባጣ/127/

- መከራን በሰው ላይ እንደዚያ ሳቀለው
  እንዲህ ይከብዳል ለተሸከመው ሰው።/141/

- ተዋቡን ሲያገባ ሠርጉ መች ደመቀ
  ደራስጌ ስናየው መልሱ አንጸባረቀ
  ፊትማ ሲያገባት ተክሲል መች ነበረው
  ካሣ ደረስጌ ነው በሕግ የተዳረው
  ሊቃውንት፤ ካህናት ካንድ ላይ በሙሉ
  ጐንደር አልነገሠም ብለው ያድማሉ
  በከንቱ ነው እንጂ ፤በራስ ፍርድ ለማምጣት
  ዘውዱ ከተሠራ ሆኗል አሥር ዓመት
  ለኢትዮጵያ ሲደክም ካየነው
  የነገሡበት ደረስጌም ጐንደር ነው።/142/

- ሺህ ሐመር፣ ሺህ ዳለች ፤ሺህ ቦራ...... ይሉት የነበረ የሸዋ ፈረስ
  አንድ ጥርኝ ቀረ፤ ቢዘልቅ ቴዎድሮስ /171/

- ቁርጡን ዐወቁና አለመኖርህን
  በረከት አገቡት ጌታዬ /ኃይለ መለኮት/ ልጅህን /171/

- አያችሁ ጉድ፤ የሚስት መናኝ
  የእናት ሹመት ለማኝ/176/

- እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሔድ
  እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ/185/

- እጅግ ሥራ ዐዋቂ ትናንት ሞተች
  መድኃኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች/185/

- ጠጅ አማረኝ ስላት ማሩን ታስጭናለች
  ራበኝም ስላት እህሉን ታስጭናለች
  በረደኝም ስላት ሸማ ትሰዳለች
  ሌባዬ ተይዛ ባልጋ ትሔዳለች
  የት አባቷን ዐውቃ ታሳዝነኛለች።
  የጣቴን ቀለበት አንተ አድርገው ካሣ
  በኔማ ጣት (በኔ ማጣት) ገብቶ አስጨነቀኝሣ/186/

- ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ
  የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነሥተውት ሄዱ /197/

- ባለድባብ ንጉሥ፤ ባለጥና አቡን
  እየዞሩ ፈቷት ኢትዮጵያን /198/

- የሸዋ መኳንንት እንግዲህ አትልፉ
  ተመዞ የነበር ተከተተ ሰይፉ /198/

- ጎጃምን ብንቆጣው በእሳቱ ተቀጣ
  ወሎን ብንቆጣው በነፍጡ ተቀጣ
  ይብላኝ ለወራሄ (ወረሂመኑ) ይብላኝ ለሰቆጣ /214/

- ጋረድ ሞተ እንኳን ተቀበረ
  ያንተ ወንድም ነውና እንፈራው ነበረ /220/

- ይብላኝ ለንጉሤ ጆርባው ተከፈተ
  ይብላኝ ለተሰማ ጆርባው ተከፈተ
  የወንዶቹ /የነቴዎድሮስ/ ወንድም አባ ገልበጥ ሞተ/220/

- ቴዎድሮስ ነገሠና
  እባብ ጠፋ በጎዳና
  ወንበዴም ሔዶ ምነና
  ገቢያችንም አለ ፈሰስ (ደመቀ)
  ጋለሞታችንም አለች ፈርነስ (ተዝናናች) /220/

- መገን ሣህሉ አባ ጆቢራ
  ሣምሳ በፊት ሣምሳ በኋላ፤ ሣምሳ በቀኝ ሣምሳ በግራ
  ክርክር አይቀርም ከዚያ ሰው ጋራ
  ከፍ ሲል ከዚያ ሰውዬ (ከቴዎድሮስ)
  ዝቅ ሲል ከገብርዬ
  ዘራፍ አትበሉ
  ይቆጣችኋል ተሰማ ሣህሉ
  ተሰማ ሣህሉ ባወጣው ጠጅ
  ይንጫጩበታል እንደ ወፍ ልጅ
  ደራሽ በቦራ አስጨናቂ በመከራ
  የንጉሤን ቤት ሠራው በኖራ.../233/

- አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ
  እንደዚህ አንድዶ፤ ለብልቦ ይፍጃችሁ /245/

- እንግዲህ ለታቦት አልሰጥም ስለት
  አዲት መድኃኔ ዓለም ነዶ አገኘሁት/246/

- ሞጣ ቀራንዮ ምነው አይታረስ
  በሬ ሳላይ መጣሁ ከዚያ እስከዚህ ድረስ።
  በሰንሰለት ታስሮ ዓመት ካራት ወር
  ማገን ዋስ አግኝቶ ተፈታ ጉንደር /246/

- ልብሴንም ገፈፈው ለበሰው እርዘኛ (የተራቆተ)
  በሬዬንም ነዳው አረዳው ነፍጠኛ (ወታደር)
  እህሌንም ዘረፈው በላው ቀለብተኛ (የተራበ ቀለብተኛ)
  ንጉሥ የቀረዎት ጥቂት አማርኛ
  ምነው ሆድ አይዘርፉ አርፌ እንድተኛ (ከምራብ ቢገድሉኝ) /247/

- ቴዎድሮስ ሲመጣ ዐይኑን አፍጦ
  ወይ መሸሸጊያ ትንሽ ቁጥቋጦ /248/

- ዘራፍ!ዘራፍ! ያንተ አሽከር የነፍስ ቢሱ
  በደም ይዋኛል ከነአውራሪሱ /261/
- ይማሩዋል እንደ አካልዬ
  ይዋጉዋል እንደ ገብርዬ /267/

- አንተም ጌታ አይደለህ እኔም ያንተ ሎሌ
  የኢየሩሳሌም ሰው ካልጫነ በርሞሌ
  ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም
  ዐርብ፤ ዐርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም /269/
- የታጠቅ ፈረሶች እንዴት ያሽካካሉ
  ባሕር ማዶ ጨፌ መለቅም ያስባሉ
  አበሻ በመላው ምን ያጉመተምታል
  በመርከብ ተሻግሮ ገና ባሕር ይዘምታል /270/

- የኔታ ደጃዝማች (ውቤ) ሁልጊዜ ደግነት
  ዛሬ እንኳ ለደሃው እንባ አተረፉለት /367/

- ከንግዲህስ ወዲያ የልቤን ልናገር
  አባ መላክ ተድላ ጠጁ ውሃ ነበር
  በሸዋ ተላከ ጥናው ሊመጣ ነው
  በትግሬ ተላከ ጥናው ሊመጣ ነው
  ተድላ ጓሉ ሞቶ ጒጃም ሊፈታ ነው
  አልሞተም ይሉናል ደጃዥማች ተድላን
  አሁን እሑድ ሲቀር የምናውቀውን /367/

- በመቅደላ በኩል ጨኸት በረከተ
  የሴቱን አናውቅም ወንዳንድ (ወንድ አንድ) ሰው ሞተ፡፡ /439/

- ዳር እስከ ዳር ይዞ የገዛው ንጉሥ፤
  እንዲህን ስሱ ነው (እንደዚህ ስስታም ነውን)
  ጠበንጃ እሚጒርስ፡፡ /439/

- ጠላቶቹን ሁሉ አጭዶ እንደ ገብስ
  መቅደላ ተጣለው ራሱን በራስ። /439/

- አባትና እናቱ አላንድ አልወለዱ
  አባ ታጠቅ ካሣ ያው አንዱ፤ ያው አንዱ (ያ ወንዱ፤ የወንዱ) /439/

- የትግሬንም ንጉሥ ፤የሸዋንም ንጉሥ ሲንቀ ሲንቁ፤
  ወንድ አለራስዎ ገድለውም አያውቁ። /439/

- አያችሁት ብያ (ወይ) ያንበሳውን ሞት
  በሰው እጅ መሞትን ነውር አድርጎት። /439/

- ገደልን እንዳይሉ ሙተው አገኙዋቸው፤
  ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው፤
  ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው?
  ለወሬ አይመቹም ተንኮለኛ ናቸው።/439/

- አምላክን መስሎ ቴዎድሮስ፤
  ንዑና ሑሩ (ኑ ሒዱ) ሲል ዋለ ሐሙስ።
  ሰኞ (የሞተበት ቀን) መቅደላ ተጨነቀ፤
  ሰው መሆኑ ታወቀ። /439/

- ቀስ ብለው ግቡ ዝግ ብለሁ ግቡ፤
  ደሞ እዚያ ላይ (እሰማይ ቤት)
  ወጥተሁ እንዳታስቸግሩ፤
  እኔው ብቻ ልግዛ ነውና ነገሩ/440/

- መላው የጎጃም ሰው፤ መላው የትግሬሰው ተይዞ በምጥ፤
  የእንግሊዝ ሐኪሞች መጥተው ቢይዙት፤
  ተገላገለ አሉ ይህ ሁሉ ፍጥረት። /440/

- እሳት መጥቶ ተቋራ፤
  ድፍን አበሻን ሲበላ፤
  እንግሊዝ መጥቶ አጠፋው፤
  ለእግዜር እግዜር አለው። /440/

- ዐርባ ቀን (ሁዳዴ) ጠሞ ጠሞ ፋሲካ ሲደርስ
  ባፈር (በአፈር) ገደፈ (ፋሲካን ፈስክ) አሉ ያበሻ ንጉሥ። /442/

## ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት

- ከቱርክ ይዋጋል እንኳን ካንካሳ
  ያባ ፈነቅል ልጅ ወሬሳው ካሳ/27/

- ንጉሥ ማራኪ ከነ ዘውዱ
  የበዝብዝ አሽከር አሉላ ወንዱ
  ከነፋስ የፈጠነ
  በወንድነቱ ይተማመነ
  ክንዱ ብርቱ እንዳንበሳ
  በጣላት ሠፈር የሚያገሳ /29/

- መቼ ኮረብታው መች አፍቀራ ነው
  መቼ ፈረሱ መች ቦራ ነው
  መቼ መሣሪያው መች ጠበንጃው ነው
  በዙ አባ ድክር እሱን ያኮራው
  ሐሞቱ እንጂ ነው፤ ባንድ የተሠራው /73/

- አንተም ጨካኝ ነበርክ ጨካኝ አዘዘብህ
  እንደ ገና ዳቦ እሳት ነደደብህ /75/

- የበዙ ፈረሶች በራና ጠለፋ እንዴት ይግረማቸው!
  ገርማሜ ባንድ እግሩ ሲኮረኩራቸው
  እሳቸው (ምኒልክ) ቢሰጡት እሱ (ገርማሜ) መቀበሉ
  ከነልቡ ነወይ ከነ አዳፋፈሩ ። /75/

- ከላይ የወረደው ከጽዮን መቅደስ
  ባባቱ ሚካኤል በናቱ ሥላስ
  አጨደው ከመረው ያን ያሕዛብ ገብስ
  ወቃው ደበደበው ሰጠው ለንፋስ
  ዐሊሙ ነፍጠኛ ዐፄ ዮሐንስ /151/
- ሲሆን ተከናነብ ሳይሆንም አጣፋው
  መታጠቅ /ማደግደግ/ አይሆንም ለእንዳንተ ያለ ሰው። /180/
- እንዴት ያለ ሩቅ ነው ጭንቅ ያለው መንገድ!
  አሻቅቦ ወጥቶ ወደታች መውረድ።/180/

- ታናሽ ታላቅ በላን ከርካ አደባባይ
  ክርስቲያን ሆይ አለልብ ሥጋ ይጣፍጣል ወይ /200/

- እነዚህ ጎጃሞች በምን ይሥቃሉ
  ጥርሳቸውን ሊሙ ጥለውት ሔዱ አሉ /204/

- እበላለሁ እገዛለሁ ብሎ ከእንጦጦ ገሥግሦ!
  በዮሐንስ አምላክ አሰኘው ደረሶ /204/

- የምኒልክ ነገር ይመስለኛል ተረት
  አሞራው በቀፎ ውሻው በሰንሰለት /294/

- መብቱን ዮሐንስ ሳሉ ላ ቢሰጠው
  እንደ ቀትር እሳት ቱርክን ገላመጠው
  ጣሊያንም ወደቀ እያንቀጠቀጠው
  አጭዶና ከምሮ እንደ ገብስ አሰጣው /390/

- አባ ነጋ አሉላ ካሥመራ ቢነሣ
  እንደ አንበሣ ሆኖ እሳት እያገሣ
  የችግር ምስጋና ባይወሳ
  ቢቸግረው ጣሊያን አለ ፎርሳ ፎርሳ /390/

- ጣሊያን በሀገርህ አልሰማህም ወሬ
  የበዝብዝ አሽከሮች እነሞት አይፈሬ
  ዘለው ጉብ ይላሉ እንደ ጉፈር ዐውሬ /390/

- አባ ነጋ አሉላ የደጋ ላይ ኮሶ
  በጥላው ያደክማል እንኳንስ ተቀምሶ /390/

- ጣሊያን ሰሐጢ ላይ እግሩን ቢዘረጋ
  በብረት ምጣዱ በሰሐጢ አደጋ
  አንገርግቦ ቅላው አሉላ አባ /390/

- ተው ተመከር ጣሊያን ይሻላል ምክር
  ሰሐጢ ላይ ሆነህ መሬት ብትቆፍር
  ኋላ ይሆንሃል ላንተው መቃብር
  የች አገር ኢትዮጵያ የበዝብዝ አገር
  ምንም አትቃጣ እንደራስ ነብር /390/

- በበላይኛው ጌታ በባልንጀራዎ
  በቅዱስ ሚካኤል በጋሻ ዥግሬዎ
  በድላላ መሴ በነጭ አባዛዎ
  ጉጃምን ይማሩት ፈሪም አንልዎ/505/

- ዘንድሮ ንጉሡ ደህና ቢመለሱ
  ምንኛ ጉልድፏል ጉጃሜ መላሱ /529/

- የዮሐንስ በቀሎ ብረኪ ብረኪ
  በመተማ በኩል መጣልሽ ማራኪ /530/

- አይታሰስም ምጣድ በግምጃ
  ዘንድሮ ደርቡሽ መትረፉን እንጃ /449/

- ጎጀም የምትሔዱ እንደኔ እማትቀሩ
  እርኩስ አርማ ሞተች ብላችሁ ንገሩ /451/

- ሣር ውሃ ከሜዳው የተዘራ አዝመራ
  አጫጁ ደርቡሽ ነው ሰብሳቢው አሞራ
  አትክለክልምይ /ተ/ሃ/ ይዘህ አለንጋህን
  አሞራ /ደርቡሽ/ ሲበላው የገዛ ገላህን /ምንትዋብን/ /451/

- አይሆንም እንጂ ተሆነማ
  ተመጋዞ ይሻላል ጉልማ/463/

- አፄ ዮሐንስ ሞኝ ናቸው
  እኛም ሁላችን ናቅናቸው
  ንጉሥ ቢሏቸው በማኸሉ
  ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ
  በጎንደር መተኮስ በደንቢያ መታረድ አዝኖ ዮሐንስ
  ደሙን አፈሰሰ እንደ ክርስቶስ
  እንዳያምረው ብሎ ድሃ ወዳ ጁን
  መተማ አፈሰሰው ዮሐንስ ጠጁን
  የጎንደር ኃይማኖት ቆማ ስታለቅስ
  አንገቱን ሰጠላት ደግማይ ዮሐንስ
  እጅግ ደስ ይለኛል ያንተ ስም ሲነሣ
  የቁና አፈር ንፉግ አንተ ነህ ወይ ካሣ /548/

## ዐፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት

➢ ማነው ብላችሁ ነው ጋሻው መወልወሉ
ማነው ብላችሁ ነው ጦራችሁ መሾሉ
ማነው ብላችሁ ነው ካራችሁ መሳሉ
የጌታችሁ /የኃይለ መለኮት/ ልጅ ነው አረ በስመ አብ በሉ /25/

➢ የበረከት ለታ ከሸንጡ ተዋግቶ
ከሻንቅላ ጋራ አብሮ ተቆራኝቶ
አገር ለምኒልክ እያለ ቆይቶ
ሊወጋቸው ሄደ የሰው ነገር ሰምቶ
አንተም አደረግሽኝ የመነኩሴ ፈራጅ
የሙት ልጅ ሲቀበል እንዲህ ነው ወይ ወዳጅ /26/

➢ አላጌ እበሩ ላይ ሲወድቅ ማገሮር
እንደ ግራኝ ሁሉ በስባት አረር /254/

➢ ከነፍጥ ጉበዝ አየሁ /የጠመንጃ ስም/
ካሽከር ገበየሁ /256/

➢ አባተ አባ ይትረፍ ነገረኛ አዋሻኪ ሰው
ይኸን መድፍ ከዚያ መድፍ አቆራረጠው /288/
➢ ቢነግሩሽ ቢነግሩሽ አታጠናቅሪ
እንደ ተርኪስ ባቡር ተገትረህ ቅሪ።/597/

➢ ባቡርም ተጫነ ስልክም ተናገረ
ይኸ በማነ ጊዜ ተደረጎ ነበረ
ምኒልክ ነቢይ ነው ሆዴ ጠረጠረ።
የሐበሻው ንጉሥ ምኒልክ ነቢይ ነህ
ኃላፊውን ትተህ መጭውን ታውቃለህ /598/

➢ ንጉሥ አይቆጡ የቀረች መስሎዎ፤
ዕዳዬን ከፍዬ እስትከተልዎ። /610/

- በተድላ በጉሹ ያልነበረ ነገር፤
  በከርሠ መቃብር ከአቡን መነጋገር፡፡ /610/

- ምን ይጠጣ ይሆን የነገው እንግዳ፤
  ጠጁ በአየራሱ በየዐይኑ ተቀዳ፡፡ /610/

- እንግዲህ የምኔ የጌታ ወዳጅ፤
  እወሀ /እንባ/ ይሰጣል ወይ አስመስሎ ጠጅ፡፡ /611/

- ዋ ዐፄ ምኒልክ እግዚአብሔር ያጥናዎ
  በየበሩ ቋሚ ከልካይ ሞተብዎ
  ሲታሰር አየነው ብረቱ ሲመታ
  ማን ዋስ አገኘና ሐረርጌ ተፈታ
  ጃንሆይ ምኒልክ ጠጉራቸው ሳሳና በራ ገለጣቸው
  እንግዲህ ምኒልክ ምን ራስ አላቸው /614/

- እሳት ቢያንቀላፋ ገለባ ኅበኘው፤
  የአባ ጠናን አገር ማነው የተመኘው፡፡/660/

- ምን ያለ ንጉሥ ነው ቂሙን የማይረሣ፤
  የአባ ጠናን አገር ሰጠው ለኮሳሳ፡፡
  ጋሻውን ውሰዱት ጐራዴውን ውሰዱት ነፍጡንም ውሰዱት
  ...እንዲሆን ለምስል፤
  የዚህ ቤት እዚያ ቤት አይገባ አይመስል፡፡/661/

- በስተቦረና በስተበላያ በስተደንገል በር ያቀናውን አገር፤
  አስረክቦት መጣ አወይ የልጅ ነገር /661/

- ፈረስ በቅሎ ስጠኝ ብዬ አለምንህም
  አምና ነበር እንጂ ዘንድሮ የለህም/666/

➢ ነጋሪት ማስመታት እምቢልታ ማስነፋት ነበረ ሥራችን
ሰው መሆን አይቀርም ደረሰ ተራችን /666/

➢ እልፍ ነፍጥ በኋላው እልፍ ነፍጥ በፊት
ባለወርቅ መጣብር አያሌው ፈረስ፤
ይመስለኝ ነበር ይኸ የማይፈርስ።

➢ ዘመን የበላንበቱ የጠጣንበቱ፤
የትሣሥ ባታ ለት ተፈታ ወይ ቤቱ።
ብትታመም ልጅህ እጅግ ጨነቀኝ፤
ብትሞትስ አልሞትም እኔ ብልጥ ነኝ።

ወልደውኛል እንጂ እኔ አልወለድሁዎ፤
አንገቴን ተብትበው ምነው መሔድዎ።

አሳዳጊ አላንተ አላውቅም እናት፤
ምነዋ ሞግዚቴ እንዲህ ያል ክዳት።

ቀድሞ የምናየው የለመድነው  ቀርቶ፤
እንግዳ ሞት አየሁ ካባቴ ቤት ገብቶ።

እጅግ አዝኛለሁ አላቅሽኝ አገሬ፤
የሁሉ አባት ሞቶ ተጎዳችሁ ዛሬ።

ትንሽ ትልቅ አይል ለሁሉ መስጠት፤
ከጧት እስከ ማታ ያለመስልቸት።

ድርቅ ሆኗል አሉ ዘንድሮ አገራችሁ፤
ዝናሙ ሲጠፋ ምነው ዝም አላችሁ።

አሻግሬ ሳየው እንዲያው በሰው ላይ፤
መከራም እንደሰው ይለመዳል ወይ።/667/

## የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922

- ባቡሩ ሰገረ ስልኩም ተናገረ፣
  ምኒልክ መልአክ ነው ልቤ ጠረጠረ። (21)

- ንጉሥ ትናንት ሞተው ጎጃም ተሸበረ፣
  እግሬ ባይታሰር ልቅሶዬ ነበር። (27)

- ስልከኛው ሲያረዳ ነገረ ተሳሳተው፣
  መኮንን አይደለም ደኸ ነው የሞተው።
  የኢትዮጵያ ንጉስ እግዚአብሔር ያጥናም፣
  በየበሩ ቋሚ ከልካይ ሞተብዎ።
  የሐበሽ ሁሉ ማረፊያ ነበረ፣
  አልጋውን መኮንን ይዞት ተቀበረ።
  የአድዋ ፊታውራሪ ያረርጌው ደጀን፣
  እንዳንድ ሰው ሞተ ራስ መኮንን። (32)

- የምኒልክ ድንኳን አውታሩ ብዙ ነው፣
  አደራ ጊዮርጊስ ተራዳው አንድ ነው። (44)

- ቀና ብዬ ባየው አፈሰሰ ቤቴ፣
  መጥተህ ክደንልኝ ታዬ ጉልላቴ። (68)

- እሳቱን እሳት እንዴት ወለደው፣
  የአባ ባሕር ልጅ ተሰማ ናደው። (77)

- ከት ከት ብላ ሳቀች ምድር አፍ ውጥታ፣
  አባተ ሲታሰር አብርሃ ሲፈታ። (88)

➢ ባልንጀራ ሳለኝ የማጫውተው፣
ምስጢሬ ተሰማ በሆዴ ያለው:: (90)

➢ አሞራው ዞረ አሞራው ዞረ፣
አበላው ኢያሱ ሥጋ እየመተረ::
የኢያሱ ጎራዴ በሐር የተሰፋው
እያመመው መጣ ደም እየከረፋው::(95)

➢ ቀድሞ  የምናውቀው የለመድነው ቀርቶ፣
እንግዳ ሞት አየሁ ከአባቴ ቤት ገብቶ::
እጅግ ያስገርማል ያስደንቃል ከቶ፣
ከሁለታችን በቀር እሚያወቀው ሰው ጠፍቶ::
ምልክቱ ይህ ነው የንጉሥ ሞት ሃዘን፣
ጣይቱ ስትጨልም ጨረቃ ደም ስትሆን::
ወልደውኛል እንጂ እኔ አልወለድሁዎ፣
አንጀቴን ተብትበው ምነው መያዝዎ
እጅግ አዝኛለሁ አላቅሰኝ አገሬ፣
የሁሉ አባት ሞቶ ተጎድተሃል ዛሬ::
ድርቅ ሆኗል አሉ ዘንድሮ አገራቸሁ፣
ዝናሙ ሲጠፋ ምነው ዝም አላችሁ::
አሻግሬ ሳየው እንዲያ በሰው ላይ፣
መከራም እንደሰው ይለመዳል ወይ::
ያች የሰጡኝ በቅሎ መጣባት ባለቤት፣
አልገዙም መሰለኝ ሲገኝ ነው ዕፍረት:: (104)

➢ እምቢልታ ማስነፋት ነጋሪት ማስመታት ነበረ ስራችን፣
ሰው መሆን አይቀርም ደረሰ ተራችን:: (104)

➢ እምዬ ምኒልክ ገንዘብ ስጠኝ ብዬ አላስቸግርህም
አምና ነበር እንጂ ዘንድሮስ የለህም:: (111)

- ቀን ይምጣ ሌት ይምጣ አታውቁትምና
  የሸዋ መኳንንት እንዳትሆኑ መና
  አልጋውን አይለቅም እያሱ አባ ጤና። (149)

- አያሌው አያሌው
  ገዳይ ከሱማሌው

- አባባ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥቱ
  እንኳዋን የሰውን ልጅ አውሬን የገዘቱ
  ልጅን ያለ አንቀልባ ያሳደግሁበት
  ቤቱን የለ መዝጊያ የተኛሁበት
  እንኳን በቁመናው ዛሬ እንኳን በሙቱ
  በምኒልክ ሲባል ይረጋል መሬቱ።(211)

- ታስሮ ተደብቆ የቀረ ምነው
  ሕልምነው ምኒልክ ጊዜ የፈታው።
  አልሞተም ይላሉ ሰዎች ንጉሡን
  ሸዋን ቢጠይቁት ምኒልክ ይሆን። (211)

- ዓይኔን ሰው አማረው ዓይኔን ሰው አማረው
  ወየው የሰው ያለህ የሰው። (211)

- የኢትዮጵያ ብርሃን ዛሬ ጠለቀች
  ሁሉን የምትጠቅም ጣይቱ ነበረች። (211)

- ስም በከንቱ አይወጣም ጣይቱ ተባለች
  አብቅላም አብስላም ታበላን ነበረች። (212)

- ወፎች ተሰብስበው ጭልፊትና ቁራ
  በዱር በገደሉ አልቀረም አሞራ
  በሾላው ጠባቂ አስነስተው ሴራ
  ሊያጠፉት መከሩ ከዚያ ሾላ ስፍራ
  እርሱ ከጠፋ ዘንድ ከዚህ ሾለ ስር

ነገደ አእዋፍ መጥተው ባንድ አይቀር
እየቀጣጠፉ ቢያደርቁት ከምድር
ምን ፍሬ ይገኛል ከጉዳት በቀር
ሰሚ የለም እንጂ የሚሰማስ ቢኖር
ለሾላ ጥበቃ የታዘዘውን ንስር
በፍቅር አድሰን በሰላም እንኑር
እስከዚህ ድረስ ነው እኔ ያሰብኩት ምክር
ይህን ተናገረ ገብረ እግዚአብሔር። (221)

- ጠጅም አልጠጣነ ከተለየናችሁ
  አውራው ከተያዘ ማሩን እባካችሁ። (242)

- ከምኒልክ ይዞ እስካሁን ድረስ
  ያልታየ ሞት ሆነ የሃብተ ጊዮርጊስ። (324)

- ንግሥት ዘውዲቱ እንዳማረብዎ
  ኤያሌ ገስግሷል ይቀባ ራስዎ።
  ገና ሳይቀባ እንዲህ ያደገ ራስ
  እንሆ ሲቀባ አድኅም አይመለስ።
  በከንቱ ይለፋል ከአልጋዎ ላይ ቀስቃሽ
  መች አንቀላፋና ልዑል አልጋ ወራሽ
  ባልጋ የታመሙ ብዙ ሰዎች አሉ
  መቼም በጎ አይሆኑ ጭራሽ ይደክማሉ።
  በፈቃድህ አይደል የወጣኸው በግድ
  አንተን የሚል ማነው ደግሞ ናልጋ ውረድ
  ብቻ እንደ ሰሎሞን እንዳባትህ ፍረድ።
  የተባረከ ነው የመኮንን ዘር
  ራስ ራስ ወልዶ እሸቱ ሲያምር።
  መኮንን ነው እንጂ ጠንካራ ገበሬ
  ዘሩ የሚበቃ ለሸዋ ለትግሬ።
  በሣህለ ሥላሴ ባባቱ መንግሥት
  እንግዳ መሰሏቸው ሊሸኙ አሰቡት።
  ሸዋ ሊያጌጥ ነበር ልቡ ያሰበው

ዋጋው ቸገረ እንጂ የራስ ማሠሪያው።
እንዴት አማረብሽ ዛሬ ብትዳሪ
ተፈሪን የሚያህል ልኩልሽ ፈጣሪ።
የመጣብን ሽክም በተፈሪ ታዞ
መች የሚያልቅ ነበር ተግዞ ተግዞ።
አቀለለው እንጂ መድኃኔ ዓለም አግዞ።
ከከተማው ጥፋ ብለውህ ነበር
እንዲህ እንደ ፀሐይ ሞቀህ ልትኖር።
እግርን ወደ ራስጌ ራስን ወደታች
ማድረግ አይመችም አትድከሙ ሰዎች።
ጭምት ነው ተፈሪ የመኮንን ልጅ
እሱ ምን አወራ ግድ አውራ አሉት እንጂ።
የተፈሪን ሸማ ማንም አይልበሰው
ጥበቡ ረቂቅ ነው ሲጥል ላየው ሰው።
ሃይማኖት ነው እንጂ ማነው ጠበቃህ
በያደባባዩ የሚቆምልህ።
ተፈጥመው ሄዱ ባላጋሮችህ።
አሁን ምን ይሆናል በከንቱ ሐሜት
እንደ ራስ እያዩ መፍረድ ነው በውነት።
የጊዜውን መድረስ ተፈሪ መርምር
መቼም አትታወቅ ጥላ ስትዞር።

## የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966

- እንግዲህ ጎጃሞች በምን ይስቃሉ
  ጥርሳቸውን ሊሙ ትተውት ሄዱ አሉ። /65/
- ብነግርሽ ብነግርሽ አታጠናቅሪ
  እንደ ተርኪስ ባቡር ተገትረሽ ቅሪ /103/
- ከኖይቱ ወረቀት ያስፈረመ የለም
  መላው ታጥቆ ገባ ግዴለም ግዴለም
  ትግሬም ገባ አሉ ሰምቶ በፍጥነት

ጎጃምም ገባ አሉ ሰምቶ በፍጥነት
የወሌውን ጉግሣ ሞኙን የኔን ጌታ መፈተኛ አርጎት /146/

## ታሪከ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ

- ወይ ጎሜ ጎሹ ወይ ጎሜ ጎሹ
  በድፍን አገር ዕዳ ነስናሹ (36)

- በነጋሪትዎ ሞት ተጥሮብዎ
  የወጣው አይገባ ያለው አይቆይዎ /51/

- ዐፄ ቴዎድሮስ ምነው ተዋረዱ
  የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነስተውት ሄዱ /53/

- አሥር ደጃዝማች የደረሰውን
  የወሌ ፈረስ ጠጣው ብቻውን /73/

- ከዚህ ቤት ገባች ዓለም እንግዳ
  እሱ ድል አድርጎ ምሽቱ ወንድ ወልዳ /73/

- ለ፺ ሲናድር ዋስ የጠራችሁ
  በሻህ አቦዬ ከፈለላችሁ::/83/

- ሴቶች ተሰብሰቡ እንውቀጥ ዳሄራ
  እርእር አይቀርም ከራስ አዳል ጋራ /103/

- ቀድሞም ጠቢቡ ነበር ሰሎሞን አባቱ
  ምኒልክ ይበልጣል ሰው ይዞ መብላቱ /207/

- ኢጣልያ መጥቶ ታቦት የሚያረክሰው
  የንጉሥ ፊታወራሪ ገበየሁ ቀደሰው:: /266/

- ወይዘሮ የውብዳር ጠፍታ መብራቲቱ
  ቀኑ ጨለመብን ሳትጠፋ ጣይቱ
  መልካም ባዝራ ሞተች የማትመለስ
  ሴት ወልዳ ለንጉሥ ወንድ ወልዳ ለራስ። /314/

- ዋ ዐፄ ምኒልክ እግዚአብሔር ያጥናዎ
  በየበሩ ቋሚ ከልካይ ሞተብዎ። /320/

## የቴዎድሮስ ታሪክ

- ጎጃምን ብንቆጣው በእሳቱ ተቀጣ
  ወሎን ብንቆጣው በነፍጡ ተቀጣ
  ይብላኝ ለወራሄ ይብላኝ ለስቆጣ /32/

## መግለጫ

ይህ ቴሲስ ( የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ) የእኔ ወጥ ስራ ሲሆን፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም :: ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ::

አዳነች አበራ

ስም

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ሰኔ፣ 2001 ዓ.ም.